# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::

## ምሥጢረ ሥጋዌ::

### "ተዋሕዶ"፥ "Orthodox" እና "Coptic" ስለሚባሉት ቃላት::

---

አዎን! እኒሁ: የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን: የእግዚአብሔር ልጅ: በፍጹም ሰውነት ስለመገለጡ: ቤተ ክህነታቸው ያላትን: "የምሥጢረ ሥጋዌ ሃይማኖታዊ አቋም: በትክክል ያስረዳልናል፤ ለዚህም ችግር መፍትሔ ሊኾነን ይችላል" ብለው ያከሉት: ይህ: "ተዋሕዶ" የሚለው ቃል: እውነትም: በኢየሱስ ክርስቶስ ስለተገለጸው: የትስብእትና የመለኮት የውሕደት ምሥጢር: ፍጹም የኾነውን ትርጉም: ያለምንም ሕፀፅ: በተሟላ ኹኔታ ሊያስተላልፍ የቻለ መልካም ምርጫ መኾኑ ታምኖበታል:: ይኸውም: "ተዋሕዶ" የሚለው: ይኸው ቃል: ቀደም ብዬ እንዳተትኋላችሁ: ተቀዳሚና ተከታይ ሳይኖረው: በመንፈስ ቅዱስ ግብር: ለአንድ ጊዜ ብቻ የተፈጸመውን: የእግዚአብሔርን ሰው የመኾን መለኮታዊ ምሥጢር: በሚበቃ ግልጽነት የሚያስረዳ በመኾኑ ነው:: እንዲህ: ረቂቅ የኾነውን: የሃይማኖት ነገር: አጉልቶና አግዝፎ፥ ምሥጢር የኾነውንም ገልጾና ተርጉሞ የሚያስረዳ በመኾኑ: ለዚህ "ተዋሕዶ" ለሚለው የተሟላ ኢትዮጵያዊ ቃል: "ኦርቶዶክስ" የሚል: ሌላ ባዕድ የኾነ ደባል: ባላስፈለገው ነበር፤ ራሱ: ብቻውን: በቂ ኾኖ ይገኛልና::

ባዕዳን ግን: ያንኑ: ጠንቀኛ ተግባራቸውን: አሁንም ሳያለዝቡ: ይህንኑ "ተዋሕዶ" የሚለውን ቃል: ሌላ የትርጓሜ ሓተታ እንዳለው በማስመሰል: ሊያማስኑት ሲሞክሩ ይታያል:: ይኸውም: "ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጸው: የሰውነት ባሕርዩን በማጥፋት: በአንድ የመለኮት ባሕርይ ብቻ ነው" ለሚለው: ለአውጣኪስ የኑፋቄ ትምህርት የተሰጠው: "Monophysite" "ሞኖፊዚት" የሚባለው ይትበሃል: ከዚሁ ከ"ተዋሕዶ" ቃል ጋር "ተመሳሳይነት አለው" እያሉ በሚያስፋፉት የሓሰት ትርጓሜያቸው ነው::

እንግዴህ: ኢትዮጵያ: የባዕዳን የኾነውን በማይከተለው: በራሷ ባህል: በቤተ ክህነቷ፥ በቤተ ምልክናዋና በቤተ ሕዝቧ መካከል መለያየትና መከፋፈል ሳይኖርባት: "ኢትዮጵያ: የእግዚአብሔር መንግሥት" በሚለው አቋሟ: አንዲት ስለኾነች፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም: በዚሁ: በባለሚሶ ዘርፍነቷ: የያዘችው: ይኸው ስሟ: እንዳለ: ማንነቷን: ራሱ ስለሚናገርና እርሱው ስለሚበቃት: ለኢትዮጵያም ያለቻት: ኢየሱስ ክርስቶስ: በአበው ልቦና: የመሠረታት፥ በነቢያት ቃል: ያጸናትና በሓዋርያት ጉባኤ የፈጸማት፥ በድንግል ማርያምም: ሕያው ኾና ህልውናዋን የቀጠለች: እርሷ: አንዲቷ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ስለኾነች: ሌላ ተጨማሪ መለያ ስያሜ ከቶ አያስፈልጋትም:: ዳሩ ግን: እውነታው ይህ ኾኖ ሣለ: በዚህ ስሟ ላይ: "Orthodox" የሚለው ስያሜ በመጨመሩ: ዛሬ ያለችውን: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን: የኢትዮጵያ ሳትኾን: የግብፅ መኾኗን: በራስ ምስክርነት ለማረጋገጥ ተቻለ:: ሌሎቹም ባዕዳን: ወደኢትዮጵያ ላስገቡት ሃይማኖታቸው: እየራሳቸውን: "በኢትዮጵያ" በማለት ፋንታ: "የኢትዮጵያ" ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን፥ "የኢትዮጵያ" ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን፥ ወዘተ. እያሉ ለመጥራት ለቻሉበት ማሳሳቻ: አመቺ በር ተከፍቶላቸው: ይህንኑ ልማድ: እንዴት: እየተጠቀሙበት እንዳሉ: ራሳችሁ የምትመለከቱት ነው:: ፺

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

### ስለምሥጢረ ሥጋዌ ማጠቃለያ።

*ጥያቄ:- እግዜር ይስጥልን! እስካሁን ላቀረብናቸው ጥያቄዎቻችን፡ ተገቢውን መልስ በማግኘት፡ በሚበቃ ተረድተናልና፡ የምሥጢረ ሥጋዌን ነገር፡ ብታጠቃልልን?*

*መልስ:-* የምሥጢረ ሥጋዌን ሐተታ፡ ከዚህ በሚከተለው ፍሬ ቃል፡ አጠቃልልላችኋለሁ፦ "'እግዚአብሔር ወልድ' ሰው በኾነ ጊዜ፡ በአንደኛው ወገን ያለው፡ የፍጹም አምላክነት፡ አካልና ባሕርይ፥ በኹለተኛው ወገን ያለውን፡ የፍጹም ሰውነት፡ አካልና ባሕርይ፥ ወይም፡ በኹለተኛው ወገን ያለው፡ የፍጹም ሰውነት፡ አካልና ባሕርይ፥ በአንደኛው ወገን ያለውን፡ የፍጹም አምላክነት፡ አካልና ባሕርይ፡ ሳያጠፋው፡ ወይም ሳይለውጠው፡ ወይም ሳይውጠው፡ በኹለቱም ወገኖች ያሉት፡ ፪ አካላትና ፪ ባሕርያት፡ በመንፈስ ቅዱስ ረቂቅ ጥበብ፡ በተዓቅቦ ተዋሕደው፡ ተቀዳሚ፡ ተከታይ በሌለው፡ በአንዱ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ አንድ አካል፥ አንድ ባሕርይ ኾነዋል፤ ይህም ማለት፡ ራሱን፡ በኹለትነት ሳይኾን፡ በአንድነት፡ “እኔ” ብሎ በሚጠራው፡ በአንዱ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ የተዋሕዶ ህላዌ ውስጥ፡ የሰውነት ፈቃድ፡ ለመለኮት ፈቃድ፡ ፈጽሞ በመገዛቱ፥ በዚህ፡ አንድ በኾነ ፈቃድ፡ መለኮት፡ የሰውነትን ሥራ፥ ሰውነትም፡ የመለኮትን ሥራ ሠሩ፡ ማለት ነው።

ተቀዳሚ፡ ተከታይ የሌለው ማለትም፡ ከእርሱ በቀር፡ ከፍጥረት በፊት አንሥቶ፡ እስከኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ድረስ ባልተደረገ፡ ከእርሱ ጀምሮና ከእርሱ በኋላ፥ እንግዲህ ወዲህም፡ ለዘለዓለም በማይደረግ፡ ዕፁብ ድንቅ በኾነ መለኮታዊ ምሥጢር፡ የቀደመውም ኾነ፡ የሚከተለው የሌለ፡ አንድ ወልድ ዋህድ፡ በሰውነት የታየበት፡ ፍጹም የብቸኛነት ህላዌ ማለት ነው። በዚህ ጊዜ፡ “አምላክ፡ በተዋሕዶ፡ ሰው ኾነ! ሰውም፡ በተዋሕዶ፡ አምላክ ኾነ!” የሚል ትርጉም ያለው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለው ስም፡ ለእግዚአብሔር ወልድ ተሰጠ። በፍጥረት መጀመሪያ፡ *“እግዚአብሔር አምላክ፡ 'እነሆ ሰው፡ ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!' አለ።”* የሚለውም መለኮታዊው የትንቢት ቃል፡ በእውን ተፈጸመ።

“ተዋሕዶ” የምንለው፡ የሃይማኖታችን ስም፥ “እግዚአብሔር ወልድ፡ በተዋሕዶ፡ ከኹለት አካላት፡ አንድ አካል፥ ከኹለት ባሕርያት፡ አንድ ባሕርይ ኾነ!” ብለን የምናምንበትም፡ “ምሥጢረ ሥጋዌ” የሚባለው፡ የሃይማኖት ትምህርትና እውቀት፡ ይህ ነው።

ምሥጢረ ሥጋዌ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ የቱን ያህል በሰውነታቸው ሠርፆና ጠልቆ፥ ሥር ሰድዶና ተወድዶ፡ በሕያውነት ተዋሕዷቸው የሚኖር መኾኑን፡ በገሃድ ከሚያሳዩት እውን ኹኔታዎች መካከል፡ ከትስብእቱ ጀምሮ፡ እስከ ትንሣኤውና ዕርገቱ ድረስ ያሉትን፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓላት የሚያከብሩበት ሥርዓትና ድምቀት፡ አንዱ ኾኖ ይገኛል፤ ይህንም፡ ወደፊት፡ ስለበዓልና በዓላት በምናደርገው ውይይታችን ላይ በስፋት እንነጋገርበታለን።

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
## ምሥጢረ ሥጋዌ።
### ስለምሥጢረ ሥጋዌ ማጠቃለያ።

---

ከዚህ ጋር፡ ከጾመ ነቢያት ጀምሮ፡ እስከዓቢይ ጾምና ሰሙነ ሕማማት፡ በተለይም፡ እስከሰሌተ ዓርብ የስቅለቱ ስግደት ድረስ ያሉትን ጾሞቻቸውን የሚፈጽሙበት የቀኖና ጽናት፡ እንዲሁም፡ ሕማማተ መስቀሉን በማዘከር፡ በየሳምንቱ የሚፈጽሙት የዓርብ ጾማቸው፡ በየወሩ፡ በ፳፯ኛው ቀን የሚውለው የመድኃኔ ዓለም የስቅለቱ መታሰቢያና በዓለ ወልድ ተብሎ፡ በ፳፱ኛው ቀን የሚውለው የጌታ የትንሣኤው በዓል፡ ስለዚሁ ስለኢትዮጵያውያኑ ሃይማኖታዊ አቋም፡ በሚበቃ ስለሚያስረዱ፡ ሌላ ማብራሪያ ከቶ አያስፈልግም።

ከዚህ በኋላ ተከታትለው፡ በቅደም ተከተል የሚቀርቡት ሦስት ምሥጢራት፡ ምሥጢረ ሥጋዌ ያስገኛቸው ናቸው፡ በእነርሱ አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር፡ ለሰው የተሰጡት ጸጋዎችም፡ በእያንዳንዳቸው ሐተታ ላይ ይብራራሉ። እንግዲህ፡ በ"ምሥጢረ ሥጋዌ" ላይ ያሏችሁ ጥያቄዎች፡ በዚህ ማጠቃለያ ከተካተቱ፡ ወደሦስተኛው ምሥጢር እናልፋለን።

## ምሥጢረ ጥምቀት።

*ጥያቄ፡- እስካሁን እንደተረዳነው፡ ስለሃይማኖታችን፡ በስፋትም ኾነ በጥልቀት ለማወቅ የሚያስችለንን ብሩህና ቀጥተኛ መንገድ፡ በዚህ ውይይታችን አማካይነት፡ ይኸው ተያይዘነዋል፡ ስለዚህ፡ ይህንኑ ያስጀመርኸንን የእውቀት ፈለግ፡ ከግብ ለማድረስ፡ እየናፈቅን ነንና፡ ስለሚቀጥለው ምሥጢር፡ የምትሰጠንን ማብራሪያ በጉጉት እንጠብቃለን።*

**መልስ፡-** የሚቀጥለው ርእሳችን፡ "ምሥጢረ ጥምቀት" ነው። በዚህ ምሥጢር፡ እግዚአብሔር፡ ከፍቅሩ ጽናት የተነሣ፡ በመልኩ እስከሚፈጥር የወደደው ሰው፡ ሴቷም፥ ወንዱም፡ ለሕይወታቸው ይበጃቸው የነበረውን፡ የእርሱን መለኮታዊ ፈቃድ ከመፈጸም ይልቅ፡ ራሳቸውን የሚጎዳ የክህደትንና የዓመፅን፥ የአመንዝራነትንም ሥራ በመፈጸም፡ የተቃዋሚው የዲያብሎስ ግብረ አበር በመኾናቸውና የክፋት ጐዳናን መርጠው በመከተላቸው ቢያሳዝኑትም፡ ያን ኹሉ በደል፡ ራሱን፡ በቤዛነት አቅርቦና ሠውቶ በመካሥ ይቅር ብሎ፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ዘለዓለማዊ ጸጋውን፡ ለእነርሱ፡ መልሶ ያጎናጸፈበት ቸርነቱ፡ በስፋትና በጥልቀት ይነገርበታል።

ይህ ምሥጢር፡ እያንዳንዱን አስተዋይ ሰብአዊ ፍጡር፡ "እኔ፡ ለእግዚአብሔር፡ እንዲህ *'ጠላቱ ስኾን'*፡ እርሱ ግን፡ ይህን የመሰለውን፡ ዕፁብ ድንቅ የኾነ፡ ይቅርታውንና ምሕረቱን ሊያደርግልኝ፡ እንዴት እንደገና ፈቃደኛ ኾነ?! ይህን ያስደረገ ኃይል፣ ከምን ዓይነቱ ፍቅር ሊመነጭ ቻለ?" በሚል የአንክሮ ጥያቄ እንዲመሰጥ፡ በእርግጥ ያስገድደዋል። ይህንም፡ ወንጌላዊው፡ *"'የእግዚአብሔር ልጆች' ተብለን ልንጠራ፡ አብ፡ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን፡ እዩ!"* ሲል፡ በመልእክቱ፡ አሳምሮ አስቀምጦታል። እግዚአብሔር፡ ይህን የመሰለውን፡ የእርሱ ልጆች ለመኾን የሚያበቃንን ታላቅ ጸጋ፡ ለሰው ልጅ የሰጠበት የቸርነት ሥራው፡ የሚነገርበት ትምህርት[፺፮] የሚገኘው፡ ከዚሁ ከ"ምሥጢረ ጥምቀት" ስለኾነ፡ "ምሥጢር" ተብሏል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ሰው፡ ነፍሱ፡ በምድራዊው ኑሮዋ፡ ገዝፋ የምትታይበትንና ለተወሰነ ዕድሜ፡ በጊዜያዊነት የምትቆይበትን፥ ማንነቷንና ምንነቷንም፡ በሃይማኖታዊ አቋሟና በምግባራዊ ድርጊቷ የምትገልጽበትን አካለ ሥጋ ለብሳ፡ ከማሕፀን እንደምትወለድ ኹሉ፡ እንዲሁ፡ በሰማያዊው ዓለም፡ ለዘለዓለም፡ በሕይወት ለመኖር የሚያበቃትን መንፈሳዊ አካል ለብሳ፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ የምትወለድበት ረቂቅ ሥርዓት፡ በፈጣሪዋ ቸርነት ተሠርቶላታል፤ ያም ሥርዓት፡ “ምሥጢረ ጥምቀት” ነው። እርሱም የተመሠረተው፡ *“ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፡ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው!”* በሚለው *መለኮታዊ ቃል ሲኾን፡ በዓይን የማይታየውና* በእጅ የማይዳሰሰው፡ ይህ፡ ረቂቅ ምሥጢር የኾነው መንፈሳዊ ሥርዓት፡ ገዝፎ እንዲታይ የተደረገው፡ *በውኃ ኾኖ ተገኘ።*[፶፰]

ይህን ሥርዓት፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ” ተብሎ፡ በምሥጢረ ሥጋዌ የተገለጸው፡ ራሱ እግዚአብሔር ወልድ፡ ዕድሜው፡ ፴ ዓመት ሲኾነው፡ በመጥምቁ በዮሐንስ እጅ፡ በዮርዳኖስ ወንዝ፡ በመጠመቅ፡ ለሥርዓተ ጥምቀት፡ በኵር ኾኖ፡ ራሱም፡ በአብነት ፈጽሞት፡ መሥርቶታል፤ ቀድሶታልም።

### የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት።

ጥያቄ:- *በመሠረቱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለምን ተጠመቀ?*

መልስ:- ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበት፡ የመጀመሪያው ምክንያት፡ ሰው የኾነው አምላክ፡ እርሱ መኾኑን፡ ለዮሐንስና ለዓለሙ በይፋ ለማሳወቅ ነው፡ የዚህ ነገር እውነተኛነት፡ ዮሐንስ፡ ባየውና በሰማው ተረጋግጧል፤ ይህንም፡ ዮሐንስ፡ ጌታን ባጠመቀው ጊዜ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ *“ሰማያት ተከፍተውለት፡ የእግዚአብሔር መንፈስ፡ እንደርግብ ሲወርድ፥ በእርሱም ላይ ሲቀመጥ አየ!”* ደግሞም፡ *“በእርሱ ደስ የሚለኝ፡ የምወድደው ልጄ ይህ ነው!' የሚል ድምፅ፡ ከሰማይ ሲነገር ሰማ።”*[፶፱] የሚለው ቃል ያስረዳል።

ኹለተኛው ምክንያት ደግሞ፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ፡ እግዚአብሔር በምድር ላይ የመሠረታትን መንግሥቱን፡ ከነሥርዓቷ በማፈራረስ፡ ዲያብሎስ፡ በሰውና በፍጥረተ ዓለሙ ላይ የዘረጋውን የክፋት ግዛት፡ በዚህ አገዛዙም ጠንቅ የሰፈኑትን የኃጢአት ቀምበርና የሞት ፍዳ፡ በእግሮቹ፡ እንደገል ቀጥቅጦና እንደሰም አቅልጦ ለማስወገድ ነው።[፷]

ሦስተኛውም ምክንያት፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ ሰው፡ አስወስዷት የነበረውን፡ ከእግዚአብሔር የመወለድን ታላቅ ክብር፡ በማስመለስ፡ ይህችን ልጅነት ለማግኘት፡ ፈቃደኞች ለኾኑ ወንዶችና ሴቶች፡ ይህንኑ ጸጋ፡ ለዘለዓለም ለማቀዳጀት ነው።[፷፩]

ጥያቄ:- *ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዮሐንስ እጅ፡ በዮርዳኖስ ወንዝ፡ በሚጠመቅበት ጊዜ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በራሱ ላይ፡ ስለምን፡ በርግብ አምሳል ወረደ?*

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
## ምሥጢረ ጥምቀት።
### የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት።

---

**መልስ:-** ቀድሞ: በጥፋት ውኃ ጊዜ: የውኃው ሙላት ጉድሎ እንደኾነ: ኣይቶ እንዲመጣ: ኖኅ: ከመርከቡ አውጥቶ ልኮት የነበረው ቁራ: ሳይመለስ ስለቀረበት: ርግብን ሰደዳት፤ እርሷም: እየበረረች ኼዳ: የውኃውን መጉደል: ተዘዋውራ አይታ: አለመጒደሉን በማየት: ይህንኑ ኹኔታ ለመግለጽ: ባዶዋን ተመለሰች: ከቀናት በኋላ: እንደገና በላካት ጊዜ ግን: ውኃው መጒደሉን በማረጋገጥ: ይህንኑ ለማመልከት: የወይራ ቀምበጥ: ባፏ ይዛ አምጥታ: አብሥራው ነበርና: አሁንም: ዓለምን: እንደጥፋት ውኃ ማዕበል ያጥለቀለቀው: የዲያብሎስ የክፋት ግዛት፣ የኃጢኣት ቀምበርና የሞት ፍዳ: ከሰውና ከፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ የሚወገድበት: የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት መፈጸሙን ለማብሠር: መንፈስ ቅዱስ: በርግብ አምሳል ተገለጠ።

**ጥያቄ:-** *የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት: በዮርዳኖስ ወንዝ የኾነበት: የተለየ ምክንያት ይኖረው ይኾን? ካለ: ብትገልጽልን?*

**መልስ:-** ዲያብሎስ: አዳምንና ሔዋንን: በተንኰሉ አሳስቶ: የፈጣሪያቸውን ፈቃድ እንዲተላለፉ: እነርሱም: የእርሱን አሳሳች ቃል ተከትለው ለመኖር በመስማማት: ግዝነቱን እንዲቀበሉ ካደረጋቸው በኋላ: ያሸከማቸውን የባርነት ቀንበር አጽንቶ ለማዝለቅ: በጽላተ ሙሴ ምሳሌ: "አዳምና ሔዋን: የዲያብሎስ ባሮች ናቸው!" የሚል ምልክት የታተመባቸው: ኹለት የድንጋይ ሰሌዳዎችን አዘጋጅቶ: አንዱን: በሲዖል፣ ኹለተኛውን: በዚህ: በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ አኑሮ እንደነበረ: በትውፊት የደረሰን አምላካዊ ቃል ይነግረናል። ስለዚህ: ያን የዕዳ ሰነድ ደምስሶ ለማጥፋት: ኢየሱስ ክርስቶስ: በዚህ ወንዝ ውስጥ ተጠመቀ። በሲዖል ያኖረውንም የዕዳ ሰነድ: መለኮት ከተዋሐደው ሥጋዋ: በሕማማተ መስቀሉ ፍጻሜ ላይ በተለየችው እካለ ነፍሱ: ኢየሱስ ክርስቶስ: ወደዚያ ወርዶ: ኹለተኛውን የዕዳ ሰነድ ደምስሶ አጠፋው፤ በዚያ የነበሩትንም: ያመኑትን ነፍሳት: ነጻ አወጣቸው።

**ጥያቄ:-** *ኢየሱስ ክርስቶስ: ጥምቀቱን: በውኃ ያደረገው ለምንድር ነው?*

**መልስ:-** *"የእግዚአብሔርም መንፈስ: በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር።"* የሚለው ቃል: ስለሥነ ፍጥረት በሚናገረው: በታላቁ መጽሐፍ መክፈቻ ላይ ተጽፎ ይነበባል፤ ስለዚህ: በጥምቀት ምሥጢር: ከእግዚአብሔር ለሚገኘው መንፈሳዊ ልደት ማስፈጸሚያ: ውኃን መርጦ መሠየሙ አያስደንቅም።

*ውኃ:* የሕይወት ምንጭ ነው፤ ማንኛውም ሥጋዊና ተንቀሳቃሽ ፍጡር: *ያለውኃ:* በሕይወት ሊኖር አይችልም። ዕፅዋት፣ አዝርዕትና እትክልት: የሚለመልሙት፥ የሚያብቡትና የሚያፈሩት: *በውኃ* መኾኑን የማይረዳ የለም። አያሌ የደዌና የሕመም ዓይነቶች የሚፈወሱት: በውኃ የኾነው: ከዚህ የተነሣ መኾኑ ሊታወቅ ይገባል። ምድር: ጸንታ፣ ተጠብቃና ተከብባ የምትገኘው: *በውኃ* ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ቸሩ ፈጣሪ፡ የምሥጢረ ጥምቀት ጸጋ የሚሰጥበትን ሥርዓት ለመፈጸም የሚያስፈልገው ዓቢይ ነገር፡ በምስኪኑ ደኃ ዘንድ ሳይቀር፡ በቀላሉ ሊገኝ የሚችለውንና የማይታጣውን፡ ውኃን የመሰለውን ተራ ሀብት እንዲኾን ማድረጉ፡ ይህንኑም ሲሳይ፡ አትረፍርፎ ማበርከቱ፡ የቸርነቱን ስፋ ልግሥና ያሳያል።

*ጥያቄ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ስለምን፡ በ፴ ዓመቱ፡ በዮሓንስ እጅ ተጠመቀ? ዝቅ ብሎ፡ በ፳፡ ከፍ ብሎ፡ በ፵ ዓመት ያላደረገው ለምንድር ነው?*

*መልስ፡-* አዳም፡ የ፴ ዓመት ጐልማሳ ኾኖ ተፈጥሮ ሳለ፡ ራሱን፡ ለፈጣሪው የሕይወት ፈቃድ ሳይኾን፡ ለሰይጣን የሞት ትእዛዝ በማስገዛቱ፡ ከእግዚአብሔር፡ በ፵ ቀን ያገኛትን ልጅነት፡ አስወስዷት ነበርና፡ ያችን ልጅነት ለማስመለስ ሲል ነው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቤዛ ኾኖ፡ ያን ካሣ ለመክፈል፡ በ፴ ዓመቱ የተጠመቀው።

አምላክ ሲኾን፡ ወደዮሓንስ ኼዶ መጠመቁም፡ ተጠማቂው፡ ምንም ታላቅ ባለማዕርግ ቢኾን፡ ወደአጥማቂው ተራ ካህን ኼዶ መጠመቅ የሚገባው መኾኑን፡ ለእኛ፡ በአርአያነት ለማሳየትና ስለትሕትና ምሳሌ ለመኾን ነው።

*ጥያቄ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በ፴ ዓመቱ ከተጠመቀ፡ "እኛም፡ ልንጠመቅ የሚገባን፡ በዚሁ ዕድሜ ነው!" የሚሉ አሉ። ይህን ስለመሰለው አስተሳሰብ፡ ምን ትላለህ?*

*መልስ፡-* ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሰው ኾኖ ወደዚህ ዓለም የመጣው፡ ለፍጥረቱ የሰጠውን ተስፋና በነቢያት የተነገረውን ትንቢት ሊፈጽም፡ በዲያብሎስ የክፋት አገዛዝ፡ በኃጢአት ቀንበርና በሞት ፍዳ ሲማቅቅ የኖረውን የሰውን ዘር ሊያድንና ሰዎች፡ በምድር ላይ ሕይወታቸው፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓተ መንግሥት ተከትለው፡ እንዴት መኖር እንደሚገባቸው፡ እንደሚችሉም ሊያስተምር መኾኑ፡ ቀደም ብሎ በየአርእስቱ፡ በተለይም፡ *በምሥጢረ ሥጋዌ* ትምህርት ውስጥ፡ በሰጠኋችሁ ሓተታ ተብራርቶላችኋል፤ ስለዚህ፡ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ራሱ ተጠምቆ፡ ማንነቱን፡ በይፋ ከማሳወቁ ጋር፡ እኛም ተጠምቀን፡ የእግዚአብሔር ልጆች የምንኾንበትን ሥርዓት ሊመሠርት፡ እስከ፴ ዓመት ዕድሜው መቆየት እንዳስፈለገው፡ በዚህ ሓተታ፡ በሚበቃ የተገነዘባችሁት ይመስለኛል።

ታዲያ፡ ሰው የኾነው አምላክ፡ ዓላማውና ግብሩ ይህ መኾኑ ተረጋግጦ ከታወቀ፡ ዕሩቅ ብእሲ የሚባለው ሰብአዊ ፍጡር፡ የዘለዓለም ሕይወት ከሚወረስባት፡ ከእግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት፡ እስከ፴ ዓመት ዕድሜው ድረስ የሚቆይበት ምን ምክንያት ይኖራል ብላችሁ ታስባላችሁ? ለመኾኑ፡ በየአፍታዋ፡ ለሞት ከተጋለጠው ከሰብአዊው ፍጡር መካከል፡ ከቶ፡ በዕድሜው፡ እስከ፴ ዓመት ለመቆየት፡ ዋስትና ያለው ሰው፡ በምድር ላይ አለን? የለም።

# ምዕራፍ ፫፡ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት፡፡

## ምሥጢረ ጥምቀት፡፡

### የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት፡፡

---

ወይስ፡ ዕድሜው፡ ከ፴ ዓመት በታች የኾነ ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት የመግባት ዕድል ተነፍጎታል ማለት ነውን? ወይስ፡ ይህ ዕድል፡ ሊነፈገው ይገባል ማለት ነውን? አይደለም፡፡

ይህ፡ የሰይጣን ወገኖች የኾኑ፡ የክፉ ሰዎች አስተሳሰብ ሲኾን፡ እግዚአብሔር ግን፡ ለሰብአዊ ፍጡሩ፡ በዚህ ረገድ ያደረገለት ቸርነት ምን እንደኾነ፡ ቀጥዬ እነግራችኋለሁ፡፡ ይኸውም፡ ማንኛውም ሰው፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ ወደእርሱ መንግሥት ለመግባት ከፈለገ፡ ገና ከእናቱ ማሕፀን ከወጣው አራስ አንሥቶ፡ ወደዐፈርነቱ መቃብር ሊወርድ እስከተቃረበው ሽማግሌ ድረስ፡ ምንም ዓይነት የዕድሜ ወሰን እንዳይደረግበት መፍቀዱና ወደር ወደማይገኝላት፡ ወደዚችው መንግሥቱ ለመግባት፡ አንዲት ግዳጅን ብቻ ይፈጽም ዘንድ የሚጠይቅ ሥርዓትን መደንገጉ ነው፡፡

#### የሰብአዊው ፍጡር ጥምቀትና የሚያገኘው ኹለተኛ ልደት፡፡

ጥያቄ:- *ሰብአዊ ፍጡሩ፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ይችል ዘንድ፡ ፈጣሪ፡ ከታላቅ ቸርነቱ ጋር፡ ከእርሱ የጠየቀው፡ አንዲት የኾነችው ብቸኛ ግዳጅ ምንድር ናት?*

መልስ:- "ኹለተኛዋ ልደት!" ናት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቃል፡ *"እውነት፡ እውነት እልሃለሁ! ሰው፡ ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም፡፡"* የተባለችው፡ "እንደገና መወለድ!" ይህች ናት፡፡

ጥያቄ:- *"ሰው፡ ከተወለደ በኋላ፡ ወይም፡ ካደገ፡ ወይም፡ ከሸመገለ በኋላ፡ እንዴት፡ እንደገና ሊወለድ ይችላል? ኹለተኛ ወደእናቱ ማሕፀን ገብቶ፡ ይወለድ ዘንድ ይችላልን?"*

መልስ:- ይገርማችኋል! ኒቆዲሞስ የተባለው፡ ፈሪሳዊ የአይሁድ አለቃ፡ በሌሊት፡ ወደጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ፡ ልክ፡ ይህንኑ፡ አሁን፡ እናንተ ያቀረባችሁትን የመሰለ ጥያቄ፡ ለጌታ አቅርቦለት፡ መልሱን ሰጥቶታል፡፡

ጥያቄ:- *እውነት!? እንዴት! ታዲያ፡ አምላክ፡ ምን የሚል መልስን ሰጠው?*

መልስ:- አዎን! ኒቆዲሞስ፡ ይህን ጥያቄ፡ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አቀረበ፡፡ ያቀረበውም፡ *"መምህር ሆይ! እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከኾነ በቀር፡ አንተ የምታደርጋቸውን፡ እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና፡ መምህር ኾነህ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን፡"* የሚለውን የመግቢያ ቃል ካስቀደመ በኋላ ነበር፡፡

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ይኸው ኒቆዲሞስ፡ ቀደም ብሎ ላሰማው፡ ለዚህ ንግግሩ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘው መልስ፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት መግባት የሚቻለው፡ ይህን የመሰለውን እውነት፡ በሌሊት፡ በሥውር መጥቶ፡ በመናገር ብቻ ሳይኾን፡ *እንደገና ተወልዶ፡ በብርሃንና በይፋ በመመስከር* መኾኑን የሚያመለክት ግጻጅን ነው።

ጥያቄውንም፡ *"እውነት፡ እውነት እልሃለሁ! ሰው፡ ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።"* ሲል፡ አምላካችን፡ "ኹለተኛው ልደት" የተባለው ምን እንደኾነ፡ ምሥጢሩን ወዲያው ገልጾለታል፡ ትርጉሙንም ፈትቶለታል።

ጥያቄ፡- *እኹንም፡ ከውኃና ከመንፈስ መወለድ እንዴት እንደኾነ ለመረዳት፡ እንደኒቆዲሞስ፡ ለእኛም፡ ከብዶናልና፡ በበለጠ ብታብራራልን?*

መልስ፡- ለዚህ ጥያቄያችሁ፡ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለኒቆዲሞስ የተናገረው፡ እንዲህ የሚለው ቃሉ፡ በቂ ምላሽ በመኾኑ፡ እዚህ ላይ ጠቅሼላችኋለሁ።

*"ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፡ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው። 'ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል!' ስላልሁህ፡ አታድንቅ! ነፋስ፡ ወደሚወድደው ይነፍሳል፡ ድምፁንም ትሰማለህ፡ ነገር ግን፡ ከወዴት እንደመጣ፡ ወዴትም እንዲኼድ አታውቅም፡ ከመንፈስ የሚወለድም ኹሉ እንዲሁ ነው።"*

ጥያቄ፡- *"ይህ፡ እንዴት ሊኾን ይችላል?" ይህን ረቂቅ ድርጊት፡ በምን ዘዴ፡ በቀላሉ ታስረዳናለህ?*

መልስ፡- በዚህ ጥያቄያችሁ፡ አሁንም እንደገና፡ ልክ፡ ኒቆዲሞስን መስላችሁ ተገኝታችኋል። ለዚሁ ጥያቄያችሁ፡ መልስ ይኾናችሁ ዘንድ፡ ራሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመለኮታዊ አንደበቱ፡ ለኒቆዲሞስ የተናገረውን፡ እንዲህ የሚለውን፡ ያንኑ ቃሉን፡ መልስ አድርጌ፡ ይኸው፡ አቅርቤላችኋለሁ፡-

*"አንተ የእስራኤል መምህር ስትኾን፡ ይህን አታውቅምን? እውነት፡ እውነት እልሃለሁ፡ የምናውቀውን እንናገራለን፡ ያየነውንም እንመሰክራለን፡ ምስክራችንንም አትቀበሉትም። ስለምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ፡ ካላመናችሁ፡ ስለሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ፡ እንዴት ታምናላችሁ?"*

እንግዲህ፡ ይህን የመሰለውን ምሥጢር መረዳትና መቀበል የሚቻለው፡ በሃይማኖት በታነፀ መንፈሳዊ አእምሮ መኾኑን፡ ቀደም ብዬ ገልጬላችሁ ስለነበረ፡ ታስታውሱታላችሁ። እናንተም፡ ይህን የተያያዝነውን፡ የአስማጺ ምሥጢራቱን ማብራሪያ፡ በዚያ ሃይማኖታዊ መሠረትና መንፈሳዊ አቋም ኾናችሁ እንደምትሰሙኝ፡ በዚያኑ ጊዜ አረጋግጣችሁልኛል።

## ምዕራፍ ፫፡ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

### ምሥጢረ ጥምቀት።

### የሰብአዊው ፍጡር ጥምቀትና የሚያገኘው ኹለተኛ ልደት።

---

ስለዚህ፡ በዚያ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ አእምሮአችሁ ጸንታችሁ የቀጠላችሁ ከኾናችሁ፡ ይህን ረቂቅ ምሥጢር፡ ከነኺደቱና ከዋኔው፡ በቀላሉ[፳፱] ለመረዳት፡ በሃይማኖት ለመቀበልም እንደማያዳግታችሁ አምናለሁ።

ይህም ኹኖ፡ እስኪ፡ ለዚህ ጥያቄያችሁ፡ ምናልባት፡ በቀላሉ፡ አጥጋቢ መልስ ሊኾናችሁ የሚችል፡ አንድ ማስረጃን ልስጣችሁ! ይኸውም፡ በዘመናዊው ሥጋዊ ትምህርታችሁ ላይ ከቀሰማችኋቸው የማሳያ አብነቶች መካከል አንዱ የኾነውን ነው። እንደምታውቁት፡ አንድ ግዙፍ አካል፡ ዕቃ፡ ወይም ጽዋ፡ ለተመልካች ይመስላል እንጂ፡ በውስጡ ምንም ነገርን ካልያዘ፡ በልማድ፡ "ባዶ ነው፡" ይባላል።

በእርግጥ ግን፡ ባዶውን አይደለም፡ ባዶውን፡ ሊኾንም አይችልም። ለምን? እኛ ባናየውም፡ በውስጡ፡ አየር ሞልቶበት ስለሚገኝ ነው። በዚያ አካል፡ ወይም፡ ዕቃ፡ ወይም፡ ጽዋ ውስጥ፡ አንድ ሌላ ነገር አምጥተን ስንጨምርበት፡ አየሩ፡ ቦታውን ይለቅና ያ፡ አዲሱ ነገር ተተክቶ፡ ቦታውን ይይዛል ማለት ነው። ለምሳሌ፡ ጽዋውን፡ ለአብነት እንውሰድ! ጽዋው፡ ተቀምጦ ሳለ፡ ምንጊዜም፡ ባዶ አልነበረም፡ ኹልጊዜም፡ በአየር ተመልቶ ይገኝ ነበር፡ ውኃ ስንሞላበት ግን፡ አየሩ ይወጣና ውኃው ይተካል፡ የወይን ጭማቂ ልንጨምርበት ብንፈልግ ደግሞ፡ አስቀድመን፡ ውኃውን ማፍሰስ ይኖርብናል፡ እንደገና፡ በወይን ጭማቂው ቦታ፡ መርዝ እንጨምርበት ብንል፡ አስቀድመን፡ የወይን ጠጁን ካልገለበጥነው፡ መርዙን፡ ልንተካ አንችልም።

በዚሁ መልክ፡ በነፍስና በሥጋ የተሠራው የሰው አካልም፡ ባዶውን ሊኾን አይችልም፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ወይም፡ በርኩስ መንፈስ መመላት አለበት፡ ከማሕፀን ጀምሮ፡ ከፈጣሪው፡ በተፈጥሮ ከተሰጠው ንጹሓ ባሕርዩ የተነሣ፡ ሕፃኑ የሚወለደው፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ተከብቦ ነው፡ በወላጆቹ ዘንድ፡ በደም የታተመና በዘር የተላለፈ የአምልኮ ባዕድ ትሥሥርና ግንኙነት ካለ ግን፡ በርኩስ መንፈስ ቍራኝነት ይወለዳል። በጥምቀት ጊዜ፡ ይኸው ሕፃን፡ ከዚህ ቍራኝነት ተላቅቆ፡ በፍጹም ነጻነት፡ ልክ፡ በንጹሓ ባሕርይ ጸንቶ እንዳለው ሕፃን፡ የመንፈስ ቅዱስን ባሕርይና አካል፡ በምልዓት ይቀዳጃል።

• በቀዳማዊውና በዚህ፡ በዳግማዊው የውይይታችን ክፍሎች ውስጥ እንደተረዳችሁት፡ እንደምትረዱትም፡ ይህ የተጠመቀ ሕፃን፡ በዕድሜው፡ እንደየጸታው፡ ለአቅመ ሔዋን፡ ወይም፡ ለአቅመ አዳም በሚደርስበት ጊዜ፡ ምርጫው፡ በዚያው፡ የደጉ ወገን በኾነው፡ በእግዚአብሔር ጸንቶ የቀጠለ ከኾነ፡ በመንፈስ ቅዱስ እንደተመላ፡ መልካም ሕይወቱን ይቀጥላል፡ ምርጫው፡ የክፉው ወገን የኾነውን፡ ዲያብሎስን ከኾነ፡ በመንፈስ ቅዱስ ቦታ፡ ርኩስ መንፈስ ተተክቶ፡ ወደኃጢአት ኑሮ ይዘፈቃል።

### ሕፃናት፡ በ፵ እና በ፹ ቀን ስለሚጠመቁበት ኢትዮጵያዊው ሥርዓት።

*ጥያቄ፡- ሰው፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት የሚገባበት ሥርዓት የሚፈጸመው፡ በጥምቀት፡ ከውኃና ከመንፈስ ዳግመኛ ተወልዶ፡ የእግዚአብሔር ልጅ የመኾንን ጸጋ በመቀዳጀት መኾኑን አውቀናል።*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

*ለዚህ ዕድል ለመብቃት ደግሞ፡ የዕድሜ ክልል የማይወስነው ከኾነ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከትንሣኤው በኋላ፡ ደቀ መዛሙርቱን፡ "ወደዓለም ኹሉ ኺዱ! ወንጌልንም፡ ለፍጥረት ኹሉ ስበኩ!" ብሎ፡ የሐዋርያነት ተልእኳቸውን አስታውቆ በላካቸው ጊዜ፡ "ያመነ፥ የተጠመቀም ይድናል! ያላመነ ግን ይፈረድበታል!" ያለው፡ የምሥራችና የፍርድ ቃሉ፡ በተግባር ላይ የሚውለው፡ እንዴት ሊኾን ነው?*[፳፰]

*መልስ፡-* ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"ያመነ፡ የተጠመቀ ይድናል!"* የሚለውን መለኮታዊ ውሳኔውን ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው፡ ከትንሣኤው በኋላና ከዕርገቱ በፊት እንደነበረ ይታወቃል።

ይህንም፡ የምሥራቹን ለመንገር፡ ወደአሕዛብ በሚኼዱበት ጊዜ፡ ውሳኔውን፡ በእነርሱው፡ በአሕዛቡ ላይ እንዲያውሉት በማስገንዘብ መኾኑን፡ እንዲህ የሚለው ቃሉ ያስረዳል፡-*"እንግዴህ፡ ኺዱና፡ አሕዛብን ኹሉ፡ በአብ፡ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እየጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ኹሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው፡ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው!"* የሚለው መምሪያውና *"ከእነርሱ ጋር አብሮ ሣለ፡ 'ከእኔ የሰማችሁት፡ አብ የሰጠው የተስፋ ቃል እስኪፈጸም፡ ለጥቂት ቀኖች ጠብቁ!"* ማለትም፡ መንፈስ ቅዱስ በላያቸው እስኪወርድ ድረስ፡ *"ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው።"*[፳፱]

ከዚያ አስቀድሞ፡ ማለትም፡ ከመስቀል መከራው፡ ከሞቱና ከትንሣኤው በፊት ግን፡ እርሱም፡ ደቀ መዛሙርቱም፡ ዋናውና ቀዳሚው ተልእኳቸው፡ ለአሕዛብ ሳይኾን፡ በአብርሃም የግርዛት ቃል ኪዳን ምክንያት፡ ከ፰ (ስምንት) ቀን ዕድሜያቸው ጀምሮ፡ *የእስራኤል ልጆች* ተብለው፡ *እንደኢትዮጵያ ልጆች፡* የእግዚአብሔር ወገኖች የነበሩትን፡ የእስራኤልን ሕዝብ ማዳን መኾኑን ተናግሩዋል።

ይህም፡ *"አሥራ ኹለቱን ደቀ መዛሙርቱን፡ ወደእርሱ ጠርቶ፡ ...ላካቸው፤ አዘዛቸውም፡ እንዲህም አላቸው፡- 'በአሕዛብ መንገድ አትኺዱ! ወደሳምራውያንም ከተማ አትግቡ! ይልቅስ፡ የእስራኤል ቤት ወደሚኾኑ፡ ወደጠፉት በጎች ኺዱ እንጂ። ኼዳችሁም፡ "የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች!"* እና *"ንስሓ ግቡ!"* *ብላችሁ ስበኩ!'"* ደግሞም፡ ከአሕዛብ ወገን የኾነች አንዲት ሴት፡ የታመመች ልጇን ይፈውስላት ዘንድ፡ ከኋላው እየተከተለች ስትጮህ፡ *"ከእስራኤል ቤት፡ ለጠፉት በጎች በቀር፡ አልተላክሁም።"* ብሎ በተናገረው ቃሉ፡ ታውቋል።

ስለዚህ፡ *"ያመነ፡ የተጠመቀ ይድናል!"* የሚለው መለኮታዊው ውሳኔ የሚጸናው፡ አምልኮተ እግዚአብሔርን፡ ገና ባልሰሙና በማያውቁ፥ ነገር ግን፡ በዲያብሎስና በሥራዊቱ አጋንንት አማካይነት፡ አምልኮተ ጣዖትንና የተለያዩ አማልክትን በሚያመልኩ፡ በአሕዛብና በአረማውያን ላይ ብቻ መኾኑ ግልጽ ነው።[፴፩]

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት፡፡
## ምሥጢረ ጥምቀት፡፡
### ሕፃናት፡ በ፵ እና በ፹ ቀን ስለሚጠመቁበት ኢትዮጵያዊው ሥርዓት፡፡

---

ጥያቄ፡- *በዚህ መለኪታዊ የመምሪያ ቃል መሠረት፡ ማንም ሰው፡ ለመጠመቅ፡ አስቀድሞ፡ ሃይማኖቱን ተምሮና አውቆ መቀበል አለበት፡ ማለትም፡ ማመን፡ ቀዳሚ ግዴታ መኾኑን፡ መለኪታዊው የመምሪያ ቃል ያመለክታል፡፡ ታዲያ፡ በዕድሜ ታናናሽ የኾኑና ለዓቅም ያልደረሱ ሕፃናት፡ ለዚህ ግዴታ ሊበቁ ሳይችሉ፡ በተለይ፡ እንደኢትዮጵያውያን ላሉ ሕፃናት፡ ለወንዶቹ፡ በ፵ ቀናቸው፡ ለሴቶቹ ደግሞ፡ በ፹ቀን ዕድሜያቸው፡ ገና በአራስነት ዕድሜያቸው የሚፈጸመው ሥርዓተ ጥምቀት "ትክክል ነው!" ተብሎ ታምኖበት፡ ሲሠራበት የተኖረው፡ በምን መሠረት እንደኾነ፡ እዚህ ላይ ገላልጸህ ብታስረዳን?*

መልስ፡- በተለይ፡ ለኢትዮጵያውያን ሕፃናት፡ ለወንዶቹም፡ ለሴቶቹም፡ ገና በአራስነት ዕድሜያቸው፡ ሥርዓተ ጥምቀት የሚፈጸምላቸው፡ ያለበቂ ምክንያት አይደለም፡ ለዚህ ሥርዓት፡ እንደሌሎቹ ኹሉ፡ "እውነትና ትክክል ናቸው!" ተብለው የታመነባቸው፡ ሃይማኖታውያን መሠረቶች አሉት፡፡ እነዚህንም፡ እንደሚከተለው ልዘርዝርላችሁ፡-

፩ኛ፡- ወደእግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት፡ የሚያስችለውን፡ ኹለተኛውን ልደት ለማግኘት፡ ማለትም፡ በጥምቀት፡ ከውኃና ከመንፈስ ዳግመኛ ለመወለድ፡ *ሕፃን መኾን* ያስፈልጋል፡፡ *ሕፃን* ካልኾኑ፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይቻልም ማለት ነው፡፡

ይህም፡ *"እውነት እላችኋለሁ! ካልተመለሳችሁ፡ እንደሕፃናትም ካልኾናችሁ፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት ከቶ አትገቡም፡፡"* በሚለው፡ በራሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ታውጇል፡ ደግሞም፡ *"እንዲዳስሳቸው፡ ሕፃናትን፡ ወደእርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱም፡ ያመጧቸውን ገሠጿቸው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ግን፡ ይህን አይቶ ተቈጣና፡- 'ሕፃናትን ወደእኔ ይመጡ ዘንድ፡ ተዉ፥ አትከልክሏቸው! **የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እንደነዚህ ላሉት ናትና፡፡ ...እውነት እላችኋለሁ! የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ እንደሕፃን የማይቀበላት ኹሉ፡ ከቶ** አይገባባትም!' አላቸው፡፡ አቀፋቸውም፡ እጁንም ጭኖ ባረካቸው፡፡"* የሚለው የምሥራቹ ዜና፡ ይህንኑ አጽንቶታል፡፡[፳፳]

ጥያቄ፡- *እዚህ ላይ እናቋርጥህና፡ "ተመልሶ፡ ሕፃን መኾን" የሚቻለው፡ እንዴት እንደኾነ፡ ኢየይዘህ ብትገልጽልን?*

መልስ፡- "ተመልሶ፡ ሕፃን መኾን"፡ አሳቡ፡ በቊሙ፡ ወይም፡ ቃል በቃል ተወስዶ፡ በአካለ ሥጋ በማነስ፤ ወይም በዕድሜ፡ ወደኋላ በመመለስ፡ እንደገና ሕፃን መኾን ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን፡ ሰውነትን፡ በንስሓ ሥርየት አጥርቶና ለጥንተ ተፈጥሮው ንጽሓ ባሕርይ አብቅቶ፡ በቅዱ[ስ] ቍርባንም አጽድቆ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ እንዲሁም፡ ለሰው፡ ራስን እንደሕፃን፡ የዋህና ትሑት አድርጎ ማቅረብ ማለት ነው፡፡

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ስለዚህ፡ የኢትዮጵያ ሕፃናት፡ በዚህ ረገድ ብቻ ሳይኾን፡ በተወለዱ በ፵ኛ ቀናቸው፡ የኪዳን ልቦናንና የኪዳን አሪትን የግርዛት ሥርዓተ ሃይማኖት፡ ቀደም ብለው ጠብቀው የተገኙ በመኾናቸው፡ ለመጠመቅ፡ ማለትም፡ የጥምቀትን ሥርዓት ለመፈጸም የሚያበቃውን፡ የሕፃንነት መሥፈሪያ፡ ፈጽመው ያሚሉ ስለኾኑ፡ በአራስነታቸው መጠመቃቸው፡ ትክክልና ተገቢ መኾኑ በቀላሉ ይረጋገጣል።

፪ኛ፡ በአምልኮተ እግዚአብሔርና በቅዱሱ ኪዳን፡ የእግዚአብሔር ወገኖች ከኾኑ አባትና እናት የተወለዱት ኢትዮጵያውያን ሕፃናት፡ ገና ከማሕፀን ጀምረው፡ በአዳምና ሔዋን፡ የቅዱስ ጋብቻ፡ በኖኅ፡ የቀስተ ደመና፡ በመልከ ጼዴቅ፡ የኅብስተ አኰቴትና የጽዋ በረከት፡ በአብርሃም፡ የግርዛት፡ በሙሴ፡ የጽላተ ሕግ፡ በዳዊት፡ የመንበረ መንግሥት፡ በመጨረሻም፡ በድንግል ማርያምና በኢየሱስ ክርስቶስ፡ የቅዱስ ቊርባን ቃል ኪዳናት ተቀድሰው የተወለዱ ስለኾኑ፡ ወንዶቹ ሕፃናት፡ በ፵ ቀናቸው፡ ሴቶቹ ሕፃናት ደግሞ፡ በ፹ቀን ዕድሚያቸው፡ የጥምቀቱን ሥርዓት ፈጽመው፡ በዳግም ልደታቸው፡ ከቃል ኪዳን አምላካቸው፡ በመንፈስ ቅዱስ ተወልደው፡ በብሉዩ ኪዳን የኖሩበትን፡ የእግዚአብሔር ልጅነታቸውን፡ በአዲስ ኪዳኑ የምሕረት ጸጋ አጽንተውና አረጋግጠው እንዲቀጥሉ ተደርጓላቸዋል።

፫ኛ፡ ኢትዮጵያውያኑ ሕፃናት፡ ወንዶቹ፡ በ፵ ቀናቸው፡ ሴቶቹ ደግሞ፡ በ፹ቀን ዕድሚያቸው፡ የጥምቀቱን ሥርዓት የሚፈጽሙበት ምክንያት፡ ቀደም ብለው ከተጠቀሱት ጋር፡ ተጨማሪ ሃይማኖታዊ መሠረት አለው፡ ይኸውም፡ በትውፊት እየተነገረ እንደደረሰን፡ በኪዳን ልቦና፡ አዳም፡ ከተፈጠረ በኋላ፡ ወደገነት የገባው፡ *አርባ ቀን*፡ በደብር ቅዱስ ቆይቶ፡ ሔዋንም፡ ከተፈጠረች በኋላ፡ ወደገነት የገባችው፡ *ሰማንያ ቀን*፡ በደብር ቅዱስ ቆይታ ስለነበረ ነው።

፬ኛ፡- ሌላው መሠረታዊ ምክንያት ደግሞ፡ በኪዳን አሪት፡ የተወለደው ሕፃን፡ ወንድ የኾነ እንደኾነ፡ በስምንተኛው ቀን ተገርዞ፡ የአብርሃምን ቃል ኪዳን ከተቀበለ በኋላ፡ አራሲቱ እናት፡ የመታረሻዋና የመንጻቷ ወራት፡ በጠቅላላ፡ በአርባ ቀን፡ ሴት የኾነች እንደኾነ ግን፡ አራሲቱ እናት፡ የመታረሻዋና የመንጻቷ ወራት፡ በጠቅላላ፡ በሰማንያ ቀን አብቅቶ፡ ሕፃኑን/ሕፃኗን፡ ከሚቃጠል መሥዋዕት ጋር ይዛ፡ በቤተ መቅደስ፡ በእግዚአብሔር ፊት እንድታቀርብ፡ የአሪቱ ሕግ ስለሚያዝ ነው።

፭ኛ፡- በመጨረሻ፡ በኪዳን መንፈስ ቅዱስ፡ ለአማናዊው የምሕረት ቃል ኪዳን ጥላዎች ኾነው የቆዩት፡ እነዚህ ሥርዓታት፡ የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊ ጸጋ፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ ባስገኘው፡ በሥርዓተ ጥምቀት ተተክተው፡ ስለጸኑ፡ ወንዶችና ሴቶች ሕፃናት፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም የተገኘውን፡ "የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን" የጸጋ ክብር ለመቀበል የሚያበቃቸውን የምሥጢረ ጥምቀት ሥርዓት ይቀበሉ ዘንድ፡ ወደቤተ ክርስቲያን የሚገቡበት ዕድሚያቸው፡ በዚያው፡ ለወንዶቹ ሕፃናት፡ በአርባ ቀን፡ ለሴቶቹም በሰማንያ ቀን እንዲጸና ኾኗል።[፵፱]

# ምዕራፍ ፫፡ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ጥምቀት።

### ሕፃናት፡ በ፵ እና በ፹ ቀን ስለሚጠመቁበት ኢትዮጵያዊው ሥርዓት።

---

፮ኛ:- እዚህ ላይ፡ ሔዋን፡ ወደገነት የገባችው፡ ከአዳም በኋላ፡ ፵ ቀን ዘግይታ፡ በ፹ ቀኗ የመኾኑን ነገር፡ ምክንያቱን፡ እርሷ፡ ከአዳም ቀጥላ ከመፈጠሩዋ ጋር በማያያዝ፡ ይህን ምሥጢር፡ ኋላ፡ በኪዳኑ እሪት ሲሠራበት ለቆየው፡ ለቤተ መቅደሱ ሥርዓትና በመጨረሻ፡ በአዲሱ ኪዳን ለሚፈጸመው፡ ለጥምቀቱ ሥርዓት፡ ቀዳሚ አርአያና ጥላ አድርጎ ማቅረቡ፡ አግባብ ይኾናል።

፯ኛ:- አራሲቱ እናት፡ ሴቷን ከወለደች በኋላ፡ ወደቤተ መቅደስ እንድትገባበት የተወሰነው፡ የጊዜ መጠን፡ ከወንዱ ዕጥፍ፡ ሰማንያ ቀን የኾነበትን ምክንያት፡ በሌላኛው ሰውኛ ባሕርዩ፡ አክሎ ማስረዳቱም ያስኬዳል፡ ይህንም፡ እንዲህ የሚለው አስተሳሰብ አጠቃልሎ ያብራራዋል:-

"ሰውን ያህል ፍጡር ጸንሳ፡ ከዚያም፡ ለዘጠኝ ወራት ተሸክማ፡ ወልዳና አጥብታ የምታሳድገው ሴት ልጅ፡ ገና በማሕፀን ስትፈጠር አንሥቶ፡ በሥጋዊ አካሏ በኩል የሚከናወነው፡ የፈጣሪዋ ጥበባዊ ትንግርት፡ ከወንዱ ይልቅ እጅግ የረቀቀና የተወሳሰበ መኾኑ ይታወቃል፡

"ከዚህ የተነሣ፡ አራሲቱ እናት፡ የሴት ልጅ ጽንስዋን ወልዳ፡ እስከምትገላገልበት ቀን ድረስ፡ በእርግዝናዋ ወራት፡ ከመንሥዔው ጀምሮ፡ በኺደቱና በዕድገቱ ወቅት፡ የሚደርሱባት፡ የተለያዩ ኺደቶችና ክዋኔዎች፡ በውስጥ ሕዋሳቷ፡ ማለትም፡ በሥጋዊ አካሏ ላይና ውስጥ ብቻ ሳይኾን፡ በነፍሳዊ ሰብእናዋ ላይና ውስጥ ጭምር እጅግ የረቀቁና የከበዱ ተፅዕኖዎችን ስለሚያስከትሉባት፡ ኹለንተናዋን፡ በጽኑ ሊያዳክመውና ሊጎዳው እንደሚችል ግልጽ ነው፡

"ያን፡ የተዳከመና የተጎዳ፡ እንስታዊ ሰውነት፡ ጠግኖ ለመመለስ፡ ለአራሲቱ የሚያስፈልጋት የማገገሚያ ጊዜ፡ ከወንዱ ይልቅ፡ ዕጥፍ ሊኾን ተገብቶታል።"

### ስለኢትዮጵያውያን የጥምቀት ሥርዓት።

**ጥያቄ:-** *በእኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ለወንዶቹ ሕፃናት፡ በ፵ ቀን፡ ለሴቶቹ ሕፃናት ደግሞ፡ በ፹ ቀን ዕድሚያቸው፡ የጥምቀቱ ሥርዓት የሚፈጸምላቸው፡ ለምን እንደኾነ፡ ከዚሁም ጋር ስለተያየዙ አንዳንድ ነጥቦች፡ ላቀረብንልህ ጥያቄ፡ መልሱን ከሰጠኸን፡ አሁን ደግሞ፡ የእግዚአብሔር ልጅ የመኾንን ታላቅ ጸጋና ክብር የሚያቀዳጀው፡ ይኸው ምሥጢረ ጥምቀት፡ ስለሚከናወንበት ሥርዓትና ስለሚያስገኘው ሕይወት ብታብራራልን?*

**መልስ:-** ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ፡ የሚጠመቀው ሰው፡ ወንድ ቢኾን፡ ሴትም ብትኾን፡ አካለ መጠን ያደረሱ ከኾኑ፡ *"የመነ፡ የተጠመቀ ይድናል!"* በሚለው *መለኮታዊ መመሪያ መሠረት፡* በቅድሚያ፡ ስለኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትና ምግባር፡ ጠንቅቀው ማወቅ ይኖርባቸዋል።

ሕጻናት፡ ወይም፡ አካለ መጠን ያላደረሱ ከኾኑ ግን፡ ቀደም ብለው በተገለጹት ኹኔታዎች፡ ተጠምቀው፡ ከዚያ በኋላ፡ ሃይማኖቱንና ምግባሩን እንዲማሩት ይደረጋል። እነዚህ ሕፃናት፡ አድገውና ነፍስ አውቀው፡ አካለ መጠን በሚያደርሱበት ጊዜ፡ ሥርዓተ ጥምቀትን ፈጽመው፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾናቸውን እውነተኛ ዜና ሰምተው ሲቀበሉት፡ "በሃይማኖት አጸኑት!" ማለት ነውና፡ በዚህ ምርጫቸውና ውሳኔያቸው፡ *"ያመነ፡ የተጠመቀ ይድናል!"* የሚለው መለኮታዊ ቃል መፈጸሙ፡ ይረጋገጣል።

አንድ ሰብአዊ ሕፃን፡ የሥጋ ወላጆቹን አባትነትና እናትነት፡ አውቆና ተረድቶ፡ በእምነት የሚቀበለው፡ አድጎ፡ ነፍስ ካወቀ በኋላ ነው፡ ይህን እውነታ፡ በሃይማኖት ተቀብሎ እስከሚያጸድቅበት እስከዚያ ዕድሜው ድረስም፡ ከአባት አብራክ ወጥቶና በእናት ማሕፀን ተፀንሶ፡ በሥጋ አካል፡ ከእነርሱ መወለዱን፡ ጨርሶ አያውቅም፡ ወላጆቹ ግን፡ እርሱን መውለዳቸውን፡ በገሃድ ያውቃሉ፡ ስለዚህ፡ እውን የኾነውን፡ ይህን እውቀታቸውን፡ እነርሱ፡ በሃይማኖት ማረጋገጥ አያስፈልጋቸውም። የእነርሱን ወላጅነትና የእርሱን ልጅነት በሃይማኖት ተቀብሎ፡ ማጽናት ያለበት፡ እርሱ ልጃቸው ነው።

እንደዚሁ ኹሉ፡ ያ፡ አንድ ሕፃን፡ ራሱን፡ ለዓቅመ አዳምነት፡ ሴት ከኾነችም፡ ራሷን፡ ለዓቅመ ሔዋንነት ባደረሱ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር ልጅ የመኾናቸውን የምሥራች ዜና ሰምተው፡ ወይም፡ ነገሩን ተረድተው፡ እውነታውን፡ በሃይማኖት እስኪቀበሉትና በምግባር እስኪያጸኑት ድረስ፡ ከእግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ የመወለዳቸውን ምሥጢር፡ ፈጽመው አያውቁም፡ በመንፈስ ቅዱስ የወለዳቸው እግዚአብሔር ግን፡ የእነርሱን፡ በሕፃንነታቸው፡ ከእርሱ በመንፈስ ቅዱስ ያገኙትን ልደት ያውቃል፡ እነዚህ ሕፃናት፡ አካለ መጠን በሚያደርሱበት ዕድሜያቸው ጊዜ፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ዳግመኛ የመወለዳቸው ዜና ሲነገራቸው፡ ዜናውን፡ ከልባቸው ተቀብለው ሲያምኑበት፡ ቀደም ብሎ እንደተነገረው፡ *"ያመነ፡ የተጠመቀ ይድናል!"* የሚለው መለኮታዊ ቃል ተፈጸመ ማለት ነው።

ሥርዓተ ጥምቀቱ ከመጀመሩ በፊት፡ ለተጠማቂው፡ የክርስትና ስም ይሠየምለታል፡ ይህ ስም፡ ተጠማቂው፡ በመለኮታዊቷ መንግሥት፡ ለዘለዓለም ሕይወት የምታበቃው፡ የእግዚአብሔር ልጅ የመኾንን ጸጋና ክብር የተቀዳጀ መኾኑ፡ ተረጋግጦ የሚታወቅበት ስለኾነ፡ ከስሞች ኹሉ የሚበልጥ፥ ወደር የማይገኝለት መታወቂያውና መጠሪያው ይኾናል።

ማናቸውም የሚጠመቀው ሰው፡ አካለ መጠን ያደረሰ ከኾነ፡ ተምሮ የተቀበለውን ሃይማኖትና ምግባር፡ ጠብቆ እንዲኖር፡ የሚጠመቀው ሰው፡ ሕፃን ወይም አካለ መጠን ያላደረሰ ከኾነም፡ ተምሮ እንዲያውቅ ለማድረግ፡ ለወንዱ ተጠማቂ፡ "የክርስትና አባት"፡ ለሴቷ ተጠማቂም፡ "የክርስትና እናት" እንዲኖሩ ሥርዓቱ ይጠይቃል። ይህን ከባድ ኃላፊነት የሚቀበሉት፡ እነዚህ፡ ክርስትና አባት እና/ወይም ክርስትና እናት፡ ራሳቸው፡ በዚሁ፡ የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትና ምግባር፡ ጸንተው የሚኖሩ ሊኾኑ ይገባቸዋል።

# ምዕራፍ ፫፡ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::

## ምሥጢረ ጥምቀት::

### ስለኢትዮጵያውያን የጥምቀት ሥርዓት::

---

በሥርዓቱ ላይ፡ የክርስትና አባት እና/ወይም የክርስትና እናት የሚኾኑት ግለሰቦች፡ በካህኑ መሪነት፡ በቅድሚያ፡ እጃቸውን በተጠማቂው ግንባር ላይ አኑረውና ፊቱን ወደምዕራብ አዙረው፡ ተጠማቂው፡ መከተል የሚችል ከኾነ፡ ቃሉን እየተቀበለ፡ ሕፃን ከኾነ ግን፡ እነርሱ እየሰሙለት፡ *"እክህደከ ሰይጣን!"፡ "ሰይጣንን፡ ክጄሃለሁ!"* ይላሉ፡ ቀጥሎ፡ በዚያው ይዞት፡ የተጠማቂውን፡ ፊቱን ወደምሥራቅ መልሰው፡ ፫ ጊዜያት፡ *"አአምን፡ በእግዚአብሔር አብ፡ አአምን፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ አአምን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ"* ይላሉ፡ በመጨረሻ፡ "የምንጠብቀውና የምናስጠብቀው ሃይማኖትና ምግባር፡ ይህ ነው፡" ብለው፡ በመሓላ በማረጋገጥ፡ የተጠማቂውን አውራ ጣት እንደያዙ፡ የኢትዮጵያውያንን የሃይማኖትና የቃል ኪዳን ጸሎቶች፡ በእየራሳቸው፡ ወይም፡ ከአጥማቂው ካህን እየተቀበሉ፡ የክርስትና አባት፡ ወይም፡ እናት የሚኾኑት እና ተጠማቂው (ሕፃን ካልኾነ)፡ ኹለቱም ወገኖች፡ ከፍ ባለ ድምፅ ያሰማሉ::

ከዚህ በኋላ፡ ቀደም ብሎ የተጀመረው፡ የመጽሐፈ ክርስትናው የንባብ ጸሎት እንደተፈጸመ፡ ሥርዓተ ቅዳሴው ተካኺዶ፡ በማብቂያው ላይ፡ ካህኑ፡ የጥምቀቱን ውኃ፡ በመስቀል እየቀዘፈ በመባረክ፡ " *አሐዱ አብ ቅዱስ፡ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፡ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ!"* የሚለውን የሥርዓተ ቅዳሴ ኀቢይ አንቀጽ፡ እስከመጨረሻው፡ በልዑል ዜማ ያሰማል:: በዚህ ጊዜ፡ ውኃው ተለውጦ፡ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዕለተ ዓርብ፡ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ፡ አንዱ ሮማዊ ወታደር፡ ቀኝ ጎኑን፡ በጦሩ በወጋው ጊዜ፡ ወዲያው፡ ሦስቱም፡ በአንድነት ሲወርዱ የታዩትን፡ ደሙንና ውኃውን፡ የማይታየውን መንፈሱንም ይኾናል::

ይህን፡ የዕለተ ዓርቡን ኹነታ፡ የዓይን ምስክር የኾነው፡ ደቀ መዝሙሩ ዮሓንስ፡ በጻፈው የወንጌልና የመልእክቱ ቃል ላይ በአጽንዖት አመልክቶታል፡ ይኸውም፡ በአንድ ወገን፡ ከአምላካችን ጋር፡ በቀኝና በግራው የተሰቀሉት ወንጀለኞች ስላልሞቱ፡ ወታደሮቹ፡ የኹለቱንም ጭኖች እየሰበሩ ሲገድሏቸው፡ እርሱን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ግን፡ አስቀድሞ፡ ፈጽሞ እንደሞተ ስላረጋገጡ፡ ጭኑን ሳይሰብሩ፡ በጦር ብቻ ወግተው የተዉት መኾናቸው ነው፡ በሌላው ወገን ደግሞ፡ ጌታ፡ ነፍሳት ወገኖቹን ነፃ ለማውጣት፡ በነፍሱ ወደሲዖል ሲወርድ፡ በሥጋውም ሕያው መኾኑን ለማጠየቅ (ለማስረዳት)፡ በዕሩቅ ብእሲ ሬሳ ዘንድ ሊኾን የማይቻለው፡ የደሙ፡ የውኃውና የመንፈሱ ተዋሕደው የመፍሰሳቸው ነገር ነው::

አጥማቂው ካህን፡ ያን ተጠማቂ፡ "አሰግደከ/ኪ በስመ እግዚአብሔር አብ፡ አሰግደከ/ኪ በስመ እግዚአብሔር ወልድ፡ አሰግደከ/ኪ በስመ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ! ስምከ/ኪ ይኩን እከሌ/ሊት"፡ ማለትም፡ "ስምህ/ሽ፡ እከሌ/ሊት ኾኖ፡ በእግዚአብሔር አብ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስም፡ አሰግድ/ሃለሁ/ሻለሁ!" እያለ፡ በአራቱም ማዕዘነ ዓለም እያዘዋወረ ያሰግደዋል::

ከዚህ አያይዞ፡ የሥርዓቱ ጸሎት በተደረገበትና በተባረከው፡ በዚያ ውኃ ውስጥ አቁሞ፥ ወይም፡ ፫ ጊዜ ብቅ ጥልቅ እያደረገ እና/ወይም በላዩ እያፈሰሰ ያጠምቀዋል። ሲያጠምቀውም፡ ፫ ጊዜ፡ "አጠምቀከ/ኪ በስመ እግዚአብሔር አብ፥ አጠምቀከ/ኪ በስመ እግዚአብሔር ወልድ፥ አጠምቀከ/ኪ በስመ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ! ስምከ/ኪ ይኩን እከሌ/ሊት"፡ ማለትም፡ 'ስምህ/ሽ፡ እከሌ/ሊት ኹኖ፡ በእግዚአብሔር አብ፥ በእግዚአብሔር ወልድ፥ ገእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅ/ሃለሁ/ሻለሁ!" እያለ ነው።

በዚህ ጊዜ፡ ያ ተጠማቂ፡ በተፈጥሮው ካገኘውም ኾነ በዘሩ ከወረሰው የከፋት ጠንቅ፥ የዓመፅ ደዌና የክህደት ርኵሰት ታጥቦ፡ ፈጽሞ ይጠራል። ከዲያብሎስ ቁራኝነት ይላቀቃል፤ ከኃጢኣት እሥራት ይፈታል፤ ከሞት ፍርድ ነፃ ይኾናል። ለዚህ ደኅንነት፥ ለዚህ ንጽሕናና ለዚህ ነፃነት ያበቃውም፡ የጥምቀቱ ሥርዓት መሥራችና በኵር የኾነው፡ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለእኛ ለሰዎች ሲል፡ እንዲያ ተጠምቆና በመስቀል ላይ መከራን ተቀብሎ፥ ሥጋውን ቆርሶና ደሙን አፍስሶ፥ ሙቶና ተቀብሮ፥ ፫ መዓልትና ፫ ሌሊት በመቃብር አድሮ፥ መበስበስን አጥፍቶና ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ፡ ዲያብሎስን ድል ያደረገበት፥ ኃጢአትን የደመሰሰበትና ሞትን ያስወገደበት፡ ያ፡ የደሙ፥ የውኃውና የመንፈሱ ጸጋ መኾኑ ሊታወቅ ይገባል።

ከዚህ የተነሣ፡ እነሆ፡ ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት የበቃችውና ቀደም ብላ፡ ከወላጆቿ፡ ሥጋዊዉን አካል ለብሳ የተወለደችው፡ የዚያ ተጠማቂ ነፍስ፡ አሁን ደግሞ፡ ከእግዚአብሔር የመወለድን ብቅዓትን አግኝታ፡ የመጨረሻውንና ዘለዓለማዊዉን መንፈሳዊ አካል ትለብሳለች፤ አዳምና ሔዋን ያስወሰዱባትን፥ ወይም ያሳጧትን፡ ያን፡ የልጅነት ጸጋ፡ ዋጋው ሊተመን የማይቻል መለኮታዊ መሥዋዕትነት ተከፍሎላት፡ በበለጠ ክብር፡ መልሳ ትጐናጸፋለች፤ በዳግመኛው ልደት፡ የእግዚአብሔር ልጅ መኾኗን ታረጋግጣለች።

ከዚህ ቀጥሎ፡ ካህኑ፡ "ዕቀብዓከ/ኪ በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ዕቀብዓከ/ኪ በስመ እግዚአብሔር ወልድ፥ ዕቀብዓከ/ኪ በስመ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ! ስምከ/ኪ ይኩን እከሌ/ሊት"፡ ማለትም፡ "ስምህ/ሽ፡ እከሌ/ሊት ኾኖ፡ በእግዚአብሔር አብ፥ በእግዚአብሔር ወልድ፥ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስም እቀባ/ሃለሁ/ሻለሁ!" እያለ የተጠማቂውን ፴፮ ሕዋሳት፡ በቅብዓ ሜሮን ይቀባዋል፤ የእግዚአብሔር ልጅ የመኾኑ ጸጋና ክብር፡ በሹመት ታተመ፤ ዘለዓለማዊነቱ፡ በማኅተም ጸደቀ ማለት ነው።

ከዚህ በኋላ፡ ከውኃውና ከቅብዓ ሜሮኑ ጋር፡ አብሮ ጸሎት የተደረገበትንና የጥምቀቱ ውኃ በመስቀሉ ላይ ታትቶ፡ ለቡራኬ የተቀዘፈበትን፥ የእግዚአብሔር አብ፥ የእግዚአብሔር ወልድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፥ እንዲሁም፡ የኢትዮጵያዊነት፡ አንድነትና ሦስትነት ምሳሌ የኾነውን፥ ሦስቱን፡ ዓበይት የቀስተ ደመና፡ ማለትም፡ አረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ ቀለማት የያዘውን፡ የኖኅን የቃል ኪዳን ማተብ፡ "'ኢትዮጵያዊ/ት' ለሚያሰኘው፡ ለዚህ፡ ለእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ልጅነትህ/ሽ፡ ይህ ምልክት ይኹንህ/ይኹንሽ!" እያለ፡ ካህኑ፡ በተጠማቂው አንገት ላይ ያሥርለታል።

# ምዕራፍ ፫፣ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
## ምሥጢረ ጥምቀት።
### ስለኢትዮጵያውያን የጥምቀት ሥርዓት።

ምሥጢረ ጥምቀት፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ የቱን ያህል በሰውነታቸው ሠርፆና ጠልቆ፡ ሥር ሰድዶና ተወድዶ፡ በሕያውነት ተዋሕዷቸው የሚኖር መኾኑን፡ በየዓመቱ፡ በጥር ፲፩ ቀን የሚውለውን በዓለ ጥምቀት፡ የሚያከብሩበት ኹኔታ፡ በሚገባ ያስረዳል፡ ይኸውም፡ በዓለ ጥምቀት፡ "የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓል ብቻ ሳይኾን፡ እኛም፡ ከእግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ተወልደን፡ የእርሱ ልጆች የመኾንን ጸጋና ክብር የተቀዳጀንበት፡ የእየራሳችንም ዘለዓለማዊ የልደት በዓላችን ነው፡" ብለው፡ በታላቅ የደስታ ስሜትና ድምቀት ማክበራቸው ነው።

### ስለምሥጢረ ጥምቀት ማጠቃለያ።

*ጥያቄ፡- ቀደም ብለህ እንዳብራራሃቸው ምሥጢራት፡ ምሥጢረ ጥምቀትም፡ ለኢትዮጵያውያን፡ እንዲህ፡ የተለየ ትርጕምና ትሥሥር ሊኖረው የቻለው፡ ከቅዱሱ ኪዳን የተነሣ መኾኑን፡ በየበኩላችን እየተረዳነው መጥተናል፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ፡ በተጨማሪ የምትነግረን ካለ፡ ብታጠቃልልልን?*

መልስ፡- እኛ ኢትዮጵያውያን፡ እንደሌሎቹ ምሥጢራት ኹሉ፡ ከዚህ ከምሥጢረ ጥምቀት ጋር፡ እንዲህ፡ በጠበቀ መልክ የተሣሠርነው ያለምክንያት አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በፍጹም ትዕግሥት፡ በተቀበላቸው መከራዎቹና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ፡ ሙቶና ተቀብሮ፡ በሦስተኛው ቀን በመነሣቱም፡ ሰይጣንንና ኃጢአትን፡ ሞትንና ሙስና መቃብርን (በመቃብር መበስበስን)፡ እነዚህን ኹሉ፡ የዘር ጠላቶቻችን የኾኑትን፡ ታላላቅና ረቂቃን የክፋት ኃይላት፡ ድል አድርጎ፡ ዘለዓለማዊ የኾነውን፡ አምላካዊ ጸጋ፡ ለእያንዳንዳችን አስገኘልን። ይህም፡ በጸሎት በተባረከው ውኃና በመንፈስ ቅዱስ በተጠመቅን ጊዜ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" የመኾንን ክብር፡ በተቀዳጀንበት፡ በክርስትና ልደት፡ ያገኘነው ጸጋ ነው። እንዲህ ከኾነ፡ እኛ፡ ይህን መሳይ ጸጋ፡ ያለአንዳች ድካምና ዋጋ ወይም መብት፡ እንዲሁ፡ በልግሥና ስጦታ ብቻ ለመቀዳጀት የቻልነው፡ ከእርሱ፡ እንዲያው በቸርነት ባገኘነው ቃል ኪዳንና እርሱ፡ ስለእኛ ቤዛ ኾኖ በከፈለልን መሥዋዕትነት መኾኑን፡ "እናንተም፡ በሚገባ ተረድታችሁታል፡" ብዬ አምናለሁ።

በዚህ ምሥጢረ ጥምቀት ምክንያት፡ ለእኛም፡ ኹለት ልደቶች እንዳሉን አውቃችኋል። "የመጀመሪያው ልደት"፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው!"* እንዳለው፡ ከአባት አብራክ ወጥተንና በእናት ማሕፀን ተጸንሰን፡ በሥጋ አካል የተወለድነው ልደት ነው።

አንድ አምላክና ፈጣሪ በኾነው፡ በእግዚአብሔር የማያምኑ አረማውያንና አሕዛብ፥ ሥጋውያንና ዓለማውያን እንደሚያስቡት፡ በምድር ላይ የምንኖረው፡ በዚህ ሰውነታችን ብቻ ቢኾን ኖሮ፥ በምንሞትበት ጊዜ፡ እንደእነርሱ አስተሳሰብ፡ ወደአልቦነት፡ ማለትም፡ ወደአለመኖር ጥፋት ተለውጠን በቀረን ነበር።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር: ማነው?

ወይም: እንደእኛ እምነት: ነፍሳችን: በምድር ላይ የምትኖረው: በዚህ ግዙፍ ሥጋዊ ልደት ብቻ ቢኾን ኖሮ: ስንሞት: በለበስነው: የኃጢአት ማኅደር፥ ሚችና በሰባሽ በኾነው: በዚሁ የሥጋ አካላችን ምክንያት: ነፍሳችን: መጀመሪያ: በሲዖል፥ በመጨረሻም: በዘለዓለም ሞት: ማለትም: ለሰይጣንና ለሠራዊቱ በተዘጋጀው: "ገሃነመ እሳት" ስትሠቃይ በኖረች ነበር።

ነገር ግን: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: *"ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው!"* ብሎ አከታትሎ እንደተናገረው: በጥምቀት: ከእግዚአብሔር የተወለድነው: የመንፈስ ቅዱስ ልደት አለ፤ ይህም: "ኹለተኛው ልደት" ነው። በዚህ ልደት: ከእግዚአብሔር: መንፈሳዊዉን ልደት ተወልደን: በኢየሱስ ክርስቶስ ድል አድራጊነት ያገኘነውን: የማይሞተውንና የማይበሰብሰውን: አዲሱን የመንፈስ ቅዱስን አካል ስለለበስን: በዚህ ዓለም: በሕይወተ ሥጋ እያለንም እንኳ: ነፍሳችንንና ሥጋችንን: በንስሓና በሥጋ ወደሙ እያጸደቅን: በፊተኛው የመንፈስ ትንሣኤ: "ሕያዋን" ኾነን እንኖራለን እንጂ: አንሞትም፤ ሥጋችን: ከሕያውቷ ነፍሳችን: በሞተ ሥጋ ቢለይም: በስብሶ አይቀርም።

እኛ ኢትዮጵያውያን: ወንዶቹም፥ ሴቶቹም: በዚህ ዓለም: ገዝፈን እንደምንታይበትና እየተንቀሳቀስን እንደምንገኝበት: እንደመጀመሪያው የሥጋ ልደታችን ኹሉ: በዚሁ ዓለም: በረቂቅ ተወልደንበትና በመንፈስ (በሃይማኖት) እየኖርንበት ላለነው: ክርስቲያናዊ ሕይወታችን የበቃንበት: ኹለተኛው፡ የመንፈስ ልደት: እንግዲህ: ይህ ነው። በዚህ: በኹለተኛው ልደት: እንዲህ ተወልደን: አዲሱን መንፈሳዊ አካል የለበስን ባንኾን ኖሮ: በመጀመሪያው: የሥጋ ልደት ብቻ: ወደእግዚአብሔር መንግሥት መግባት ባልቻልንም ነበር። *"ሥጋና ደም: የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም!"* ተብሏልና። ለዚህም ኹሉ መሠረቱ: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ለኒቆዲሞስ: *"እውነት፥ እውነት እልሃለሁ! ሰው: ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር: የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም።"* መልሶም: *"እውነት፥ እውነት እልሃለሁ! ሰው: ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር: ወደእግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይችልም።"* ብሎ የተናገረው ቃሉ መኾኑን አውቃችኋል።

የአራሶቹ ሕፃናት ሕይወት የሚያሠጋ ኾኖ በመገኘቱ: ከዚህ ባጠረ: የቀን ዕድሜያቸው ከሚጠመቁት በቀር: እኛ የኢትዮጵያ ልጆች: ወንዶቹ: በ፵ ቀን፥ ሴቶቹ ደግሞ: በ፹ ቀን ዕድሜያችን ተጠምቀናል፤ በዚህም የክርስትና ጥምቀት: ኹለተኛውን የመንፈስ ልደት ተወልደናል። እንዲህ: በመንፈስ ቅዱስ በተወለድንበት: በዚህ: በኹለተኛው ልደት: የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ልጆች ኾነናል። ይህን ልጅነት ለማግኘት: በሕፃንነታችን የተጠመቅንበት ምክንያት: ቀደም ብዬ እንዳብራራሁላችሁ: አባቶቻችንና እናቶቻችን: ስለዚህ ሥርዓት አፈጻጸም: ከጥንት ጀምረው: በኪዳነ ልቦና፥ ቀጥሎ: በኪዳነ ኦሪት፥ በመጨረሻ: በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ: ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን መመሪያ ተከትለውና በሥራ ላይ አውለው በመኖራቸው መኾኑን ተገንዝባችሁታል።

# ምዕራፍ ፫፡ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ጥምቀት።

### ስለምሥጢረ ጥምቀት ማጠቃለያ።

ይኸውም፡ እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ፡ በኪዳን ልቦና፡ በአዳምና ሔዋን መሥርቶት፡ በኖኅ አማካይነት፡ መልከ ጼዴቅ የተረከበውና ከዚያ፡ በእርሱ ቡራኬ፡ ለአብርሃም የተላለፈው የቃል ኪዳን ሐረግ፡ እነሆ፡ የ፰ ቀን ዕድሜ ባለው አራስ ሕፃን ላይ፡ በግርዛት ምልክትነት በሚፈጸመው ሥርዓት የተወጠነው ነው፡ ይህም የግርዛት ቃል ኪዳን ሥርዓት፡ በእኛ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ከአብርሃምም በፊት፡ ጠብቀነው የኖርን ሲኾን፡ እስከዛሬና ዛሬም ድረስ እነሆ፡ ተከብሮና በሥራ ላይ ውሎ ይገኛል፡ እዚህ ላይ፡ በማስተዋል ተመልከቱት! ለአብርሃም የተሰጠው፡ ያ፡ ቃል ኪዳን፡ ለዚያ፡ የ፰ ቀን አራስ የሚፈጸምለት፡ ሕፃኑ፡ በዚያ ጨቅላ ዕድሜው፡ ቃል ኪዳኑን አውቆትና አምኖበት የሚቀበለው ኾኖ አይደለም፡ ነገር ግን፡ ያ ሕፃን፡ በተፈጥሮው፡ ከእግዚአብሔር ባገኘው ንጹሓ ጠባይ፡ አብርሃም፡ ከጽኑ የሃይማኖት ፈተና በኋላ፡ በቃል ኪዳን ለተቀበለው መለኮታዊ በረከት፡ የሚያበቃው ስለኾነ ብቻ ነው።

ቀጥሎ ያለው፡ በኪዳን ኦሪት የተጠናከረው ሥርዓት ሲኾን፡ ሙሴ፡ ከእግዚአብሔር በተቀበለው፡ በዚህ ሥርዓት መሠረት፡ ወላጆች፡ ወንዱን ሕፃን ልጃቸውን፡ በ፵ ቀኑ፡ ሴቷን ሕፃን ልጃቸውንም፡ በ፹ ቀኗ፡ ከታዘዘው መሥዋዕትና ቊርባን ጋር ይዘው፡ ወደቤተ መቅደስ ያገቧቸው፡ በእግዚአብሔርም ፊት ያቀርቧቸው ነበር። የቀደሙት ኢትዮጵያውያን አባቶቻችንና እናቶቻችን፡ ይህን ሥርዓት ሲፈጽሙት ኖረዋል።

በመጨረሻ፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በኪዳን መንፈስ ቅዱስ፡ ጥንታዊውን ኪዳን፡ በአዲስ ኪዳን በማደስ፡ ሥርዓተ ጥምቀትን ራሱ ፈጽሞና መሥርቶ፡ እኛም እንድንፈጽም ባዘዘ ጊዜ፡ እነሆ፡ ኢትዮጵያውያን ሕፃናት፡ ገና በአራስነታቸው፡ በክርስትና ጥምቀት፡ ኹለተኛውን የመንፈስ ልደት ተወልደው፡ ለዘለዓለም፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ክብር፡ በምሕረቱ ቃል ኪዳን እንዲቀዳጁ አደረገ።

እግዚአብሔር፡ እርሱን፡ በእውነትና በመንፈስ ሲያመልኩት ይኖሩ ከነበሩት ኢትዮጵያውያን በኋላ፡ ለእሥራኤልም፡ በኪዳን ልቡና፡ ለአብርሃም፡ በኪዳን ኦሪት ደግሞ፡ ለሙሴ፡ በሰጣቸው ሥርዓቶች፡ ሕፃናት፡ ገና በአራስነት ዕድሜያቸው፡ ከእግዚአብሔር ፊት እየቀረቡ፡ የቃል ኪዳኖቹን በረከት እንዲቀበሉ፡ በብሉዩ ዘመን፡ ፈቃዱ እንደነበረ ኹሉ፡ ኋላም፡ በአዲሱ ዘመን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በተቀዳጀነው ጸጋ፡ ይህንኑ ቸርነቱን አብዝቶ አፈሰሰልን።

በብሉዩ ዘመንም ኾነ፡ በአዲሱ ኪዳን ዘመን፡ ለእግዚአብሔር ጸጋና በረከት፥ ይልቁንም፡ ለእግዚአብሔር ልጅነትና ለመንግሥቱ ወራሽነት የሚያበቃው መሥፈርት፡ የእውቀት፡ ወይም፡ የዕድሜ ልኅቀት (በእውቀት፡ ወይም፡ በዕድሜ መላቅ) ሳይኾን፡ እንዲያውም፡ የእነዚያ ተቃራኒ የኾነው፡ ሕፃንነት፡ ወይም፡ ራስን፡ ለሕፃንነት ባሕርይ ማብቃት መኾኑን፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተናገራቸውና ቀደም ብለው ከተጠቀሱት ቃላት ተረድታችሁታል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

በመጀመሪያው፡ የሥጋ ልደታችን ጊዜ፡ ከሥጋ ወላጆቻችን ስንወለድ፡ አንዳች የምናውቀው እንዳልነበረ፥ ወይም፡ ዛሬ ልናስታውሰው የምንችለው፡ አንዳችም ነገር እንደሌለ ኹሉ፡ በዚያ፡ በአራስነት ዕድሜያችን፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ ቅዱስ የተወለድንበትንም፡ ኹለተኛውን ልደት፡ እንዲሁ፡ በዚያ፡ የሕፃንነት ጊዜአችን፡ ልናውቀው፡ ወይም፡ ዛሬ፡ ልናስታውሰው የምንችለው፡ አንዳችም ነገር ከቶ የለም። ስለማይታየውና ረቂቅ ስለኾነው፡ መንፈሳዊው ልደት ቀርቶ፡ ስለሚታየውና ገዝፎ ስለሚኾነው፡ ስለሥጋዊው ልደት እንኳ፡ ከእነርሱ፡ በሥጋ መወለዳችንን፡ አረጋግጠው የሚያውቁትና ለእኛም የነገሩን ወላጆቻችን እና/ወይም በወቅቱ ተገኝተው፡ መወለዳችንን ያዩ፡ የዓይን ምስክሮች ብቻ ናቸው።

ነገር ግን፡ ይህ፡ የወላጆቻችን የሥጋ ወላጅነትና የእኛ የሥጋ ልጅነት፡ በእኛ ዘንድ እውን ሊኾን የቻለው፡ እኛ፡ ነፍስ እያወቅን በኼድን መጠን፡ ይህንኑ፡ ከእነርሱ የተረዳነውን፡ የእነርሱን ወላጅነትና የእኛን ልጅነት እያረጋገጥን ስላደግንና ራሳችን በእምነት ስለተቀበልነው እንጂ፡ በእየራሳችን ስንወለድ፡ መወለዳችንን፡ ራሳችን አይተን፡ ወይም አውቀን ያረጋገጥነው ነገር ኖሮ አይደለም።

ከእግዚአብሔር የተወለድንበትም መንፈሳዊ ልደት፡ እንዲሁ ነው። ልዩነቱ፡ መንፈሳዊው ልደት፡ እንደሥጋዊው ልደት አለመታየቱና ኅልዮ ቢታይም፡ በጥምቀቱ ውኃ ብቻ መኾኑ ነው። በሥጋ ከእነርሱ የተወለድን መኾናችንን በእርግጥ የሚያውቁትና የሚመሰክሩት፡ የሥጋ ወላጆቻችንና በጊዜው በቦታው የነበሩ ሰዎች ብቻ እንደመኾናቸው፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ከእርሱ የተወለድን መኾናችንንም የሚያውቀው፡ የመንፈስ አባታችን የኾነው፡ እርሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እዚህ ላይ፡ የእግዚአብሔር ወልድ እናት፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ ባገኘነው ጸጋ ምክንያት፡ ለእኛም፡ የመንፈስ እናታችን መኾኗን፥ ከዚህ የተነሣም፡ እንደምድራውያኑና ጊዜያውያኑ የሥጋ ወላጆቻችን ኹሉ፡ ሰማያውያንና ዘለዓለማውያን የመንፈስ ወላጆችም እንዳሉን አትዘንጉ!

በግዙፉ ውኃ ተጠምቀንና በረቂቁ ቅዱስ መንፈስ፡ ከእግዚአብሔር ተወልደን፡ የእግዚአብሔር ልጆች መኾናችንን፥ ደግሞም፡ ለሥጋዊው ልደታችን መታወቂያ እንዲኾነን፡ ወላጆቻችን፡ የዓለም ስም እንዳወጡልን ኹሉ፡ ለዚህም መንፈሳዊ ልደታችን፡ መታወቂያ እንዲኾነን የተሰጠን ልዩ የክርስትና ስም፡ ማን መኾኑን፡ ጨምረው የነገሩን፡ እነዚያው የሥጋ ወላጆቻችንና የክርስትና ባላደራዎቻችን፥ እንዲሁም፡ የእግዚአብሔር ተጠሪዎች የኾኑት ካህናት ብቻ ናቸው እንጂ፡ እኛ፡ በዚያን፡ በጥምቀታችን ጊዜ፡ የምናውቀው ነገር ኖሮ አይደለም።

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::
## ምሥጢረ ጥምቀት::
### ስለምሥጢረ ጥምቀት ማጠቃለያ::

ነገር ግን: እያንዳንዳችን: በአካል እያደግን፥ በአእምሮ እየጐለመስንና በመንፈስ እየጠነከርን በኼድን መጠን: ይህንኑ: እነርሱ የነገሩንን የጥምቀታችንን ዜና: በበለጠ እየተረዳንና እየተገነዘብን ኼደን: በመጨረሻ: አምነን ስለተቀበልነው: እነሆ: ይህ: የእግዚአብሔር ልጅነታችን: በእምነታችን ተረጋገጠ፥ ጸደቀ፡ እውነት ኾነ ማለት ነው:: በዚያን ጊዜ ነው: *"የመነ: የተጠመቀ ይድናል!"* ያለው: ያ: የመድኃኒታችን: የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል: በእኛም ዘንድ ሳይቀር: "ተፈጸመ!" ሊባል የሚቻለው::

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ይህን: *"የመነ፥ የተጠመቀ ይድናል!"* የሚለውን መመሪያ የሰጠው: የአዲሱ ኪዳን "የምሥራች ቃል" እንዲሰበክላቸው ላዘዘላቸው: የእግዚአብሔርን አምልኮ ላላወቁት አረማውያንና አሕዛብ እንጂ: ከአዳምና ሔዋን ዘመን አንሥቶ: ከእግዚአብሔር ጋር በቅዱሱ ኪዳን ተሣሥረንና በስምንተኛ ቀን ግርዛት ታትመን ለኖርን: ለእኛ: ለቃል ኪዳን ወገኖቹ አለመኾኑን: ቀደም ብላችሁ ተረድታችሁታል::

እኛ: ኢትዮጵያውያንማ: በሕፃንነታችን: ከመገረዛችንና ከመጠመቃችን እንኳ በፊት: በሥጋ ወላጆቻችን አማካይነት: ከማሕፀን ጀምሮ: በኪዳኑ ልቡና ተመሥርቶ፡ ወደኪዳኑ አሪት አልፎ፥ ለኪዳኑ መንፈስ ቅዱስ የበቃውን: የቅዱሱን ኪዳን ሃይማኖት: በሥጋም፥ በነፍስም፡ በመንፈስም ተወልደንበታል፥ ታትመንበታል፥ አድገንበታል፥ ኖረንበታል፡ ዛሬስ: ይኸው: እየኖርንበት አይደለምን? አዎን! ገና: በ፰ና በ፹ ቀናችን: ምኑንም ሳናውቀው: የተጠመቅነው: ቀደም ብሎ እንደተብራራው: በዚሁ ምክንያትክ ነው::

እንግዴህ: እያንዳንዳችን: በሕፃንነታችን በተቀበልነው የክርስትና ጥምቀት: ከእግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ተወልደን: የእርሱ ልጆች ለመኾን የበቃንበት ምሥጢር: ሐተታው በዚህ ይጠቃለላል::

እኔ: ዛሬ: በኢትዮጵያዊነቴ: በዚህ ዓለም: በሕይወተ ሥጋ: እየኖርሁት ያለውን: ይህን የተቀዳጀሁትን ክብር: በመንፈሳዊው አእምሮዬ ሳስበውና በዓይነ ሕሊናዬ ስመለከተው: የሚሰማኝን ደስታ፥ ደግሞም: ይህንኑ: የሥጋና የነፍስ ዘለዓለማዊ የክብር ዘውድን ላቀዳጀኝ: ቸር ፈጣሪዬ የማቀርበውን የባለውለተኛነት ምስጋና: በቃላት ልገልጸው ያዳግተኛል:: እናንተም: በዚሁ የሃይማኖታችሁ እውቀት እያደጋችሁና እየደረጃችሁ በኼዳችሁ መጠን: ይህን የመሰለው ስሜት: በበለጠ እያደረባችሁ እንደሚኼድ አምናለሁ::

## ምሥጢረ ቍርባን::

**ጥያቄ:-** *ይገርማል! እኛም: በውስጣችን እየተነሣሣ ያለው ስሜት: ይኸው: ያንተውን የመሰለ ኾኖ እያገኘነው ነንና: በመጨረሻ በተናገርከው ቃል እንደነቃለን:: ስለዚህ: የተያያዝነውን የእውቀት ፍለጋ ውይይታችንን: ከግብ ለማድረስ እንበቃ ዘንድ: ወደሚቀጥለው ምሥጢር እንሸጋገርና: እስኪ: ስለምሥጢረ ቍርባን አስረዳን?*

## ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
### "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር: ማነው?

---

መልስ:- ከንጹሕ የስንዴ እህል: በንጽሕና ተፈጭቶ፥ ተለውሶና ተዘጋጅቶ: በዓሕል የቀረበውን ኅብስት፥ ደግሞ: ከንጹሕ የወይን ፍሬ: በንጽሕና ተለቅሞ: ታሽቶና ተጣርቶ: በጽዋ የቀረበውን ጭማቂ: ካህኑ: ኹለቱንም መባዖች: በቅዳሴው ጸሎት ሲባርካቸው: ኅብስቱ ተለውጦ: *ሥጋ መለኮት:* ወይኑ ተለውጦ: *ደመ መለኮት* የሚኾንበት ሥርዓት: *ምሥጢረ ቊርባን* ይባላል::

የዚህም መሠረቱ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ብዕለተ ዓርብ: በመስቀል ላይ: ለዓለሙ: የመጨረሻው የፋሲካ በግ ኾኖ በመታረድ: ሥጋውን ከመቊረሱና ዘለዓለማዊው ቤዛ ኾኖ: ደሙን ከማፍሰሱ በፊት በነበረችው የሐሙስ ምሽት: ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በቤተ አልዓዛር ተቀምጦ: መሥዋዕተ ኦሪትን በሻረበት፥ የአዲስ ኪዳንንም መሥዋዕተ ምሕረት በሾመበት: የፋሲካ ገቢታ ጊዜ: የሠራልን ሥርዓት ነው::

በዚያ ሥርዓት: ጌታችን: የቀረበለትን ኅብስት፥ የተቀዳለትንም የወይን ጽዋ: አንሥቶ: "ይህ ኅብስት: ሥጋዬ ይኾን ዘንድ፥ ይህም ወይን: ደሜ ይኾን ዘንድ: የእኔ ፈቃድ እንደኾነ: የአንተም ፈቃድ ይኹን!" ለማለት: "*ወደሰማይ ወደአባቱ አየ!*" በዚህ አድራጎቱም: "*እኔና አብ አንድ ነን*" ባለው ቃሉ መሠረት: የአብ ፈቃድ: የእርሱ ፈቃድ መኾኑን አረጋገጠ፤ "*አመሰገነ! ባረከ!*" በሚለው ቃሉም: ጌታ: ኅብስቱን: ወደሥጋ መለኮትነት፥ ወይኑንም: ወደደመ መለኮትነት እንዲለወጥ ማድረጉን ያመለክተናል:: ኅብስቱን: ፈትቶ (ዛሬ: ካህኑ: በቅዳሴ ጊዜ: ከታች ሳይለየው: ከላይ ብቻ በጣቱ እየወጋ እንደሚለየው) እና ፲፫ ቦታ ቆርሶ: ፩ዱን: ለራሱ፥ ፲፪ቱንም: ለ፲፪ቱ ሐዋርያት አቀበላቸው፤ ይህም: አይሁድ: በማግሥቱ ይዘው: ለአረማውያን አሳልፈው ከሰጡት በኋላ የሚቀበለው: "የ፲፫ቱ ሕማማተ መስቀል ምሳሌ ነው!" ተብሎ ተተርጉሟል::

ደሙንም: በመጀመሪያ: እርሱ ከቀመሰበት: ከአንዱ ጽዋ: እነርሱም: ኹላቸው: በተራ እየተቀበሉ እንዲቀምሱ ማድረጉ: ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም ይኖሩበት ዘንድ የመሠረተላቸውን የሕይወት አንድነት ብቻ ሳይኾን: የመከራውና የክብሩም ተካፋዮች መኾናቸውን ጭምር ለማመልከት መኾኑ:[፵፱]
የ"ጽዋ"ን ትርጓሜ ለተረዳ: ለማንም አስተዋይ ተመልካች ግልጽ ነው::

ዛሬ: ቀሳውስት: ሕዝቡን ከማቁረባቸው በፊት: አስቀድመው: ራሳቸው የሚቆርቡት፤ ደግሞም: "ነገ: አይሁድ: በመስቀል ላይ በጦርና በችንካር ወግተው የሚፈትቱት ሥጋዬና የሚያፈስሱት ደሜ: ይህ ነው፤ ንሡ፥ ብሉት! ጠጡት!" ብሎ: ጌታ: ለሐዋርያት: የኅብስቱን ቊራሽና የጽዋውን ወይን እንዳቀበላቸው ኹሉ: እነርሱም: ለምእመናን: "ራሳችሁን: ለክፉት መንፈስ በማስገዛት: የሠራችሁትን ኃጢአት ያስተሰርይላችሁ ዘንድ፥ እየራሳችሁ ላመጣችሁት: ለነፍስና ለሥጋ ደዌያችሁም: መድኃኒት ኾኖ ይፈውሳችሁ ዘንድ፥ በኃጢአታችሁ ምክንያት ከተዳረጋችሁበት የሞት ፍዳም ድናችሁ: የዘለዓለምን ሕይወት ትወርሱበት ዘንድ: ይህን: የጌታን: ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ተቀበሉ!" ብለው የሚያቆርቧቸው: ይህ: የጌታ ሥርዓት: አብነት ኾኗቸው ነው::

## ምዕራፍ ፫፣ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት፡፡
## ምሥጢረ ቊርባን፡፡

ከዚህ ጋር፡ ጌታ፡ ይህን፡ የአዲስ ኪዳኑን ሥርዓት የሰጣቸው፡ የብሉዩን የፋሲካ ሥርዓት ከፈጸመ በኋላ መኾኑ፡ ታናሽና ጊዜያዊ የነበረችው፡ መሥዋዕተ ኦሪት አልፋ፡ ታላቅና ዘለዓለማዊ የኾነው፡ መሥዋዕተ ምሕረት፡ በእርሱ ሥጋና ደም መተካቱን ለማብሠር መኾኑን፡ በማስተዋል ተመልከቱት!

ቅዱሱ ቊርባን ፡ በስንዴ ኅብስትና በወይን ጭማቂ ስለመኾኑ፡፡

ጥያቄ፡- *አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የአዲስ ኪዳኑን መሥዋዕት፡ ቀድሞ፡ በኦሪቱ ሥርዓት፡ በእንስሳትና በአዕዋፍ ደም ይቀርብ ከነበረው፡ የተለየ እንዲኾን በማድረግ፡ እንዲህ፡ በስንዴና በወይን ብቻ እንዲፈጸም፡ ለምን እንደፈቀደ ልትገልጹልን ይቻልሃል?*

መልስ፡- "ይቻልሃል?" ብላችሁ ለምን ትጠይቃላችሁ? በመንፈስ ቅዱስ ሕይወት ውስጥ የማይቻል፡ ምንም ነገር የለም፣ እውነተኛ መልስ የሌለው ጥያቄም ከቶ የለምና፡ ማናቸውንም ጥያቄ ከማቅረብ ወደኋላ እንዳትሉ፡ ቀደም አድርጌኮ ነግሬአችኋለሁ፡፡ በዚህ መሠረት፡ የአዲስ ኪዳኑ ቅዱስ ቊርባን፡ በስንዴ ኅብስትና በወይን ጭማቂ እንዲኾን፡ የአምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃዱ ስለኾነበት ምክንያት አሁን ላቀረባችሁልኝ ጥያቄ፡ የምሰጣችሁ መልስ፡ ከዚህ የሚከተለው ይኾናል፡፡

እግዚአብሔር፡ ፍቅሩና ቸርነቱ፥ ቤዛነቱም፡ ለሰው ብቻ ሳይኾን፡ "እርባዕቱ እንስሳ" ተብለው፡ በሰው፥ በአንበሳ፥ በላምና በንሥር ተመስለው፡ መንበረ ጸባዖቱን ለተሸከሙት ፍጥረቱ ኹሉ ጭምር መኾኑን፡ በዚህ ምሥጢር አማካይነት፡ በይፋ አሳውቋል፡፡ ይኸውም፡ ራሱን፡ ለመሥዋዕትነት ያቀረበው፡ ሰው በኾነበት ሥጋውና ደሙ ሲኾን፡ ይህ መሥዋዕትነቱ፡ በዚሁ፡ ሕያው ነፍስ ካለው ፍጡር በተገኘ የሥጋና የደም ቊርባን እንዲቀጥል ማድረግ ሲችል፡ በቀላሉ፡ ከእርሻ በተመረተ እፍኝ እህልና ከተክል ሐረግ በተለቀመ ጥቂት ፍሬ እንዲኾን ማድረጉ፡ ከእርሱ መሥዋዕትነት በፊት፡ ሥጋቸውንና ደማቸውን ብቻ ሳይኾን፡ ሕይወታቸውን ሳይቀር፡ በተለያየ መልክ፡ ቤዛ አድርገው ይከፍሉ የነበሩትን፡ ሰዎችንና እንስሶችን፥ ወፎችንና አውሬዎችን፡ ከመገደልና ከመታረድ ሊያድን መኾኑ አይጠረጠርም፡፡

ደግሞ፡ ሰው ኹሉ፡ ኃጢአቱን ለማስተሰረይ የሚያስፈልገውን የእንስሳ ወይም የወፍ መሥዋዕትና ቊርባን ለማቅረብ፡ በተለይ፡ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኝ፡ ወይም ችግረኛ ለኾነ ግለሰብ፡ እጅግ ይከብድበት የነበረውን ሸክም፡ ይህ፡ የአዲስ ኪዳኑ፡ የኅብስትና የወይን መሥዋዕትና ቊርባን፡ የቱን ያህል እንዳቀለለለት፥ ጨርሶም እንዳነሣለት እንመለከታለን፡፡ በተለይም፡ አንዲቱ ኅብስትና የአንዲት ጽዋ ወይን፡ ለአያሌ ቆራቢዎች እንዲበቃ ማድረግ የሚቻል በመኾኑ፡ በዚህ ረገድ፡ የእግዚአብሔርን ቸርነት ተመልክቶ ማድነቁ፡ ለማንም አያዳግትም፡፡

## ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
### “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ቀጥሎ፡ መብል መጠጥ፡ ሰዎችን የሚያቀራርብና የሚያፋቅር ከመኾኑ ጋር፡ በግለሰብም ደረጃ፡ ሰውነትን ይዋሃዳል:: እግዚአብሔርም፡ ሰው በመኾኑ፡ ከፍጡሩ ከሰው ጋር በመዛመድ ብቻ ሳይወሰን፡ በመለኮትነቱ በተዋሐደው ኅብስትና ወይን፡ ተበልቶና ተጠጥቶ፡ እያንዳንዱን ሰው፡ በሥጋና በደም ጭምር፡ ሊዋሃድ ፈቃዱ ኾነ!

ከዚያም፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ የኃጢአትና የደዌ ምንጭ፡ መብልና መጠጥ በመኾኑ፡ በዚያ መነሻ የመጣውን ኃጢአትና ደዌ፡ በዚያው በመነሻው፡ በመብልና በመጠጥ ሊያጠፋ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ የኃጢአት ማስተስረያውን መሥዋዕትና የደዌ መፈወሻውን መድኃኒት፡ በመብልና በመጠጥ አደረገው::

በመጨረሻ፡ “እውነተኛው ንጉሥ” በሚል ስም፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ኾኖ ተገልጾ የነበረው መልከ ጼዴቅ፡ በካህንነቱ፡ ለእግዚአብሔር ያቀርበው የነበረው የምስጋና መሥዋዕትና የበረከት ቍርባን፡ በኅብስትና በወይን ስለነበረ፡ አማናዊው መልከ ጼዴቅ፡ እርሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑን፥ ምሳሌነቱ፥ ትንቢቱና ተስፋውም ኹሉ፡ በእርሱ አማናዊነት መፈጸሙን ለማረጋገጥ፡ የቅዱስ ሥጋውና የክቡር ደሙ፡ አማናዊ መገለጫ፡ ያው፡ የስንዴው ኅብስትና የወይኑ ጭማቂ እንዲኾን አደረገ::

ስለኅብስቱና ወይኑ፡ ወደመለኮት ሥጋነትና ደምነት መለወጥ::

*ጥያቄ፡- ኅብስቱ ተለውጦ፡ ሥጋ መለኮት፥ ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት የሚኾንበትን ምሥጢር ብታብራራልን?*

መልስ፡- በጥምቀት ጊዜ፡ ካህኑ፡ በሥርዓተ ቅዳሴው ጸሎት፡ “አሐዱ አብ ቅዱስ፥ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፥ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ!” እያለ ሲባርከው፡ ውኃው፡ በመንፈስ ቅዱስ ተለውጦ፡ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀል ላይ እያለ፡ በጦር ከተወጋው ጎኑ የፈሰሰውን፡ *ደም፥ ውኃና መንፈስ* እንደሚኾን፡ ይህም፡ ኅብስትና ወይን፡ በሥርዓተ ቅዳሴውና በፍሬ ቅዳሴው ጸሎት፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም ይኾናል:: ይህ፡ በእርግጥ እውን የሚኾነው፡ *“እግዚአብሔር፡ መንፈስ ነው፤ የሚያመልኩትም፡ በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ያስፈልጋቸዋል!”* በሚለው፡ በጌታ ቃል መሠረት፡ አቀባዩ ካህንና ተቀባዩ ምእመን፡ በዚያ ሥርዓተ ቅዳሴ ላይ የሚያካኺዱት አምልኳቸው፡ ማለትም፡ ሃይማኖታቸውና ምግባራቸው፥ ንስሓቸውና ጸሎታቸው፡ መንፈስ ቅዱስ በሚያውቀውና በሚቀበለው፥ ካህኑና ምእመኑም በእየራሳቸው በሚያውቁትና በሚያቀርቡት፡ “መንፈሳዊ እውነት” የኾነ እንደኾነ ብቻ ነው:: ይህም ማለት፡ ካህኑና ምእመኑ፡ በአምልኮታቸው ጊዜ፡ በዚህ “የእግዚአብሔር እውነትና መንፈስ” የማይገኙ ከኾኑ፡ ያ የተቀደሰበት፡ የጻሕል ኅብስትና የጽዋ ወይን፡ ወደመለኮት ሥጋና ደምነት አይለወጥም ማለት ነው::[፳፩]

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ቍርባን።

### ስለኅብስቱና ወይኑ: ወደመለኮት ሥጋነትና ደምነት መለወጥ።

በበለጠ ለማብራራት: ዛሬም: በዘመነ ምሕረት በተገኘው አዲስ ኪዳን: "በመንፈስና በእውነት" መመለክን የሚወድደው: ያ: እግዚአብሔር ወልድ: ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ: ከቅድስት ድንግል ማርያም በሰውነት በመወለድ: ለዘለዓለም ሕይወት ይኾነን ዘንድ: ሥጋውን እንድንበላ፥ ደሙንም እንድንጠጣ ሰጠን። ስለዚህ: ሥጋውና ደሙ በሚፈተትበት: በአዲስ ኪዳኑ ታቦት ፊት: እኛ: በእውነት ስንቀርብ፥ እርሱ ደግሞ: በዚያ: በቀረበው መሥዋዕት ላይ: በቅዱስ መንፈሱ ተገልጾ: አምልኳችንን ይቀበላል።

እንዲህ: በእውነት የምናቀርብለትን አምልኳችንን: በመንፈስ መቀበልን የሚወድደው አምላካችን: በቅዱስ ቁርባኑ ላይ ተገኝቶ: መለኮታዊ ምሥጢሩን የሚያከናውነው: በመንፈስ ቅዱስ ነው፤ ይህም: በቍርባን ጊዜ: በእርግጥ: ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የሚቀበሉት: ከካህናቱም ኾነ ከምእመናኑ ወገኖች መካከል: የበቁት ብቻ በመኾናቸው ይታወቃል። "የበቁት" የሚባሉትም: በንስሓቸው: "እውነተኞች" ኾነው የቀረቡት ናቸው፤ ለእነርሱ: በመንፈስ ቅዱስ የተለወጠው: የመለኮት ሥጋና ደም ይሰጣቸዋል። በ"እውነተኛነት": ወይም: በ"እውነተኛ ንስሓ" ያልቀረቡት ግን: ካህናቱም ኾኑ ምእመናኑ: የጎረሱት: ምድራዊዉን የኅብስት ቁራሽ፥ የተጎነጩትም: ምድራዊዉን የወይን ጭማቂ እንጂ: መለኮት የተዋሐደውን: መንፈሳዊዉንና ሰማያዊዉን አይደለም፤ እነዚህ: በ"እውነት" ባለመቅረባቸው: "ስላልበቁ": በምሥጢረ ቍርባን ትርጓሜ እንደሚታተተው: መለኮት የተዋሐደውን: መንፈሳዊውን ሥጋና ደም: መላእክት ከእነርሱ ወስደው: በዚያው ቤተ ክርስቲያን ላሉት: በ"እውነተኛነታቸው" "ለበቁት" ካህናት እና/ወይም ምእመናን፥ ወይም በበረሃ ለሚኖሩት ገዳማውያን እና/ወይም ባሕታውያን ይሰጧቸዋል ማለት ነው።

### ስለአዲሱ ኪዳን ጽላትና ታቦት።

**ጥያቄ:-** *የአዲስ ኪዳን ታቦት ስላልከው ነገር: እዚህ ላይ: ጥቂት ብትነግረን?*

**መልስ:-** "ጽሌ": በነጠላው: "ሰሌዳ" ማለት ሲኾን: በኹለትና ከዚያ በላይ ሲበዛ: "ጽላት" ይባላል፤ "ታቦት": ጽላቱ የሚቀመጥበት: "ሣጥን" ማለት ነው። ሙሴ: በደብረ ሲና: ከእግዚአብሔር የተቀበላቸውን: ኹለቱን ጽላት የያዘው: የቃል ኪዳኑ ታቦት: አንድ ብቻ ነበር፤ ይህም ታቦት: በብሉዩ ኪዳን ዘመን እሪት: ለእግዚአብሔር አምልኮ: የተቀደሰ ማዕከል ኾኖ ሲያገለግል ቆየ። በእነዚያ ጽላት ላይ በተጻፉት ዐሥሩ ቃላት የተገለጸው: ያ: እግዚአብሔር ወልድ: ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ: ከአማናዊቷ ታቦት: ከድንግል ማርያም: በሰውነት ከተወለደ በኋላ ግን: አንድ ጽሌን ብቻ የያዘ: ሌላ ተመሳሳይ ታቦት: በክርስትና እምነት መሠረት: ተዘጋጀ።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

የአዲስ ኪዳኑን ጽሌ (ጽላት) የያዘው ይህ ታቦት፡ በየቤተ ክርስቲያኑ መቅደስ ውስጥ ባለው መንበር መካከል ተቀምጦ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ወደመለኮት ሥጋና ደምነት ይለወጥ ዘንድ፡ ኅብስቱ፡ በጻሕል፡ ወይኑ፡ በጽዋ[፳፯] ኾኖ ለሚቀርበው፡ ለአዲስ ኪዳኑ ቅዱስ ቍርባን በመሠዊያነት ያገለግላል።

ኹለቱን፡ የብሉዩን ኪዳን ጽላት ተክቶ፡ በአዲሱ ታቦት (ማጥን) ውስጥ የተቀመጠው፡ የአዲስ ኪዳኑ ጽሌ (ጽላት)፡ አራት ማዕዘንና ከኹለት መዳፍ ያልበለጠ ስፋት ያለው፡ ጠፍጣፋ ኾኖ፡ ከማይነቅዝ እንጨት ተፈልፍሎ፡ ወይም፡ ከዕብነ በረድ ተጠርቦ የወጣ፡ ነጠላ ሰሌዳ ሲኾን፡ በላዩ ተቀርጾ የሚታየው ጽሑፍ፡ እንደቀደሙት ጽላት፡ ዐሥሩ ን ትእዛዛት የያዘው፡ የእግዚአብሔር ቃል ሳይኾን፡ ያ ቃል፡ በድንግል ማርያም ማሕፀን፡ ሰው መኾኑን ለማሳየት፡ ከላይ፡ የቅድስት ሥላሴ ስም እና/ወይም ሥዕል፡ በመኻል፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥነ ስቅለት ኾኖ፡ በቀኝ፡ የድንግል ማርያም፡ በግራ፡ የወንጌላዊው ዮሓንስ ሥዕሎች፡ ዙርያውንም፡ የእግዚአብሔር፡ የአምላክነቱ ስሞች ተጽፈውና ተሥለው የሚታዩበት ነው። ያ፡ ታቦት የሚገኝበት ቤተ መቅደስ፡ በጌታ ወይም በእመቤታችን ስም እንደኾነ፡ ስማቸው፡ አለዚያ፡ መታሰቢያነቱ፡ ለነቢይ፡ ለሓዋርያ፡ ለጻድቅ፡ ለሰማዕት ወይም ለመልአክ ከኾነ፡ የዚያ ቅዱስ ስም፡ "ዝ ጽላት፡ ዘቅዱስ እከሌ" ተብሎ፡ ከጀርባው ይቀረጽበታል።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ በዚያ፡ በመጀመሪያው የአዲስ ኪዳኑ ጽሌ ዓይነት፡ ነገር ግን አራት ማዕዘን ኾኖ፡ በዕብነ በረድ፡ ወይም በማይነቅዝ የእንጨት ዓይነት፡ በተለያየ ቅጽና ቅርጽ እየተዘጋጀ፡ እየተራባና በተገቢው ሥርዓተ ጸሎት እየተባረከ፡ ታቦት በተባለውም፡ የእንጨት ማጥን ውስጥ በክብር እንዲቀመጥ እየተደረገ፡ ሲሠራበት ኖርዋል። ይህን የመሰለውን ጽላትና ታቦት ነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፡ ለሰው ልጆች ባስገኘው ዘለዓለማዊ ትድግናው አማካይነት፡ የሚወርዱትን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች፡ ወደምእመናን ለማስተላለፍ የሚያስችሉት ምሥጢራትና ሥርዓታት በሚፈጸሙበት፡ በእያንዳንዱ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መቅደስ ባለው መንበር ውስጥ እያኖሩ የሚቀድሱበት። ይህ ሥርዓት፡ የእኛ የኢትዮጵያውያን ብቸኛ ቅርሳችን መኾኑን አትዘንጉትም።

በብሉዩ ኪዳን እንደነበረው ኹሉ፡ የአዲስ ኪዳኑም ጽሌ፡ ወይም በልማድ እንደሚባለው፡ ጽላቱ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ ታቦቱ ደግሞ፡ የቅድስት እናቱ፡ የድንግል ማርያም ምሳሌ የመኾኑ ምሥጢር፡ ሳይቃወስ ቀጥሏል። እንዲህ ኾኖ፡ የአዲስ ኪዳኑን እምነት በመከተል ያልተቋረጠው፡ ይህ፡ የጽላትና የታቦት ዝግጅትና ሥርዓት፡ እስከዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥር በተቋቋሙት አብያተ ክርስቲያን ዘንድ ሲካኼድ የኖረው፡ ለምን እንደኾነ፡ ከዚህ የሚከተሉት ሦስት ምክንያቶች በሚበቃ ያስረዳሉ፡-

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ቍርባን።

### ስለአዲሱ ኪዳን ጽላትና ታቦት።

---

፩ኛ: ማናቸውም የቤተ ሕዝቡ ሰበካ ጉባዔ: ማለትም: ገጠር: ደብር ወይም ገዳም: በማኅበር ተቋቁሞና በቤተ ክርስቲያንነት ተደራጅቶ መገልገል ሲፈልግ: ጽላቱ: ከሌላ ከማንም ምእመን: ካህን ወይም ጳጳስ ሳይኾን: ሕጋዊው ሥልጣን ካላት: ከኢትዮጵያ ቤተ ክህነት: በዘመኑ እጨጌ አማካይነት ብቻ: ለዚያ ሃይማኖታዊ አቋምና መንፈሳዊ ድርጅት: የመሠረቱ ድንጋይ: ሕጋዊው ፈቃድና መለኮታዊው ማኅተም ኾኖ ይሰጣል።

፪ኛ: ካህናቱ: በእውነተኛው ሃይማኖታዊ አምልኮ ኾነው: በቅዳሴ ጊዜ በሚያከናውኑት ሥርዓተ ጸሎት: የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ኃይል በዚያ ተገኝቶ: ወደኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ይለውጠው ዘንድ: ኅብስተ አኰቴቱን: በጻሕል: ወይኑ በረከቱን: በጽዋ አድርገው: ለሚያቀርቡት ቅዱስ ቍርባን: በመንበሩ መካከል ጽላቱን ይዞ የሚገኘው ታቦት: መሠዊያ ኾኖ: ተልእኳቸው ይፈጸምበታል።

፫ኛ: በኪዳነ ልቦና: ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ እስከኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ: ከዚያም በኢትዮጵያዊው ካህን ዮቶር በኩል: እስከንግሥተ ሳባ ዘመን: ተያይዞ የደረሰው: የኅብስተ አኰቴትና የጽዋዓ በረከት አምልኮተ እግዚአብሔር: በኪዳነ ኦሪቱ ተጠናክሮ ከኖረ በኋላ: "የአዲሱ ኪዳኑ አቤሜሌክ" በተባለው: በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የክርስትና ጥምቀት ጸድቆ እንዲቀጥል በተደረገ ጊዜ: የጽላቱና የታቦቱ ሥርዓት: ሽግግሩን እንዴት እንዳሠመረው በማዘከር: ይህን ቅርስ ጠብቃ የኖረች ኢትዮጵያ ብቻ መኾኗን ለማረጋገጥ: የአዲስ ኪዳኑን ጽላት የያዘው: ይኸው ታቦት: የዚህ ትውፊት: አማናዊ ድልድይና ቋሚ ማስረጃ ኾኖ: ለትውልደ ትውልድ ይተላለፍበታል።

ይህን: የብሉይ ኪዳኑን የአምልኮተ እግዚአብሔር ሥርዓት: እንዲህ: በአዲስ ኪዳኑ ምሥጢራት አድሶና አስተካክሎ በመተካት: የቀድሞው ቅርስ ተጠብቆና ሕያው ኾኖ እንዲቀጥል የማድረጉ ችሎታና ብቃት የተገኘው በኢትዮጵያውያን ዘንድ ብቻ መኾኑ ይታወቃል። ይኹን እንጂ: ኢትዮጵያውያን: አምላካቸውን: እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት: ይኸው አዲሱ የክርስትና ሥርዓት: ጥንትም ኾነ ኋላ: ምንጊዜም:- *"እግዚአብሔር: መንፈስ ነው: የሚያመልኩትም: በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ያስፈልጋቸዋል።"* በሚለው በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ላይ የተመሠረተና ያንን የተከተለ መኾኑ ሊዘነጋ አይገባም።

ይህን የመሰለው: በቅዱሱ ኪዳን ላይ የተመሠረተው: የአምልኮተ እግዚአብሔር ባህል: ባንድ ወገን: የቃል ኪዳኑ ታቦት: ወደኢትዮጵያ መጥቶ: እስከመጨረሻው: በዚችው ምድር ለመቆየቱ: ተጨባጭ ማስረጃና ሕያው ምስክር ሲኾን: በሌላው ወገን ደግሞ: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን: በመላዋ ምድር ላይ በሚገኙት: በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ መካከል: ከኹሉ የተለየች ብርቅና ከኹሉ የቀደመች አረጋዊት ለመኾኗ: ዓቢዩ መለያ ምልክት ኾኖ ይኖራል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

### የቅዱስ ቍርባን አስፈላጊነት፡፡

ጥያቄ፡- *ምሥጢረ ቍርባን፡ ለምን እንዳስፈለገ፡ ምክንያቱን አስፋፍተህ ብትገልጽልን?*

መልስ፡- እኛ ሰዎች፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከእግዚአብሔር ያገኘነው ጸጋ፡ ፍጹምና ሙሉ ነው፡፡ የመጀመሪያው ጸጋ፡ በምሥጢረ ጥምቀት ሐተታ ላይ እንደተገለጸው፡ ከእግዚአብሔር በመንፈስ ተወልደን፡ ከሰይጣን ገዥነት፥ ከኃጢአት ቀንበርና ከሞት ፍርድ ነጻ የኾነ፡ አዲስ መንፈሳዊ አካልን መልበሳችን ሲኾን፥ ኹለተኛው ደግሞ፡ ሰውነታችንን፡ ከኃጢአት በንስሓ ካነጻን በኋላ፡ በልተነውና ጠጥተነው፡ ከእግዚአብሔር ጋር፡ በመንፈስ ብቻ ሳይኾን፡ በሥጋና በደም ጭምር፡ እንድንዋሐድና ሕያዋን ቤተ መቅደሶቹ እንድንኾን፡ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መስጠቱ ነው፡፡ የቤተ ክህነት መኖር፡ ማለትም፡ የካህናት መሠየምና የቤተ ክርስቲያን መቋቋም፡ ብቸኛ ዓላማው፡ ሌላ ሳይኾን፡ የሰውን ልጆች ኹሉ፡ ለዚህ ጸጋ ለማብቃት መኾኑን፡ በትክክል ልትገነዘቡት ይገባል፡፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከተጠመቀ በኋላ፡ ለሚሰሙት ኹሉ፡ ማንነቱን እየገለጠ ሲያስተምራቸው፡ *"በእኔ የሚያምን፡ የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ ከሰማይ የወረደ፡ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው፡ ከዚህ እንጀራ ቢበላ፡ ለዘለዓለም ይኖራል፤ እኔም፡ ስለዓለም ሕይወት፡ የምሰጠው እንጀራ፡ ሥጋዬ ነው፡፡ <u>...እውነት፡ እውነት እላችኋለሁ! ሥጋዬን ካልበላችሁ፥ ደሜንም ካልጠጣችሁ፡ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም፡፡</u> ሥጋዬን የሚበላ፥ ደሜንም የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ እኔም፡ በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ፡፡ ሥጋዬ፡ እውነተኛ መብል፥ ደሜም፡ እውነተኛ መጠጥ ነውና፡፡ ሥጋዬን የሚበላ፥ ደሜንም የሚጠጣ፡ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ፡፡ ሕያው አብ እንደላከኝ፥ እኔም፡ ከአብ የተነሣ፡ ሕያው እንደምኾን፡ እንዲሁ፡ የሚበላኝ ደግሞ፡ ከእኔ የተነሣ፡ ሕያው ይኾናል፡፡ ...ወደእኔ የሚመጣ፡ ከቶ አይራብም፤ በእኔ የሚያምንም፡ ኹልጊዜም፡ ከቶ አይጠማም፤ እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ኹሉ፡ ለዘለዓለም አይጠማም፡፡"*[፳፯] ሲል ተናግሮ ነበር፡፡

በሥጋዊው አካላችንና በደማዊት ነፍሳችን የሚንቀሳቀሰው ግዙፉ ኹለንተናችን፡ የሚተነፍሰውን አየር፥ የሚጠጣውን ውኃና የሚበላውን ምግብ፥ የሚሞቀውንም የፀሓይ ብርሃን ካጣ፡ የዚህ ዓለም ሕይወቱ ሊቀጥል እንደማይችል ኹሉ፡ እንዲሁ፡ ለባዊቷና ነባቢቷ፥ ሕያውቷም ነፍሳችን፡ ፈጣሪዋ፡ በተለይ፡ ለእርሷ፡ "ያስፈልጋታል!" ብሎ ያዘጋጀላትን፡ ምግብና መጠጥ ከተነፈገች፡ ከመልካም ሕይወቷ ትቋረጣለች፡፡ ባጭሩ፡ ሥጋዊው ሰውነታችን፡ በፍጥረታዊ ህልውናው ለመኖር፡ በምልዓት ከተሰጠው፡ ከአየሩ እስትንፋስና ከፀሓዩ ብርሃን ጋር፡ በብርቱ የሚያስፈልጉት፡ ምድራዊው መጠጥና ምግብ እንደመኾናቸው መጠን፡ ነፍሳዊዋ ሰውነታችንም፡ በዘለዓለማዊው ህልውናዋ ጸንታ ለመገኘት፡ የሚያስፈልጋት፡ መንፈሳዊው ምግብና መጠጥ የኾነው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ነው፡፡

# ምዕራፍ ፫፣ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ቍርባን።

### የቅዱስ ቍርባን አስፈላጊነት።

---

*እውነት፡ እውነት እላችኋለሁ! ሥጋዬን ካልበላችሁ፡ ደሜንም ካልጠጣችሁ፡ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም።* የሚለው አምላካዊ መመሪያ፡ በሥጋ አካል ግዘፎና በመንፈስ አካል ረቅቆ ያለው፡ ይህ፡ "እኔ" የምንለው፡ የእየራሳችን ማንነት የታወቀባት፡ ዘለዓለማዊቷ ነፍሳችን፡ "ያለዚህ ቅዱስ ቍርባን፡ ሕይወትም፡ ህልውናም የላትም!" ማለቱ መኾኑ፡ ለማንም ሰብአዊ ፍጡር ግልጽ የኾነ ቃል ነው።

ጥያቄ፡- *ይህ ቃል፡ ለእኔ ብቤ ሰሚ፡ እንዴት ያስጨንቃል?*

መልስ፡- አዎን! ለአንተ ብቻ ሳይኾን፡ በእርግጥ፡ ለማንም ያስጨንቃል፡ ይልቁንም፡ ይህን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል፡ በዚያች ወቅት፡ በአጠገቡ ኾነው፡ ከአንደበቱ ሲወጣ የሰሙት ደቀ መዛሙርቱ ሳይቀሩ፡ ግራ ገብቷቸው፡ *"ይህ፡ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው፡ ማን ሊሰማው ይችላል?"* ሲሉ፡ እርስ በርሳቸው የተለዋወጡትን የኑፋቄ አሳብ፡ እዚህ አስታውሼ ስጠቅሰው፡ ይህ የአንክሮ[፷፯] ጥያቄያችሁ፡ ከዚያ አነጋገራቸው ጋር ፈጽሞ መመሳሰሉ ያስደንቀኛል።

የእግዚአብሔር የኾነው ቀርቶ፡ ፍጥረታዊ የኾነው የሥነ ፍጥረት ነገር እንኳ፡ ለራሱ፡ ፍጡር ለኾነው ለሰው ጭምር፡ የረቀቀ ምሥጢር ኾኖበት፡ ይከብደዋል፡ ያስጨንቀዋል፡ ለዚህ ነው፡ ሐዋርያው፡ *"ለፍጥረታዊ ሰው፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር፡ ሞኝነት ነውና፡ አይቀበለውም፡ በመንፈስ የሚመረመር ስለኾነ፡ ሊያውቀው አይችልም፡"* ያለው። በእግዚአብሔር መንፈስ ያለ፡ ሰው ግን፡ የእግዚአብሔር የኾነውን ሊመረምርና ሊያውቅ እንደሚችል፡ ይኸው ሐዋርያ፡ *"እኛ ግን፡ የክርስቶስ ልብ አለን!"* ባለው[፷፰] መደምደሚያ ቃሉ አረጋግጦታል።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ይህን ጭንቀታቸውንና ኑፋቄአቸውን፡ በሃይማኖት ለማስወገድ፡ ሕማማተ መስቀሉና ሞቱ ከሚፈጸምባት፡ ዕለተ ዓርብ በፊት ባለችው፡ "ምሴተ ሐሙስ" በተባለችው፡ በመጨረሻዋ የሐሙስ ምሽት፡ ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ፡ ለፋሲካ ራት ተቀምጦ ሳለ፡ በገበታው ላይ ያለውን ኅብስቱንና በጽዋ የተቀዳውን ወይኑን፡ ኹለቱንም አንሥቶ፡ ወደእርሱ ሥጋና ደምንት ለውጦ ሰጥቷቸዋል። ይህንም ያደረገው፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ ኹሉ የሚቻል መኾኑን ሊያሳያቸው፡ እርሱ ራሱም፡ እግዚአብሔር ወልድ መኾኑን ሊያሳውቃቸው፡ ከትንሣኤው በኋላ፡ የሚቀበሉትን፡ የጸሐሉን ኅብስትና የጽዋውን ወይን ለውጦና የመለኮት ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም አድርጎ የሚሰጣቸው፡ ያው፡ እርሱ ራሱ መኾኑን ሊያረጋግጥላቸው መኾኑን እንድትገነዘቡት ያስፈልጋል።

በማግሥቱ ዓርብ፡ መለኮት የተዋሐደውን ሰውነቱን፡ እውነተኛውና ዘለዓለማዊው የፋሲካ በግ አድርጎ፡ በመስቀል ላይ በመሥዋዕትነት የሚያቀርበው መኾኑን በማመልከት፡ በሰጣቸው የዘለዓለም መመሪያ፡ ይህንኑ፡ የቅዱስ ቍርባንን ረቂቅ ምሥጢር፡ ለደቀ መዛሙርቱ፡ አብራርቶና አግዝፎ አሳውቋቸዋል።

*የሳወቃቸውም፡ ያን፡ የሚሠዋውን ሥጋውን፡ በጻሕሉ ኅብስት ለውጦ፡ "ይህ፡ ሥጋዬ ነውና፡ እንካችሁ ብሉ!"፡ ያን፡ የሚያፈስሰውን ደሙንም፡ በጽዋው ወይን ለውጦ፡ "ይህም፡ ስለብዙዎች፡ ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስስ፡ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነውና፡ ኹላችሁ፡ ከእርሱ ጠጡ!"* ብሎ፡ ለእያንዳንዳቸው በመስጠት ነው፡፡ እኛም፡ ይህን መመሪያ፡ እስከዳግም ምጽዓቱ ድረስ፡ ለሕይወታችን ስንል፡ በመታሰቢያነቱም ሳናቋርጥ፡ እያከበርነው እንቆይ ዘንድ ባዘዘን መሠረት፡ እነሆ፡ ዛሬ፡ *ምሥጢረ ቍርባን* ብለን፡ በሥርዓተ ቅዳሴ፡ ስንፈጽመው እንገኛለን፡፡[፴፱]

ዘወትር በየቀኑና በየዕለተ ሰንበቱ፡ በየበዓላቱም፡ በየቤተ ክርስቲያኑ የሚቀደሰው ቅዳሴ፡ ይህን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተውን፡ የምሥጢረ ቍርባንን ሥርዓት ለመፈጸም ስለኾነ፡ እኛ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ይህንኑ ሥርዓት ከማካኼድ አናስታጕልም፡፡

## ስለቅዱስ ቍርባን የሚደረገው ሥርዓተ ቅዳሴ፡፡

ጥያቄ:- *እዚህ ላይ፡ የጻሕሉን ኅብስትና የጽዋውን ወይን፡ ወደመለኮት ሥጋና ደምነት እንዲለወጥ ስለሚያደርገው፡ ስለቅዳሴ ሥርዓተ ጸሎት ብታስረዳን?*

መልስ:- ሕዝቡ፡ በቤተ ክርስቲያኑ መቅደስ፡ በአፍኣ (በውጭ) ኾነው፡ ተሰጥኦውን እየተቀበሉ (ለጸሎቱ ምላሽ እየሰጡ)፥ ልኡካኑ ካህናት (ልብሰ ተክህኖ ለብሰው፡ በቅዳሴው ጊዜ የሚያገለግሉት ቀሳውስትና ዲያቆናት) ደግሞ፡ እመቅደሱ ውስጥ ኾነው፡ ኅብስቱን፡ በጻሕል፥ ወይኑን፡ በጽዋ አድርገው፡ ለእግዚአብሔር በሚያቀርቡት፡ በአዲስ ኪዳኑ መሥዋዕት ላይ የሚያካኺዱት፡ ማለትም፡ ምሥጢረ ቍርባንን የሚፈጽሙበት፥ የጸሎት ሥርዓት፡ "ቅዳሴ" ይባላል፡፡

የቅዳሴ ጸሎት፡ ለመልካሙ ሥጋዊና መንፈሳዊ፥ ምድራዊና ሰማያዊ፡ ጊዜያዊና ዘለዓለማዊ ሕይወት ትብቁ ዘንድ፡ ኑ! "ሥጋዬን ብሉ! ደሜንም ጠጡ!" የሚለውን፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለድ፡ ሰው የኾነውን የእግዚአብሔርን ጥሪ፡ እያንዳንዳችን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ተቀብለን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሊቀ ካህናትነትና በንጉሠ ነገሥትነት፡ ድንግል ማርያም፡ በቤተ መቅደስነትና በንግሥተ ንግሥታትነት ክብር በተቀመጡበት ዙፋናዊ መንበር ፊት፡ በፍጹም ትሕትና ቆመን፡ የፈጣሪያችንን የሕይወት ግብዣ ለመሳተፍ የምንገኝበት፡ የመለኮታዊው ግብር ቅዱስ ገበታ ነው፡፡

የቅዳሴው ሥርዓት ዝግጅት፡ ይህን ታላቁን የፈጣሪን ዓላማ፡ ከግቡ ለማድረስ በመኾኑ፡ እያንዳንዳችን፡ የሥርዓቱ ተካፋዮች፡ ውሳጣዊት ነፍሳችንን፡ በንስሓ አንጽተንና የሥጋ አካላችንን፡ በውኃ አጽድተን፥ መንፈሳችንንም፡ ለእውነተኛው አምልኮ አብቅተን፡ ብሩህና ጸዓዳ ልብስን በተጎናጸፈ ሰውነት መቅረብ ይገባናል፡፡

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ቍርባን።

### ስለቅዱስ ቍርባን የሚደረገው ሥርዓተ ቅዳሴ።

---

ይህ፡ የቅዳሴ ሥርዓተ ጸሎት፡ "ሥርዓተ ቅዳሴ" እና "ፍሬ ቅዳሴ" ተብሎ፡ በኹለት አርእስት ይከፈላል፦

- "ሥርዓተ ቅዳሴ" የሚለው፡ የመጀመሪያው ክፍል፡ የቅዳሴው የመግቢያና የመዘጋጃ ተግባሮች የሚፈጸሙበት፥ ለዕለቱ ተስማሚና ተገቢ የኾኑ ምንባቦች፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት እየተውጣጡ የሚነበቡበትና የሚደመጡበት፥ ትምህርታዊ መልእክትም የሚተላለፍበት፥ ልዩ ልዩ የምልጃ ጸሎቶች የሚቀርቡበትና የምስጋና መዝሙሮች የሚዘመሩበት ጊዜ ነው።

በሕዝባዊው አነጋገር፡ "ቅዳሴ ገቡ!" የሚባለውን፡ የቅዳሴውን መጀመር የሚያበሥረው የአዋጅ ምልክት፡ ከውስጥ፡ ከቤተ ልሔም፡ በቃጭል ድምፅ፥ በውጭ፡ በዓፀደ ቤተ ክርስቲያኑ ደግሞ፡ በደወል ድምፅ ተላልፎ ይሰማል። ለቅዳሴው መጀመር፡ የአዋጅ ምልክት የኾነው ቃጭል፡ በቅድሚያ የሚመታው፡ በቤተ መቅደስ ከሚጠባበቀው፡ ከ"ሠራዒው" (ከዋናው መሥዋዕት አቅራቢ) ቄስ በቀር፡ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው፡ ለአገልግሎቱ የተሠየሙት ልኡካን፡ ገና ከቤተ ልሔም ሲወጡ ነው።

ቃጭሉ፡ ከእነርሱ መካከል፡ ዣንጥላውን፡ በመሥዋዕቱ ቍርባን ላይ፡ ከጎን ኾኖ ባጠላው፡ በ"ንፍቁ" (ረዳት በኾነው) ዲያቆን እየተመታ፥ "ሠራዒው" (የቍርባኑን ደም፡ ለምእመናን የሚያቀብለው ዋናው) ዲያቆን፡ የወይኑ ጭማቂ የተመላበትን መቍረርት፡ በተጌጠ ማኅፈድ ሸፍኖ ይዞ፡ ከፊት ለፊት እየመራ፥ በመኻል፡ "ፍሬ ሰሞነኛው" (ሳምንቱን ሙሉ፡ የቤተ ክርስቲያኑን ቍልፎች ኹሉ ይዞ፡ መሥዋዕቱን የሚያዘጋጀው) ዲያቆን፡ ኅብስት አኰቴቱ የሚገኝበትን መሶበ ወርቅ፡ እንደታቦት፡ በመኈናጸፊያ ተሸክሞ፥ ንፍቁ ቄስ፡ ፍሕምና ዕጣን የመላበትን ማዕጠንቱን እያወዛወዘ፡ መሥዋዕቱን ከኋላ አጅቦ፡ ከተዘጋጀበት፡ ከቤተ ልሔም አንሥተው ይዘው፡ ወደቤተ መቅደሱ ያመራሉ።

ቀዳስያኑ ካህናት፡ በዚህ መልክ፡ መሥዋዕቱን ከተዘጋጀበትና በምሥራቅ አግጣጫ ከሚገኘው፡ ከቤተ ልሔሙ፡ አንሥተውና አጅበው፡ በክብር፥ በይባቤ፥ በዕጣኑ መዓዛ ታውደው፡ ወደቤተ መቅደስ ይገባሉ፤ እየዘመሩም፡ መንበሩን ሦስት ጊዜያት ይዞራሉ፤ "ሃሌ ሉያ! የሚለውን፡ የቅዳሴውን የመግቢያ ጸሎት እያዜሙ በሚዞሩበት ጊዜ፡ ለሕዝቡ ከሚያስሰሙት የአዋጅ ቃል መካከል፡ እንዲህ የሚለው፡ ብርቱና ግልጽ ማሳሰቢያ ይገኝበታል፦ ይህንም፡ እናንተ፡ በማስተዋል አዳምጡት!

*"ሃሌ ሉያ! ወደቤተ ክርስቲያን ከገቡ ምእመናን መካከል፡ በቅዳሴ ጊዜ፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን የማያዳምጥ፥ የቅዳሴውም ጸሎት እስኪፈጸም የማይታገሥ፥ <u>ከቍርባኑም የማይቀበል ቢኖር፡ ከቤተ ክርስቲያን ይለይ! የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና፤ የሥጋና የነፍስ ንጉሥ በሚኾን፡ በሰማያዊው ንጉሥ ፊት መቆምንም አቃሏልና፤</u> ሐዋርያት፡ እንዲህ ብለው፡ በሲኖዶሳቸው አስተምረውናል።"*[፳]

ሠራዒው ቄስና ተራዳኢው ቄስ፡ ከተገቢው ጸሎት ጋር፡ ኅብስቱን በጻሕል፥ ወይኑን በጽዋ አድርገው፡ በመንበረ ታቦቱ ላይ የሚያስቀምጡት፡ በዚህ ጊዜ ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

በቅዳሴው መግቢያ ሥርዓት፡ ከቤተ ልሔም ጀምሮ እስከዚህ ድረስ የሚፈጸመው፡ እያንዳንዱ ድርጊት፡ በዚህ መልክ የሚካኼድበት ምክንያት፡ ትርጉምና ምሳሌነት አለው፦ ይኸውም፡ አማናዊው መሥዋዕትና ዘለዓለማዊው ቍርባን የኾነው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለእኛ ለሰዎች ሲል፡ ከእውነተኛዋ ቤተ ልሔም፡ ከቅድስተ ድንግል ማርያም፡ በበረት ውስጥ ተወልዶ፡ በ፰ኛው ቀን ከተገረዘ በኋላ፡ በ፵ኛው ቀን፡ ወደቤተ መቅደስ መግባቱን፡ ለሦስት ዓመታት ከሦስት ወራት እየተዘዋወረ ማስተማሩንና ተአምራት ማድረጉን፡ ከጥምቀቱ እንሥቶ፡ እስከሞቱ ድረስ፡ በቀራንዮ ካፈሰሰው ደሙ ጋር፡ ከተቀበላቸው የመስቀል መከራዎችን፡ በትእግሥት መቀበሉን፡ በመጨረሻም፡ ከሙታን ተለይቶ መነሣቱንና ወደሰማያዊ ክብሩ ማረጉን፡ ከዚህ ኹሉ ቤዛነቱ የተነሣ፡ ከእግዚአብሔር የምንወለድበትን፡ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ያስገኘልን መኾኑን በማዘከር፡ ያ የመለኮት ዕፁብ ድንቅ የቸርነት ሥራ፡ ዛሬም፡ እነሆ፡ አኹን በቀረበው፡ በዚህ፡ በኅብስቱ ሥጋውና በወይን ደሙ ቅዱስ ቍርባንነት፡ ሕያው ኾኖ የሚፈጸምበት ሥርዓተ ጸሎት፡ ይኸው ተጀመረ ለማለት ነው።

- "ፍሬ ቅዳሴ" የሚባለው፡ ኹለተኛው ክፍል ደግሞ፡ ከወንጌል ንባብና ምዕዳን በኋላ ተያይዞ፡ እስከቅዳሴው ፍጻሜ ድረስ የሚቀጥለውን ጸሎት የሚያጠቃልል ነው፡ ይህም፡ በቅዳሴው መግቢያ ላይ እንደተደረገው ኹሉ፡ በቃጭልና በደወል የድምፅ ምልክት የታጀበ፡ የአዋጅ ቃል እየተነገረበት የሚጀመር፡ የጸሎቱ ዋናውና ተከታዩ ምዕራፍ ነው።

ሠራዒው ዲያቆን፡ ቃጭሉን እየደወለ፡ በዜማ፡ "ዓው ንኡስ ክርስቲያን!" ማለትም፡ "የክርስቲያን ታናናሾች ውጡ!" የሚለውን የአዋጅ ቃል ያሰማል። ቀድሞ፡ ይህ የአዋጅ ቃል እንዲነገር የተደነገገው፡ የክርስትናውን ትምህርት ተምረውና አውቀው፡ ለመጠመቅ፡ ገና ያልበቁት ወንዶችና ሴቶች፡ የቅዱስ ሥጋውና የክቡር ደሙ ምሥጢር እየተነገረ በሚዘጋጅበትና በሚፈተትበት ጊዜ ግር እንዳይላቸው፡ ለእነርሱ የሚያስፈልጋቸውና እነርሱ ሊካፈሉበት የሚገባቸው ጸሎት ስላበቃ፡ "እንግዲህ፡ እናንተ፡ ወደየቤታችሁ ተመለሱ!" ለማለት ነበር።

በአኹኑ ጊዜ ግን፡ ይህ የአዋጅ ቃል እንዲሰማ የሚተላለፈው፡ በቤተ ክርስቲያን ተጠምቀው፡ "ክርስቲያን!" ከተባሉ በኋላ፡ እየራሳቸውን፡ በንስሓ እያደሱና ቅዱስ ቍርባንን እየተቀበሉ፡ ክርስቲያናዊዉን ሕይወት መኖር ሲገባቸው፡ ይህን ለማድረግ፡ ፈቃደኞች ሳልኾኑና በዚያ ሥርዓተ ቅዳሴ ላይ፡ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለማይቀበሉ፡ "በእውነት ሳይኾን፡ ለይስሙላ ብቻ፡ "ኢትዮጵያውያን ነን!" ለሚሉ ግለሰቦች ነው፤ እነዚህም፡ እግዚአብሔር፡ በለጋሥነቱ የሰጣቸውን፡ ታላቁን የኢትዮጵያዊነት ክብር፡ "አንፈልገውም!" ብለው፡ በገዛ ፈቃዳቸው በመወሰን፡ እየራሳቸውን፡ ከንኡስ ክርስቲያንነት ወደባሰው፡ ወደባዕዱ አምልኮ ወገንነት፡ አዘቅዝቀው ያዋረዱ ግለሰቦች ናቸው።

## ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::

### ምሥጢረ ቍርባን::

### ስለቅዱስ ቍርባን የሚደረገው ሥርዓተ ቅዳሴ::

---

አዎን! እኒህ ግለሰቦች: በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ተቀዳጅተውት፥ ነገር ግን: በእየራሳቸው አለመፈለግ ብቻ: ገሸሽ አድርገውት ወደነበረው: ወደእውነተኛው የኢትዮጵያዊነት ክብራቸው: በንስሓ ተመልሰው: ቅዱስ ቍርባንን ለመቀበል ፈቃደኞች እስኪኾኑ ድረስ: እነርሱ የሚሳተፉበት የጸሎቱ ክፍል: ያበቃ መኾኑን አውቀው: እየራሳቸውን ወደውጭ እንዲያገልሉ ይገባቸዋል::

በዚህ ፍሬ ቅዳሴ ጊዜ: መሥዋዕት ኾኖ የሚቀርበው: "የስንዴው ኅብስት" ተለውጦ: "መለኮት የተዋሐደው: የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ"፥ "የጽዋው ወይን" ተለውጦ: "መለኮት የተዋሐደው: የኢየሱስ ክርስቶስ ደም" ይኾናል:: እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት: ሊታሳቁ: መለኮታዊ ጸጋና በረከት በሚያበቃቸው: በዚህ ሥርዓት ላይ: በተቻላቸው ዓቅም: ምን ጊዜም እየ ተገኙ: የጸሎቱና የቁርባኑ ተሳታፊዎች ይኾናሉ::

የሥርዓተ ቅዳሴውና የፍሬ ቅዳሴው ሙሉ ጸሎት: በዚህ ውይይታችን መነሻነት: ወደፊት: ራሱን ችሎ: እንዲወጣ በሚደረገው የጸሎት መጽሐፍ ውስጥ: ከሌሎቹ መደበኞች ጸሎቶች ጋር ተዘጋጅቶ ስለምታገኙት: ዝርዝሩን እየተመለከታችሁት: በጸሎትነቱ ትጠቀሙበታላችሁ::

ጥያቄ:- *ሊታሳቁ: መለኮታዊ ጸጋና በረከት መብቃት እንዴት ነው?*

መልስ:- እያንዳንዳችን: የኃጢአታችንን ሥርየት: ከፈጣሪያችን: በንስሓ አግኝተን: ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ስንቀበል: በውስጣችን: ማለትም: ነፍሳችን: አጋርዋ በኾነው: በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ተጠብቃ በምትገኝበት: በመልካሙ "መንፈሳዊ" ፈቃድ እንጂ: በርኩስ መንፈስ እየተደገፈ ያለማቋረጥ ከሚጻረራትና ከሚያስቸግራት ከ"ሥጋዊ"ው ክፉ ፈቃድ ጋር ኹለቱ: የተለያዩ ፈቃዶች: ስለሚስማሙላት: አዎን! በውስጣችን: እውነተኛዋን የእግዚአብሔርን ሰላም እናገኛለን::

ይህንኑ ምሥጢራዊ ኃይል: ላብራራላችሁ:- በአንድ ወገን: እንስሳዊት በኾነችው: በደመ ነፍሳችን የሚንቀሳቀሰውና መልካም የኾነውን: የእግዚአብሔርን ሕግ መከተል የተሣነው፥ ይህ: ሟችና በስባሽ የኾነው: ሥጋዊ አካላችን አለ፤ እርሱም: ከአባት አብራክና ከእናት ማሕፀን: በዘር ስንወለድ: የወረስነው ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ: ቀድሞ: ከመለኮታዊው እስትንፋስ ተከፍላ: የተሰጠችንና ኋላም: በክርስትና ጥምቀት: ከእግዚአብሔር የተወለድንበትን: መንፈሳዊ ጸጋ የለበሰች በመኾኗ: መልካም የኾነውን: የእግዚአብሔርን ሕግ የምትሻው: ባለአእምሮና ባለአንደበት የኾነችው፥ የማትሞተው ነፍሳችን አለች:: ከእነዚህ ከኹለቱ: የሰውነታችን ግብይት አካላትና ባሕርያት የሚፈልቁት: ኹለት የተለያዩ ፍላጎቶች: እውነተኛው የሃይማኖት ንስሓና ሥጋ ወደሙ ባስገኙት የእግዚአብሔር ፈቃድ: ፍጹም ተስማምተው: አንድ ይኾናሉ::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

በዚህ ጊዜ፡ በሰይጣን ክፋት ምክንያት፡ ከእግዚአብሔር ተለይቶ የነበረው፡ የእኛ ሰብአዊ ፈቃድ፡ ተመልሶ፡ ለእግዚአብሔር ፈቃድ የሚገዛ ይኾናል። እኛም፡ ከእግዚአብሔር ጋር፡ በመንፈስ ብቻ ሳይኾን፡ በሥጋም ጭምር እንዋሐዳለን። እንደእኛ ካሉትም ምእመናን ጋር ኹሉ፡ ሙሉኅብረት ይኖረናል። ከዚህ እምነትና ሥርዓት ውጭ ከኾኑት ጋር፡ ያለን ግንኙነት ሳይቀር፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በምድር ላይ ያደርግ እንደነበረው፡ ችግር የሌለበት፡ መልካም ይኾናል።

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የሰው ጠላቶች የኾኑትን፡ ሰይጣንን፡ ኀጢአትንና ሞትን፡ ድል አድርጎ፡ ለዘለዓለም ሕያው እንደመኾኑ፡ እኛም፡ እነዚያኑ ጠላቶቻችንን፡ ድል የምናደርግበትን፡ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ተቀብለን፡ ከእርሱ ጋር፡ በሥጋም፡ በመንፈስም፡ በምንዋሐድበት ጊዜ፡ የድሉና የትንሣኤው ሕይወት ባለቤቶች የመኾንን ብቅዓት እናገኛለን። በዚህ ምክንያት፡ ሰይጣናዊው የክፋት ኃይል፡ ኀጢአትና ሞት፡ በእኛ ላይ ፈጽሞ ሥልጣን አይኖራቸውም፡ ከቶውንም፡ ሊቀርቡን አይችሉም። የሰይጣን ኃይል፡ ለፈተና ያህል፡ ቢያገኘን እንኳ፡ ድሉ፡ የእኛ ይኾናል። በማሰብ፡ በመናገር እና/ወይም በማድረግ፡ በኹለቱ፥ ወይም፡ በኹሉም፡ ኀጢአት ብንሠራ፡ መሳሳታችን፥ ማጥፋታችን፥ መበደላችን፥ ወይም፡ ኀጢአት መሥራታችን፡ በግልጽ ታውቆን፡ ወዲያው፡ ንስሓ ስለምንገባ፡ ኀጢአትና በኀጢአት ምክንያት፡ የሰው ልጆች ጽዋ የኾነው ሞት፡ በእኛ ላይ፡ ሥልጣን የሌላቸው ይኾናሉ፤ ዛሬ፡ በሕይወተ ሥጋ እያለን፡ በመንፈስ፡ ከሞት ወደሕይወት ስለተሸጋገርን፡ መሞት ቀርቶ፡ ለፍርድ እንኳ ከመቅረብ፡ ነጻ መኾናችንን አውቀን፡ በዕረፍትና በሰላም እንኖራለን። ይህንም፡ *“እውነት፡ እውነት እላችኋለሁ! ቃሌን የሚሰማ፥ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ ከሞት ወደሕይወት ተሻገረ እንጂ፡ ወደፍርድ አይመጣም።”*[፹፭] ብሎ በተናገረው ቃሉ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ አረጋግጦልናል።

በመላው የሥነ ፍጥረት ዜና መዋዕል ውስጥ፡ ለፈጠረው ፍጥረቱ ሲል፡ ራሱን፡ ቤዛ አድርጎ በማቅረብ፡ በመስቀል ላይ ሥጋውን ቆርሶና ደሙን አፍስሶ፡ ለመሥዋዕትነት የሰጠ፥ በዚህ፡ በፈጸመው ዘለዓለማዊ መድኃኒትነቱም፡ መላውን ፍጥረቱን፡ ከሰይጣን ገዢነት፥ ከኀጢአት ቀንበርና ከሞት ቅጣት ያዳነ መሪ፡ አንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

በቅዳሴ ጊዜ፡ ፈጣሪያችን፡ የየኀጢአታችንን ሥርየት ይሰጠን ዘንድ፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ ማለትም፡ በእውነት መንፈስ ኾነን፡ እየራሳችንንና ሌሎችን ይቅር ብለን፥ እርሱንም ከልባችን፡ ይቅርታን በመጠየቅ፡ በዙፋኑ አንጻር ወድቀን ከለመንነው በኋላ፡ ቅዱስ ቍርባኑን ለመቀበል፡ ወደማዕዱ ከመቅረባችን በፊት፡ ካህኑ፡ “በእውነት አምነው፡ ከእርሱ ለሚቀበሉ ኹሉ፡ ሕይወትና መድኃኒት፥ የኀጢአት ማስተስረያም ሊኾን የሚሰጥ፡ የአምላካችንና የመድኃኒታችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋ፡ ይህ ነው፤ ክቡር ደሙም ይህ ነው!” ብሎ ያውጃል።

# ምዕራፍ ፫፡ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ቍርባን።

### ስለቅዱስ ቍርባን የሚደረገው ሥርዓተ ቅዳሴ።

---

እኛም፡ "አዎን! እውነት ነው!" እያልን፡ አንድ ጊዜ፡ ለቅዱስ ሥጋው፡ አንድ ጊዜ ደግሞ፡ ለክቡር ደሙ፡ መላልሰን፡ የአዋጁን ቃል፡ በሃይማኖት እናረጋግጠዋለን።[፹፪]

እንዲህ አድርገን፡ በቃል ኪዳን የተቀበልነውን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ዛሬ፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋ እያለን፡ በልዩ መድኃኒትነቱ፡ ከነፍሳችንና ከሥጋችን ደዌያት ኹሉ ፈውሶ፡ በኃጢአት ማስተስረያነቱም፡ ከየኃጢአታችን፡ ፈጽሞ አንጽቶ፡ በሕይወት ሰጪነቱም፡ እነሆ፡ ሞት በሌለባት፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ለመኖር ያበቃናል።

#### ሞት ስለሌለባት የእግዚአብሔር መንግሥት።

ጥያቄ፦ *"ሞት የሌለባት የእግዚአብሔር መንግሥት"፡ ምንድር ናት? በየትስ ትገኛለች?*

መልስ፦ "ሰማይ"፡ ረቂቅ ኾኖ ይታያል እንጂ፡ እንደማይጨበጥ፡ እንደማይደረስበትም፡ እንዲሁ፡ የእግዚአብሔርም መንግሥት፡ በሰው ልቡና ውስጥ ሰፍና፡ በዓለሙም ኹሉ መልቶ የምትገኝ ስትኾን፡ የማትጨበጥ ረቂቅ በመኾኗ፡ *"መንግሥተ ሰማያት"* እየተባለች ስትጠራ ኖራለች። ይህች *"የእግዚአብሔር መንግሥት"* ብለን የምንኖርባት ሕይወት፡ ዛሬ፡ በመካከላችን ገዝፋ እንድትገኝ የተደረገበት የመለኮት ጥበብ የተፈጸመውና ጸጋው የተገኘው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ነው።

*"የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና፡ ንስሓ ግቡ!"* የሚለው፡ የአምላክ የአዋጅ ቃል የተነገረው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት፡ አብሣሪ በነበረው፡ በመጥምቁ ዮሓንስ ነበር፤ ኋላም፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ይህችኑ፡ "የእግዚአብሔር *መንግሥት*" የተባለችውን ረቂቅ *መንግሥቱን*፡ በመስቀሉ ዙፋን ላይ ኾኖ፡ በሠዋው ቅዱስ ሥጋውና ባፈሰሰው ክቡር ደሙ፡ በምድር ላይ፡ እንደገና አድሶና አግዝፎ እስኪገልጣት ድረስ፡ ይህንኑ የአዋጅ ቃል አሰምቷል። ሰይጣንን ድል አድርጎ፥ ኃጢአትን ደምስሶ፡ ሞትንም አጥፍቶ፥ በኃይልና በምስጋና፥ በመንግሥታዊም ሥልጣን ከተነሣ በኋላ ግን፡ "ሰማያዊት" ትባል የነበረችው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በምድር ላይ፡ እንደገና እንድትገለጥ፥ የማትታይና ረቂቅ የነበረችውም፡ ገዝፋ፡ እንደገና በግሃድ እንድትታይ አደረገ። የተገለጠችው፥ የታየችውም፡ በእርሱ በራሱ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህንም፡ *"የእግዚአብሔር መንግሥት፡ መቼ ትመጣለች?"* ብለው ለጠየቁት ተቃዋሚዎቹ፡ *"የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በመጠባበቅ አትመጣም፤ ደግሞም፡ 'እነኋት በዚህ፡ ወይም እነኋት በዚያ ናት!' አይሏትም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እነሆ፡ በመካከላችሁ ናትና!"* ብሎ በሰጠው ቃል አረጋግጦታል።[፹፫]

ስለዚህ፡ እግዚአብሔር፡ በዚች፡ የእርሱ በኾነችው መንግሥቱ፡ ልጆቹና ዜጎቹ ኾነን፡ እኒያ፡ የመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን፥ እንዲሁም፡ ዛሬ፡ እንደእነርሱ፡ እምቢተኞች የኾኑት መሰሎቻቸው ያጧትን፡ እውነተኛ የገነት ሕይወት፡ መልሰን እንድናገኛት ሊያበቃን፥ ለእያንዳንዳችንም፡ በዚህ ዓለም ወስኖ በሰጠን ዕድሜ፡ በብቻኝነት ኾነ በጋብቻ፡ በኅብረተሰብ ኾነ በሀገረሰብ ደረጃ፡ ፈጽሞ የሰላምና የጤና፥ የደስታና የብልጽግና ኑሮን እንድንኖር ሊያስችለን፡ በቸርነቱ የሰጠንን፡ የሥጋ ወደሙን ታላቅ ጸጋ፡ ያልኾነ ምክንያት እየፈጠርን፡ ወደቅዱሱ ቍርባን በመቅረብ ፋንታ፡ እንዳንርቅ፡ በመቀበል ፋንታ እንዳንተወው ልንጠነቀቅ ይገባናል።

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በያለንበት፡ ቅዳሴ እየተቀደሰ፡ በቍርባኑም ገበታ ዙርያ እየተሰበሰብን፡ የምንቀበለው ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ እንዲዘጋጅልን የሚያደርገው፡ እኛ የቃል ኪዳን ልጆቹ፡ ደካሞች ስለኾንን፡ በማሰብ፥ ወይም፡ በመናገር፡ ወይም፡ በማድረግ፡ ዘወትር ኃጢአት መፈጸማችን እንደማይቀር ስለሚያውቅ፡ ለዚህ ኃጢአታችን ማስተስረያ እንዲኾነን፥ ሥጋዊውና መንፈሳዊው ሕይወታችንም፡ ጭንቀት፥ ሥጋትና ፍርሃት የሌለበት፡ የሰላምና የደስታ እንዲኾንልን፥ እንዲሁም፡ በነፍሳችንና በሰውነታችን ሕመም ቢያገኘን፡ በፍቱን መድኃኒትነቱ እንድንፈወስ አስቦልን መኾኑን ልንዘነጋው አይገባም።

ሥጋ ለባሾች እንደመኾናችን፡ በዚህ ተፈጥሮአችን ምክንያት፡ ዘወትር፡ ስሕተተኞች መኾናችንን፡ እርሱ ፈጣሪያችን፡ ከእኛ የበለጠ ያውቃል። እርሱ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ሰው የኾነው፡ በእርሱ ቤዛነት፡ ከዚህ የስሕተት ጠንቅ እንድንድን ሊያደርግ መኾኑን፡ እኛም፡ እነሆ፡ በሃይማኖት አውቀናል። ስለዚህ፡ ነፍሳችን፡ ምድራዊ ከኾነው፡ ከዚህ ሥጋዊ፡ ደማዊ አካል እስክትለይ ድረስ፡ ምንጊዜም፡ ከኃጢአት ልንርቅና ፍጹም ንጹሓን ልንኾን አንችልም። በመንፈሳዊው ባሕርያችን፡ ከኃጢአት ንጹሓን የመኾን ፈቃድ ቢኖረንም፡ በሥጋዊው ተፈጥሮአችን ደግሞ፡ ኃጢአት የመሥራት ፍላጎት እንዳለብን፡ እየራሳችን፡ በየሰውነታችን ባሕርይ እናውቀዋለን። *"በነፍሴ፡ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛል፤ ነገር ግን፡ ከዚህ፡ ከነፍሴ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና ወደኃጢአት የሚማርከኝን ሌላ ሕግ፡ በሥጋዬ አያለሁ። እንግዲያስ፡ እኔ፡ በነፍሴ፡ ለእግዚአብሔር ሕግ፤ በሥጋዬ ግን፡ ለኃጢአት ሕግ የምገዛ ከኾንሁ፡ ምንኛ ጐስቋላ ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት፡ ማን ያድነኛል? በኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአምላካችን ያለው፡ የሕይወት መንፈስ ሕግ፡ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ፡ አርነት ስላወጣኝ፡ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይኹን!"*[፳፱] የሚለው የሐዋርያው ቃል፡ ይህን እውነታ ያረጋግጥልናል።

# ምዕራፍ ፫፡ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ቍርባን።

### ሞት ስለሌለባት የእግዚአብሔር መንግሥት።

---

ስለዚህ፡ ከኃጢአት ልንለይና ፍጹም ንጹሖች መኾን የምንችለው፡ በንስሓ ብቻ ነው። ንስሓም፡ በራስ ፍላጎትና እውቀት የተፈጸመውን ስሕተት፤ ጥፋት፥ በደል፡ ወይም፡ ኃጢአት፡ በእውነት አምኖ መጸጸትና ሰውን፡ ይቅር ማለት፡ ወይም፡ ሰውንና እግዚአብሔርን ይቅርታ መጠየቅ ሲኾን፡ ከዚህ አያይዞ፡ ሳይዘገዩ፡ የተሳሳቱትን አርሞ፥ ያጠፉትን አልምቶ፥ የበደሉትን ክሦ፤ የቀሙትን መልሶ፤ የሰጡትን ቃል ጠብቆ፥ የሠሩትንም ኃጢአት፡ በጾም፡ በጸሎትና በምጽዋት አስተሥርዮ፡ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መቀበል ነው።

ስለንስሓ ፍቱን መድኃኒትነትና ስለመምህረ ንስሓ ሥልጣን ክህነት።

ጥያቄ፡- *ስለንስሓ፡ በበለጠ አስፋፍተህ ብትገልጽልን?*

መልስ፡- ንስሓ፡ ሰው ኃጢአቱን አምኖ፡ የፈጣሪውን ይቅርታ፡ በእውነተኛ መንፈስ የሚጠይቅበት ምግባር መኾኑን፡ ቀደም ብዬ፡ በየቦታውና በየጋጣሚው አብራርቼላችኋለሁ። እርሱም፡ ከራስ መንጭቶ፡ በፈቃድ የሚፈጸም ሥርዓት መኾኑ ሊታወቅ ይገባል። ካህን፡ በቅርብ ካለ፡ ለዚህ ይረዳል። የሥጋ ሐኪም፡ ለሥጋዊ ሕመም፡ የበሽተኛው ምሥጢረኛና ጓደኛ፡ አማካሪና ረዳት፡ አካሚና አስታማሚ እንደኾነ ኹሉ፡ ካህኑም፡ ለኃጢአተኛው፡ እንዲሁ ነው። ኃጢአት፡ የነፍስ ደዌ፡ የነፍስ በሽታ ስለኾነ፡ ካህኑ፡ ለኃጢአተኛው፡ መንፈሳዊ አማካሪውና ረዳቱ፡ ምሥጢረኛ ጓደኛውና አጽናኙ ሲኾን፡ ሐኪሙ ግን፡ ራሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ መድኃኒቱም፡ እርሱ የሰጠው ሥጋውና ደሙ መኾኑን፡ ካህኑ፡ ለኃጢአተኛው እያብራራ፡ ምሥራቹን ይነግረዋል። የሰው ልጆች፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከእግዚአብሔር ያገኙት የይቅርታና የምሕረት ጸጋ፡ ወሰን የሌለው መኾኑን ያስረዳዋል።

እዚህ ላይ፡ እውነተኛውና ዘለዓለማዊው ካህናችን፥ ሐኪማችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ይህን በሚመለከት፡ የተናገራቸውን፡ እንዲህ የሚሉትን፡ ሕያዋን የምሥራች ቃላት፡ ካህኑ፡ ለኃጢአተኛው ይጠቅቅስለታል። *"ሐኪምና መድኃኒት የሚያስፈልጋቸው፡ ሕመምተኞች እንጂ፡ ጤነኞች አይደሉም፤ እኔም፡ ወደዚህ ዓለም፡ ሰው ኾኜ መጥቼ የተሠዋሁት፡ ኃጢአተኞችን ወደንስሓ ልጠራ እንጂ፡ ጻድቃንን ልጠራ አይደለም። ...እላችኋለሁ፡ ንስሓ ከማያስፈልጋቸው፡ ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ፡ ንስሓ በሚገባ፡ በአንድ ኃጢአተኛ፡ በሰማይ፡ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት፡ ደስታ ይኾናል።"*[፹፮]

ካህኑ፡ ከዚህ ጋር አያይዞ፡ *"ኃጢአት በሚሠረይባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን!"* የሚለውን ቃል፡ ዘወትር ከሚደገመው፡ የሃይማኖት ጸሎት ጠቅሶ፡ ስለዚሁ ምሥራች ያብራራለታል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ይኸውም፡ በዘር ሲያያዝ፡ ከዚያ ኃጢአተኛ ወላጆች ደርሶ፡ እርሱ በሥጋ ልደቱ፡ ከእነርሱ የወረሰው ኃጢአት፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ ኾኖ በተወለደባት፡ በዚያች፡ የክርስትና ጥምቀትና ዕለት የተደመሰሰለት መኾኑን ነው፡ ከዚያ በኋላ፡ በተለይም፡ ነፍስ ካወቀበት ጊዜ አንሥቶ፡ የሠራቸውን ኃጢአቶች ኹሉ ለማስወገድ የሚያስፈልገው፡ እውነተኛ ንስሓ ብቻ ስለኾነ፡ የኃጢአት ጠንቅ፡ በእርሱ ላይ፡ ምንም ዓይነት ሥልጣንና ኃይል የሌለው መኾኑን፡ አበክሮ፡ ለኃጢአተኛው ይነግረዋል፡፡

ሰው፡ በተፈጥሮው ምክንያት፡ አጥፊና ኃጢአተኛ መኾኑን የሚያውቀው ፈጣሪው እግዚአብሔር፡ ከእርሱ የሚጠይቀውና የሚጠብቀው ነገር ቢኖር፡ ከኃጢአት፡ ፍጹም ንጹሕ መኾንን ሳይኾን፡ በንስሓ መመለስን ስለኾነ፡ ከእርሱ፡ ከኃጢአተኛው የሚፈለገው፡ እውነተኛ ንስሓ ብቻ መኾኑን፡ ንስሓውንም ከፈጸመ በኋላ፡ ሥጋ ወደሙን በመቀበል፡ ያንን ኃጢአት እንዳልሠራ ኾኖ እንዲገኝ የሚያደርገው መኾኑን፡ ካህኑ፡ ለኃጢአተኛው ያስገነዝበዋል፡፡

በዚህ መሠረት፡ በብቸኝነት የምንኖር፡ ቢኀብቻ ተወስነን ያለን፡ ወይም፡ ወደፊት ተጋብተን ለመኖር የምንሻ፡ ለዓቅመ አዳምና ለዓቅመ ሔዋን የደረስን፡ ወንዶችም፡ ሴቶችም፡ ኹላችን፡ በንስሓ እየተመለስን፡ በየግላችን ኾነ በአንድነት፡ ሥጋውን ደሙን እየተቀበልን ልንኖር፡ ከዚህ ዓለም፡ በሥጋ ለምንለይበትም ኾነ፡ ሊቀ ካህናትና ንጉሠ ነገሥት ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለመጨረሻው ፍርድ፡ በዚህ ዓለም፡ እንደገና ለሚገለጥበት፡ ለዚያች ድንገተኛ ዕለትም፡ የበቃንና የተዘጋጀን ኾነን ልንጠብቅ ይገባናል፡፡

*ጥያቄ፡- "ንስሓ"ን በሚመለከት፡ ለካህን ስለተሰጠው ሥልጣን፡ ከዚህ ጋር አያይዘህ ብታብራራልን? በዚህ ረገድ፡ ሥጋዊና ዓለማዊ ለኾነ ሰው ቀርቶ፡ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ለኾነውም ተመልካች እንኳ ቢኾን፡ የሚከብዱና ግራ የሚያጋቡ፡ በግድም፡ በውድም፡ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው፡ አንዳንድ፡ የአስተሳሰብ አቋሞችና የድርጊት ኹኔታዎች ስላሉ፡ በእነዚህ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያን ለማግኘት ስንል፡ ይህን ጥያቄ ልናቀርብልህ ተገድደናል፡፡*

መልስ፡- እኔ ራሴ፡ እንደምእመንነቴ፡ ለራሴ፡ መምህረ ንስሓ ያስፈለገኝ፡ በሥልጣነ ክህነቴም፡ የመምህረ ንስሓነት ቀንበርን የተሸከምሁ በመኾኔ፡ በዚህ፡ ሥልጣነ ክህነቴ ምክንያት፡ በራሴና በሰው ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ በተለይ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ የቱን ያህል፡ የሚያስጠይቅ፡ ከባድ ኃላፊነት ያለበት መኾኑን ስለማውቀው፡ ንስሓንና መምህረ ንስሓን የሚመለከተውን፡ ይህን ጥያቄ በማንሣታችሁ፡ ደስ ብሎኛል፡፡ ይህን ዓቢይ ርእስ በሚመለከት፡ በመጀመሪያው ውይይታችን ጊዜ የተነጋገርንባቸውን ቊም ነገሮች እንድታስታውሷቸው እያሳሰብኋችሁ፡ ለእኹኑ ጥያቄያችሁ የምሰጣችሁን፡ ከዚያ የቀረ መልስ፡ እንደሚከተለው፡ በሦስት ክፍሎች መድቤ አቅርቤላችኋለሁ፡፡

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ቍርባን።

### ስለንስሓ ፍቱን መድኃኒትነትና ስለመምህረ ንስሓ ሥልጣነ ክህነት።

---

፩ኛ፡ የሰዎች ክህነት፡ ለፍጹምነት በቅቶ የተገኘ ቢኾን ኖሮ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በሰውነት መገለጥ፡ ከዚያም፡ "ተራ ካህን" እና "ሊቀ ካህናት" መኾን ባላስፈለገው ነበር፡ ነገር ግን፡ በመልኩ የፈጠረው ሰው፡ ከእርሱ ጋር፡ በእውነትና በመንፈስ አምልኮ እንዲገናኝበት፡ ገና፡ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ ለሰጠው የክህነት ባለአደራነት የበቃ ሰብአዊ ፍጡር፡ አንድ እንኳ ባለመገኘቱ፡ በሰዎች ክፋት፡ በሥጋ ተፈጥሮና በዲያብሎስ አበጋዝነት ምክንያት፡ አዳምና ሔዋን፡ ልጆቻቸውም አጥተውት የነበረውን፡ የተራ ካህንነትንና የሊቀ ካህንነትን ሥልጣን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰውነቱ፡ መልሶ ለራሱ አድርጎታል፡ ሰዎችም፡ በዚህ ጸጋው እንዲጠቀሙበት፡ አስችሏቸዋል።

ይህንም፡ *"እውነት፡ እውነት እላችኋለሁ፡ እኔ፡ የበጎች በር ነኝ፡ በእኔ የሚገባ ቢኖር፡ ይድናል፡ ይገባልም፡ ይወጣልም፡ መሰማርያም ያገኛል። ከእኔ በፊት የመጡ ኹሉ፡ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው፡ ዳሩ ግን፡ በጎቹ አልሰሟቸውም፡ ሌባው፡ ሊሰርቅና ሊያርድ፡ ሊያጠፋም እንጂ፡ ስለሌላ አይመጣም። እኔ፡ ሕይወት እንዲኾንላቸው፡ እንዲበዛላቸውም መጣሁ። መልካም እረኛ፡ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ፡ ነፍሱን፡ ስለበጎቹ ያኖራል። እረኛ ያልኾነው፡ በጎቹም፡ የእርሱ ያልኾኑ፡ ሞያተኛ ግን፡ ተኵላ ሲመጣ ባየ ጊዜ፡ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፡ ተኵላም ይነጥቃቸዋል፡ በጎቹንም ይበትናቸዋል፡ ሞያተኛ ስለኾነ፡ ለበጎቹም ስለማይገደው፡ ሞያተኛው ይሸሻል።"* ባለው ቃሉ አረጋግጦታል።

በሰዎች ዘንድ የነበረው፡ የክህነት ሥልጣን፡ የተዳረገበት የሙስና ውርደት፡ ከመጨረሻው ዝቅጠት ደርሶ፡ ፍጹም ከመደምሰስ ሊድን የቻለው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ሰው ኾኖ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በፈጸመው ቤዛነቱ መኾኑ፡ ከቶ አይታበልም። ይህ እውነታ፡ በዘመኑ የነበሩት፡ ካህናትና ሊቃነ ካህናት፡ በእርሱ ላይ በፈጸሙት ግፍ፡ በማያሻማ መልኩ፡ ገሃድ ወጥቷል። ይህንም፡ ሊቀ ሐዋርያት ጴጥሮስ፡ መንፈስ ቅዱስን ተመልቶ፡ እንዲህ ሲል በተናገረው ቃሉ፡ ግልጽ አድርጎታል፦ *"የእሥራኤል ሰዎች ሆይ! ይህን ነገር ስሙ! ራሳችሁ እንዲያችሁት፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ፡ እግዚአብሔር፡ በመካከላችሁ፡ በእርሱ እጅ ባደረገው፡ በኃይሉ ነቱና በተአምራቱ፡ በድንቅ ሥራዎቹም፡ እግዚአብሔር፡ ለእናንተ የገለጠላችሁ ሰው ነው፡ እርሱንም፡ እግዚአብሔር አውቆ መክሮ፡ በሠራው ሥርዓት፡ እናንተ፡ ለዓመፀኞች አሳልፋችሁ ሰጣችሁት፡ ሰቀላችሁት፡ ገደላችሁትም። እግዚአብሔር ግን፡ የሞትን ማሠሪያ ፈትቶ፡ ከሙታን ለይቶ አስነሣው፡ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና።"*

ከዚህ ንግግር የተነሣ፡ እኒህ የአይሁድ ካህናትና ሊቃነ ካህናት፡ እጅግ ተቈጥተው፡ ጴጥሮስንና ሐዋርያትን፡ ሊገድሏቸው አስበው፡ እያስፈራሩ በጠየቋቸው ጊዜ፡ የሰጧቸው፡ እንዲህ የሚለው መልሳቸው፡ የቀደመውን፡ የሊቀ ሐዋርያቱን ቃል ያጠናክረዋል፦

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

*"ከሰው ይልቅ፡ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባናል፡ እናንተ ክዳችሁ፡ በእንጨትም ላይ ሰቅላችሁ የገደላችሁትን፡ ኢየሱስን፡ የአባቶቻችን አምላክ አስነሣው፡ እግዚአብሔር፡ ለእሥራኤል፡ ንስሓን፡ ለኃጢአታቸውም ሥርየትን ይሰጥ ዘንድ፡ እርሱን፡ የሕይወት ራስም፡ መድኃኒትም አደረገው፡ በቀኙም አስቀመጠው፡፡ እኛም፡ ለዚህ ነገር፡ ምስክሮች ነን፡ ደግሞም፡*[፹፯] *እግዚአብሔር፡ ለሚየምኑበት የሰጠው መንፈስ ቅዱስም ምስክር ነው፡፡"*

"የእግዚአብሔር ሥልጣን ክህነት"፡ እስከዚያን ዘመን ድረስ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ከብራና ተጠብቃ መኖርዋን ቀጥላለች፡ "እሥራኤላውያን ነን!" በሚሉ፡ በእኒህ ወገኖች ዘንድ ግን፡ እንዲያ ተዋርዳና ማስና እንደነበረ፡ ከእዚህ የበለጠ ምስክርነት አያስፈልግም፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ተጻራሪ የኾነው ዲያብሎስ፡ ከጥንት ጀምሮ፡ ሊያጠፋት ዐቅዶ፡ ሲጥርበት የኖረበት ሥውር መንገዱ፡ በእነዚያ አገልጋዮቹ መሣሪያነት በመጠቀም መኾኑ፡ የኹሉም ሥራ፡ ኹሉንም ስላጋለጠ፡ የምስክሮቹ እውነተኛነት፡ ከቶ አያጠያይቅም፡፡ እንግዲህ፡ ያችን "የእግዚአብሔር ሥልጣን ክህነት"፡ ያን ከመሰለ ጠላት ተቤዥቶ የታደጋትን፡ እውነተኛውንና ዘለዓለማዊዉን ካህንና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ነው፡ እኒያ፡ የአይሁድ ካህናትና ሊቃነ ካህናት፡ ያን በመሰለ ግፍና ጭካኔ፡ የመስቀል ሞት ፍርድን በይነውበት፡ እንዲገደል ያደረጉት፡፡

ከዚያ ክፉ ድርጊታቸው በፊት ግን፡ ለዚያ መሠሪ ዓላማቸው አፈጻጸም የሚረዳቸውን ማስረጃ ለመሰብሰብ፡ በእርሱ፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ፡ በረቂቅ ተንኰል የዘረጉት፡ የተለያየ አያሌ ወጥመድ እንደነበራቸው ይታወሳል፡ ያም ወጥመድ፡ በየጊዜያቱና በየቦታው፡ በየምክንያቱም፡ ለፈተና ያቀርቡለት የነበረው የጥያቄ ማዕበል ነበር፡ ከእነዚያ ጥያቄዎች መካከል፡ የመጨረሻዋ ለኾነችው ጥያቄያቸው፡ መልስ ይኾናቸው ዘንድ፡ በበኩሉ ያቀረበላቸው፡ እንዲህ የሚል ጥያቄን ነበር፦ *""ስለክርስቶስ፡ ምን ትላላችሁ? የማን ልጅ ነው?" እነርሱም፡ "የዳዊት ልጅ ነው፡" አሉት፡፡ ጌታችን ኢየሱስም፡ እንዲህ አላቸው፤ "እንግዲያ፡ እርሱ ራሱ ዳዊት፡ መንፈስ ቅዱስን ተመልቶ፡ 'ጌታ [እግዚአብሔር አብ]፡ ጌታዬን [እግዚአብሔር ወልድን]፡ ጠላቶችህን፡ ከእግርህ በታች እስከጥላቸው ድረስ፡ በቀኜ ተቀመጥ አለው፡' ለምን አለ? እንግዴህ፡ እርሱ ራሱ ዳዊት፡ 'ጌታዬ!' ያለው፡ እርሱ፡ እንግዲያ፡ ለእርሱ፡ እንዴት ልጁ ይኾነዋል?""* ለዚህ፡ ለጌታችን ጥያቄ፡ መደምደሚያ ይኾን ዘንድ፡ ወንጌላዊው የጻፈው ቃል፡ *"ከዚች ቀን ጀምሮ፡ አንዲትም ቃል*[፹፰] *ሊመልስለት የቻለ፡ ምንም ሊጠይቀውም የደፈረ የለም!"* የሚል ነው፡፡

## ምዕራፍ ፫፡ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::
### ምሥጢረ ቍርባን::
### ስለንስሓ ፍቱን መድኃኒትነትና ስለመምህረ ንስሓ ሥልጣነ ክህነት::

---

እኒህ የአይሁድ ካህናትና ሊቃነ ካህናት፡ ምሁራንና ሊቃውንት፡ "የእኛ፡ ብቸኛ ይዞታችን ነው!" ብለው ይመጻደቁበትና በአሕዛብ ዘንድ ለግብዝነት ተግዳሮት ዳርገውት ስለነበረው፡ "የእግዚአብሔር ሥልጣነ ክህነት"፡ ወንጌላዊው፡ *"ከዚህ በኋላ፡ ጌታችን ኢየሱስ፡ ለሕዝቡና ለደቀ መዛሙርቱ፡ እንዲህ ብሎ ነገራቸው፡"* በሚል መግቢያ የሚጀምረውን፡ ራሱ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመለኮታዊ አንደበቱ፡ የሠነዘራቸውን ተግሣፆችና ዘለፋዎች፡ እስኪ፡ በዛሬዎቹ፡ የኢትዮጵያ ትውልድ ካህናትና ሊቃነ ካህናት፡ ምሁራንና ሊቃውንት እየተፈጸመ ካለው ድርጊት ጋር እያነጻጸርንና እየመዘዘንን፡ በእውነተኛው የሕሊና ጆሮአችን እንስማው!? በእውነተኛው የሕሊና ዓይናችንም፡ እስኪ እንመልከተው!?

*"ጻፎችና ፈሪሳውያን፡ በሙሴ መንበር ላይ ተቀምጠዋል፡ ያስተማሩአችሁን ኹሉ አድርጉ! ጠብቁም! የሚያስተምሩትን፡ ራሳቸው አይሠሩትምና፡ እንደሚሠሩት ግን፡ አትሥሩ! ትልቅና ከባድ ሸክም አሥረው፡ ሰውን፡ በጫንቃው ላይ ያሸክሙታል፡ እነርሱ ግን፡ በጣታቸው ስንኳ፡ አይነኩትም:: የሚሠሩትን ሥራቸውን ኹሉ፡ ለሰው ይምሰል ይሠሩታል፡ የቀሚሳቸውን እጅጌ፡ ያሰፋሉ፡ የልብሳቸውንም ዘርፍ፡ ያስረዝማሉ:: በማዕድ ጊዜ፡ እላይ ባለው የገበታ ወንበር መቀመጥን ይመርጣሉ፡ በአደባባይም ፊት ለፊት መቀመጥን ይወድዳሉ:: ሰው ኹሉ፡ በገበያ፡ 'መምህራን!' እያለ፡ እጅ ይነሳቸው ዘንድ ይወድዳሉ::*

*"እናንተስ፡ በምድር ላይ፡ 'መምህራን!' አትባሉ! መምህራችሁ፡ አንድ ነውና፡ እርሱም፡ ክርስቶስ ነው:: እናንተስ፡ ኹላችሁ፡ ወንድማማች ናችሁ:: በምድር ላይም፡ አባት አታድርጉ! የሰማዩ አባታችሁ፡ አንድ ነውና:: በምድር ላይ፡ ጌታ አታድርጉ! ጌታችሁ፡ አንድ ነውና፡ እርሱም፡ ክርስቶስ ነው:: ነገር ግን፡ ከእናንተ የሚበልጠው፡ አገልጋይ ይኹናችሁ! ራሱን፡ ከፍ ከፍ ያደረገ፡ ይዋረዳልና፡ ራሱን ዝቅ ዝቅ ያደረገ ይከብራልና::*

*"እናንተ ግብዞች! ጻፎችና ፈሪሳውያን! ወዮላችሁ! አብዝቶ መጸለይን፡ ምክንያት አድርጋችሁ፡ የድኾችን ገንዘብ ትበላላችሁና፡ ስለዚህም፡ ጽኑ ፍርድን ትቀበላላችሁ::*

*"እናንተ ግብዞች! ጻፎችና ፈሪሳውያን! ወዮላችሁ! ሰው፡ ወደመንግሥተ ሰማያት እንዳይገባ፡ ትዘጉበታላችሁና፡ እናንተም አትገቡም፡ የሚገቡትንም፡ ከመግባት ትከለክሏቸዋላችሁ::*

*"እናንተ ግብዞች! ጻፎችና ፈሪሳውያን! ወዮላችሁ! አንድ መጻተኛን ለማጥመቅ፡ ባሕሩን፡ የብሱን ትዞራላችሁና፡ ከተጠመቀም በኋላ፡ ለገሃነም፡ የእናንተ ተከታይ ታደርጉታላችሁ::*

*"እናንተ የዕውራን መሪዎች! "በቤተ መቅደስ የማለ፡* [መሓላውን ባይፈጽም]፡ *ኃጢአት የለበትም፡ በቤተ መቅደስ ወርቅ የማለ ግን፡* [መሓላውን ባይፈጽም]፡ *ኃጢአት ይኾንበታል!"* የምትሉ፡ *ጻፎችና ፈሪሳውያን! ወዮላችሁ!*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡

## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

"እናንተ አላዋቂዎችና ዕውሮች! የትኛው ይበልጣል? ወርቅ ነውን? ወይስ፡ ቤተ መቅደስ? ወርቅን የሚቀድሰው፡ ቤተ መቅደስ አይደለምን? "በመሠዊያው የማለ፡ [መሐላውን ባይፈጽም]፡ በደል አይኾንበትም፡ በመሠዊያው ላይ ባለው፡ በመሥዋዕቱ የማለ ግን፡ [መሐላውን ባይፈጽም]፡ በደል ይኾንበታል!" ትላላችሁ፡ እናንተ አላዋቆችና ዕውሮች! የትኛው ይበልጣል? መሥዋዕቱ ነውን? ወይንስ መሠዊያው? መሥዋዕቱን የሚቀድሰው፡ መሠዊያው አይደለምን? በመሠዊያው የማለ፡ በእርሱና በላዩ ባለውም ኹሉ ማለ። በቤተ መቅደስም የማለ፡ በቤተ መቅደስና በውስጡ ባለውም ኹሉ ማለ። በሰማይ የማለ፡ በእግዚአብሔር ዙፋን ማለ፡ በላዩ በተቀመጠውም ማለ።

"እናንተ ግብዞች! ጻፎችና ፈሪሳውያን! ወዮላችሁ! ከአዝሙድና ከሴናዳም፡ ከከሙንና ከእንስላል፡ ዐሥራትን አውጥታችሁ የምትቀበሉ! ታላላቁን የኦሪትን ትእዛዛት፡ ፍርድንና እውነትን፡ ምጽዋትንና ሃይማኖትንም የምትተዉ! ይህን ልታደርጉት፡ ያንንም ሳትተዉ ይገባል። እናንተ የዕውራን መሪዎች! ትንኝን የምታጠሩ! ግመልንም የምትውጡ!

"እናንተ ግብዞች! ጻፎችና ፈሪሳውያን! ወዮላችሁ! የጽዋዉንና የጻሕሉን ውጭዉን የምታጥቡ! ውስጡ ግን፡ ቅሚያንና ዓመፅን፡ ንጥቂያንም የተመላ ነው። አንተ ዕውር ፈሪሳዊ! ውጭው፡ ንጹሕ ይኾን ዘንድ፡ አስቀድመህ፡ ጽዋውንም፡ ጻሕሉንም፡ ውስጡን እጠበው!

"እናንተ፡ የተለሰኑ መቃብሮችን የምትመስሉ፡ ግብዞች! ጻፎችና ፈሪሳውያን! ወዮላችሁ! መቃብሮቹ፡ በውጫቸው፡ አምረው የሚታዩ፤ በውስጣቸው ግን፡ አጥንትንና ርኵስ ነገርን ኹሉ፡ የተመሉ ናቸው። እንዲሁ፡ እናንተም፡ በውጭ፡ ለሰው ይምሰል፡ እውነተኞች ትመስላላችሁ፤ በውስጣችሁ ግን፡ ዓመፅንና ቅሚያን፡ አድልዎንም የተሞላችሁ ናችሁ።

"እናንተ፡ የነቢያትን መቃብር የምትሠሩ፡ የጻድቃንንም መታሰቢያ የምታስጌጡ፡ ግብዞች! ጻፎችና ፈሪሳውያን! ወዮላችሁ! "በአባቶቻችን ዘመን ኖረን ቢኾን፡ ነቢያትን ልንገድል፡ ከእነርሱ ጋር ባልተባበርን ነበር፡" ትላላችሁ።

"እነሆ፡ የነቢያት ገዳዮች ልጆች እንደኾናችሁ፡ እናንተ ራሳችሁ ታምናላችሁ። እናንተም፡ የአባቶቻችሁን መሥፈሪያ ሙሉ! እናንተ፡ ዕፉኝቶች! የምድር እባቦች ልጆች! ከገሃነም ፍርድ ልታመልጡ፡ እንዴት ትችላላችሁ?

"ስለዚህ፡ እነሆ፡ እኔ፡ ነቢያትንና ሐዋርያትን፡ ጥበበኞችንና ጸሐፊዎችን፡ ወደእናንተ እልካለሁ፤ ከእነርሱም መካከል፡ ትገድላላችሁ፤ ትሰቅላላችሁ፤ በምኵራባችሁም፡ ትገርፋላችሁ፤ ከአገር ወደአገርም ታሳድዷቸዋላችሁ። ይህንም የምታደርጉት፡ ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ፡ በቤተ መቅደስና በመሠዊያው መካከል እስከገደላችሁት፡ እስከበራክዩ ልጅ፡ እስከዘካርያስ ደም ድረስ፡ በዓለም የፈሰሰው፡ የጻድቃን ኹሉ ደም፡ በእናንተ ላይ ይደርስ ዘንድ ነው። እውነት እላችኋለሁ! ይህ ኹሉ፡ በዚች ትውልድ ላይ ይደርስባታል።

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::

## ምሥጢረ ቍርባን::

### ስለንስሓ ፍቱን መድኃኒትነትና ስለመምህረ ንስሓ ሥልጣነ ክህነት::

---

*"ኢየሩሳሌም! ኢየሩሳሌም! ነቢያትን የምትገድል! ወደእርሷ የተላኩትን ሐዋርያትንም የምትወግር! ዶሮ: ጫጩቶቿን: በክንፎቿ ጉያ እንደምትሰበስብ: ልጆችሽን ልሰበስብ: የቱን ያህል ወደድሁ?! እናንተ ግን: "እንቢ!" አላችሁ:: ስለዚህ: እነሆ! ቤታችሁ: ምድረ በዳ ኾኖ ይቀርላችኋል:: እውነት እላችኋለሁ! "በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ: ቡሩክ ነው!" እስከምትሉበት ጊዜ ድረስ: ከዛሬ ጀምሮ አታዩኝም::"* [፹፱]

፪ኛ: የንስሓና የመምህረ ንስሓ: የሥልጣነ ክህነትም ነገር: ምንን እንደሚመስል: ከዚህ ጋር የተያያዘ: አንድ ሐተታን: እስኪ: በመጠኑም ቢኾን ላቅርብላችሁ! ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ከለምጹ ደዌ: ነጻ አድርጎ ለፈወሰው ሕመምተኛ: የተናገረውን ቃል: ከወንጌል በመጥቀስ: ምእመን የኾነ ኹሉ: ኃጢአቱን: ለመምህረ ንስሓው ካህን ካልነገረ በቀር: ሊሠረይለት እንደማይቻል ተደርጎ የሚታመንበትና የሚሠራበት ጠንካራ ይትበሃል እንዳለ የምታውቁ ይመስለኛል፤ ለዚህ ይትበሃል ማስረጃ ኾኖ የሚጠቀሰውም: *"እነሆ: ለምጻም ቀርቦ: 'ጌታ ሆይ! ብትወድስ: ልታነጻኝ ትችላለህ' እያለ ሰገደለት:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም: እጁን ዘርግቶ ዳሰሰውና: 'እወድዳለሁ፣ ንጻ!' አለው:: ለምጻሙም: ወዲያው: ከለምጹ ነጻ:: ጌታችንም: 'ለማንም እንዳትናገር: ተጠንቀቅ! ነገር ግን: ኺደህ: ራስህን ለካህን አሳይ! ለእነርሱም: ምስክር እንዲኾን: ሙሴ ያዘዘውን መባ አቅርብ!' አለው::"* የሚለው ቃልና ለእርሱ የተሰጠው ያልተስተካከለ ትርጓሜ ነው:: [፺]

*ጥያቄ:- ጌታችን: ለምጻሙን: 'ለማንም እንዳትናገር: ተጠንቀቅ!" ያለው ነገር ምን እንደኾን ብትተረጉምልን?*

መልስ:- በመሠረቱ: "ለምጽ": ደዌ፥ ወይም: በሽታ እንጂ: ኃጢአት አለመኾኑን የሚያረጋግጠው የኦሪቱ ሕግ: የወለደችን ሴት: "ርኵሲት"፥ ራሱን "መውለድ"ንም ሳይቀር: "ርኵሰት" ያደርግ እንደነበረ ኹሉ: የለምጽ ደዌ የያዘውንም ሰው: እንዲሁ: "ርኵስ" ብሎ: ከኅብረተሰቡ እንዲገለል ደንግጎ: በዚሁ መልክ ሲሠራበት እንደነበረ ይታወቃል::

እንደዚያ ባይኾን ኖሮ: የብሉዩም፥ የአዲሱም ኪዳናት ጌታ: እርሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: በኃጢአት ምክንያት ታምመው የሚሠቃዩ ሌሎች በሽተኞችን በሚፈውስበት ጊዜያት ኹሉ: ለእያንዳንዳቸው: "ኃጢአትህ ተሰረየልህ!" ይል እንደነበረው: ለዚህም ለምጻም: ይህን የመሰለውን ቃል ተናግሮ ባሰናበተው ነበር:: ነገር ግን: የኾነው: ይህ አልነበረም:: [፺፩]

ጌታችን: ኢየሱስ ክርስቶስ: ለዚያ: እንዲፈውሰው ጠይቆት ላዳነው ለምጻም የተናገረው: የዚህ ቃሉ: እውነተኛውና ትክክለኛው ትርጓሜ: ምንን እንደሚመስል ትገነዘቡት ዘንድ፥ የእግዚአብሔርን መንፈስ በተመላ: እውነተኛ ልቦናም ኾናችሁ ትመለከቱት ዘንድ: ከራሱ: ከተፈወሰው ለምጻም እንደበት ሊሰሰማ የሚችለውን መልእክት: እንደሚከተለው: አቅርቤላችኋለሁ:-

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

*“ኃጢአቴንና በደሌን፡ ጥፋቴንም፡ እንድናዘዝለት የሚጠየቀኝ፥ ነገር ግን፡ በልቤ ውስጥ ሠውሬ ከያዝኳቸው፡ ከእነዚያ ኹሉ ምሥጢሮቼ መካከል፡ አንዱንም እንኳ ሳልነግረው፡ ኹሉን፡ አስቀድሞ አውቆና እኔ ራሴ፡ ኃጢአቴን አምኜ፡ ለመዳን፡ በእውነት መፈለጌን ብቻ አይቶ፡ ይቅርታውን ያደረገልኝ እርሱ፡ እንዲህ አለኝ፡-*

*“'ከዚህ የለምጽ ደዌ የፈወሰኝ፡ ቸሩ እግዚአብሔር ነው' በል እንጂ፡ 'የፈወሰኝ፡ ኢየሱስ ነው!' ብለህ፡ ለካህኑ ካልኾነ በቀር፡ ለሌላ ለማንም ሰው እንዳትናገር፡ ተጠንቀቅ! ይህም ሊኾን የተገባው፡ በእውነተኛው ማንነቴ የምገለጥበት ጊዜ፡ ገና ስላልደረሰ ነው፡፡ ሊምጻም እንደነበርህ ለሚያውቅህ፡ ለዚያ ካህንም፡ ይህን ፈውስ ያገኘኸው፡ ከእውነተኛው ካህን፡ ከእኔ መኾኑን፡ ምሥጢሩን፡ ገልጠህ ንገረው! በኦሪቱም ሕግ መሠረት፡ የተፈወሰውን ገላህን አሳየውና ከለምጹ ደዌ የነጻህ መኾንህን፡ እንደሕጉ ሥርዓት ያረጋግጥልህ!*

*“'እኔ እግዚአብሔር ወልድ፡ ወደዚህ ዓለም መጥቼ፡ ሰው የኾንሁት፡ ኦሪትንና ነቢያትን፡ ላጸናቸውና ልፈጽማቸው እንጂ፡ ልሽራቸው አለመኾኑን፡ እርሱ፡ ራሱ፡ ካህኑና የሚቃወሙኝ አይሁድ፡ ለእየራሳቸው፡ በትክክልና በገሃድ አረጋግጠው ያውቁ ዘንድ፥ በእግዚአብሔርና በሰውም ፊት፡ ምስክር ይኾንባቸው ዘንድ፡ ስለዚሁ ስለደዌህ ፈውስ፡ ሙሴ ያዘዘውን ቍርባን፡ ይዘህ ወስደህ፡ ለእግዚአብሔር እንዲያቀርብልህ፡ ለካህኑ ስጠው!”*

### ራስን ለካህን የማሳየት ትርጓሜ፡፡

ጥያቄ፡- *ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ “ራስህን ለካህን አሳይ!” ስላለው ቃሉና ዛሬ፡ እኛ፡ በዚህ ረገድ ልንፈጽመው ስለሚገባን ተግባር፡ ገላልጸህ ብትነግረን፡ በጣሙን ይረዳናል!*

መልስ፡- *“ራስህን ለካህን አሳይ!”* የሚለው መለኮታዊ ትእዛዝ፡ ይህን፡ አኹን የሰማችሁትን፡ ቀጥተኛ ትርጉም ያለውን መልእክት የያዘ ነው፡፡ ይኸውም፡ እንደኦሪቱ ሕግ፡ ከደዌው መፈወሱን ለማረጋገጥ፡ ለምጻሙ፡ የተፈወሰ ገላውን፡ ለካህኑ፡ ገላልጦ እንዲያሳይና ካህኑም፡ ያ ሕመምተኛ፡ ከለምጽ ደዌው መዳኑን አይቶ፡ ተገቢውን የመንጻት ቁርባን ወደእግዚአብሔር እንዲያቀርብለት የሚያስገነዝብ መኾኑ ነው፡፡

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::
## ምሥጢረ ቍርባን::
### ራስን ለካህን የማሳየት ትርጓሜ::

---

የአዲስ ኪዳኑ ምእመን: ራሱ: በፈቃዱ ፈልጎ ካልኾነ በቀር: “የሠራኸውን ኃጢአት ኹሉ: በግድ: ለእኔ ካልተናዘዝህልኝ: ሥርየትን አታገኝም!” የሚለውን: ሰዎች: ለግል ሥልጣናቸውና ክብራቸው፥ ጥቅማቸውም ሲሉ የሚኼኑበት: የሕግ ሸክም ቢኖር: ለዚያ ግዳጅ: ምክንያትና ማጽኛ ኾኖ ሊጠቀስ አይገባውም::

አለዚያማ: ቀደም ብዬ እንደጠቀስሁላችሁ: እንደምሥራቹ ቃል: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: በአዲስ ኪዳን ደሙ: ከኃጢአት አንጽቶ: ሥርየትን ያስገኘለትንና በዚያ: በኦሪቱ የቀንበር ሸክም ምክንያት: የተዳከመው: ያን: የቀድሞውን ሰው: እንደገና: ለሕገ ኦሪቱ ቀንበር በመዳረግ: የንስሓ ፍሬን ሊያፈራ ወደተሣነው: ወደደረቀው የበለስ ዛፍነት እንዲመለስ ማስገደድ ይኾናል:: ስለዚህ: *“ራስህን ለካህን አሳይ!”* ማለት: “ከለምጹ ደዌ: ፈጽመህ የዳንህ መኾንህን አይቶ: ንጽሕናህን ያረጋግጥልህ ዘንድ: እንደኦሪቱ ሥርዓት: ወደ ካህኑ ኺደህ: ሰውነትህን ገልጠህ አሳየው!” ማለት መኾኑ: በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት: የተረጋገጠ መኾኑ: እንዲህ በግልጽ ተነብቦ እየታወቀ: የኦሪቱን የቅጣት ሕግ: አለቦታው: ለአዲሱ የምሕረት ኪዳን በመጥቀስ: ያውም: አለአገባብ በመተርጐም: “‘ኃጢአትህን ለካህን ንገር!’ ማለት ነው፡” ብሎ ለማሳመን መሞከር ተገቢ አለመኾኑን: ልትረዱት ይገባል::

እንዲያማ ካልኾነ: ቀደም ብሎ የተነገረውን: የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል ማስተሓቀርና እርሱ: ሰው ኾኖ የፈጸመውን ቤዛነቱን: ከንቱ ማድረግ ሊኾን አይደለምን? ለዚያውስ ደግሞ: የትኛው ሰብአዊ ካህን ነው: ምእመኑ: ኃጢአቱን በሙሉ የተናዘዘለት መኾኑን ፈጽሞ አረጋግጦ: ተገቢውን ንስሓ ከሰጠው በኋላ: “አኹን: እንግዴህ: ለሥጋ ወደሙ በቅተሃልና: መቀበል ትችላለህ!” ብሎ: የመጨረሻውን የፈቃድ ማኅተም አስይዞ: ወደቅዱሱ ቍርባን ሊያቀርበው የሚችለው? በራሱ ብቅዓት ተማምኖና ይህን ኃላፊነት ወስዶ: ለምእመኑ: የፈቃድ ቃሉን ሊሰጠው የሚችል: ሥጋ ለባሽ ካህን ከቶ ይኖራልን? አይኖርም::

ምእመኑም ቢኾን: ካህኑ: እንደእርሱ: ደካማ ፍጡር መኾኑን ስለሚያውቅ: ኃጢአቱንና በደሉን፥ ጥፋቱንም ኹሉ: ጨርሶ ሊናዘዝለት አይፈልግም:: ታዲያ! ኃጢአቱንና በደሉን፥ ጥፋቱንም ኹሉ: ከካህኑ ሸሽጎ ያስቀረው ምእመን: ምንም: “ለቅዱሱ ቍርባን ያበቃዋል!” ብሎ: መምህረ ንስሓው: ባለማወቅ: ያልተሟላ ቀኖናን ቢሰጠው፥ ያም ምእመን: በዚህ መልክ የተሰጠውን ቀኖና ቢፈጽም እንኳ: ለእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ንስሓ: እንደምን ሊበቃ ይቻለዋል? በዚህ ኹኔታስ: ራሱ: ምእመኑም ቢኾን: “በቅቻለሁ!” ብሎ: እንደምን: የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ሊቀበል ይደፍራል? ሊደፍር አይገባውም::

እንዲህ ከኾነ: እግዚአብሔር ወልድ: ራሱ ሰው ኾኖ: በራሱ መሥዋዕትነት: የቤዛነት ካሣን ከከፈለ በኋላ: የካህኑንና የሊቀ ካህናትነቱን ሥልጣን: ለራሱ መያዝ ያስፈለገው: ለምን እንደኾነ: ምክንያቱ: እነሆ: “ታወቀ! ተረዳ!” ማለት ነው::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ይህም ምክንያት፡ በምእመኑም ኾነ በካህኑ፡ በኹለቱም በኩል ያለውን፡ ይህን የመሰለውን ድክመትና ጉድለት ለማስወገድ መኾኑ፡ በገሃድ ስለሚታይ፡ በማኅናቸውም ጤናማ ሰብአዊ ሕሊና ዘንድ፡ በቀላሉ ሊታመንበት እንደሚቻል መገመት አያዳግትም። እንዲህ ካልኾነ ግን፡ ራሱ፡ ሰብአዊው ፍጡር፡ የተደረገለትን የመለኮት ቸርነትና የተሰጠውን የንስሓ ጸጋ፡ ለከንቱነት ዳረገው ማለት ይኾናል።

ይህን ኹሉ እውነታ፡ እኔ፡ ራሴ፡ ካህን በመኾኔና የክህነቱን ቅርስ፡ ከረዥሙ የትውልድ ሐረግ፡ በውርስ በማግኘቴ፡ በካህን ቤተሰብ ውስጥ ተወልጄ በማደጌም፡ ይልቁንም፡ "ለራሴና ለቤተሰቤ፡ ጠባቂ ይኾኑኛል!" ብዬ፡ በመምህረ ንስሓነት ከያዝኳቸው ካህን ጀምሮ፡ በክህነት አገልግሎቴ አካባቢ፡ እስከ አገር አቀፍ ደረጃ ባሳለፍሁት ዘመን፡ ካጋጠሙኝ ኹኔታዎችና ድርጊቶች ስላረጋገጥሁት፡ በቅዱሳት መጻሕፍቱ ቃላት እሙንነት እደነቃለሁ።

በዚህ አንጻር፡ ኢትዮጵያዊው መምህረ ንስሓ፡ *"እኔ ኀጢአተኛውን፡ 'በእርግጥ ትሞታለህ!' ባልሁት ጊዜ፡ አንተም፡ ባታስጠነቅቀው፡ ነፍሱም እንድትድን፡ ከክፉ መንገዱ ይመለስ ዘንድ፡ ለኀጢአተኛው አስጠንቅቀህ ባትነግረው፡ ያ ኀጢአተኛ፡ በኀጢአት ይሞታል፤ ደሙን ግን፡ ከእጅህ እፈልጋለሁ። ነገር ግን፡ አንተ፡ ኀጢአተኛውን ብታስጠነቅቅ፥ እርሱም፡ ከኀጢአቱና ከክፉ መንገዱ ባይመለስ፡ በኀጢአቱ ይሞታል፤ አንተ ግን፡ ነፍስህን አድነሃል።"** ከሚለው አምላኩ፡ በቃል ኪዳን በተቀበለው፡ የሥልጣነ ክህነት አደራና ኀላፊነት፡ ለኢትዮጵያዊው ምእመን፡ የሚነግረው፡ የእውነት ቃል አለ፡ ይህም ቃል፡ ኢትዮጵያዊው ምእመን፡ ስለኀጢአቱ፡ ከፈጣሪው፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ስርየትን ለማግኘት የሚፈጽመው ንስሓ፡ እንዴት ሊኾን እንደሚገባ የሚያመለክት ነው፤ ያም፡ እንዲህ ይላል፡-

> *"በሽታህ፡ ምን መኾኑን፡ ከአንተ በላይ፡ በትክክል አውቆ፡ ፍቱኑን ፈዋሽ መድኀኒት፡ በመስቀል ላይ አዘጋጅቶ የሰጠህ፡ እውነተኛው ሓኪምህ፡ እውነተኛው ካህንህና ሊቀ ካህናትህ፡ እርሱ፡ ራሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ እኔም፡ አንተን፡ በአስታማሚነት አገለግል ዘንድ የመደበኝ፡ የእርሱ ረዳት ነኝ። ስለዚህ፡ የምታውቀውን ኀጢአትህን፡ በደልህንና ጥፋትህን፡ በምንም መንገድ ሳትሠውር፥ ወይም፡ ሳትሸሽግ፡ ግልጽልጽ አድርገህ ልትነግረው፥ ማለትም፡ ልትናዘዝለት የሚገባህ፡ ለእኔ ሳይኾን፡ ለእርሱ መኾኑን እንድትገነዘበው ያስፈልግሃል።*
>
> *"ይህን ማለቴ፡ እኔ፡ እንደምሥጢረኛ ጓደኛና አማካሪ፥ የነፍስ ረዳት ሓኪምም፡ የቅርብ ባልደረባህ ኾኜ፡ አገለግልህ ዘንድ፡ ከፈጣሪህ፡ በአደራ የተሰጠኸኝ፥ እኔም፡ በቃል ኪዳን የተቀበልሁህ ስለኾንሁ፡ ልትነግረኝ፥ ሊታማከረኝና ሊታካፍለኝ የምትፈልገውን ምሥጢር ኹሉ ዘርዝረህ ልትገልጽልኝ ትችላለህ፤ እኔም፡ ወደኋላ ሳልል፡ ዓቅሜ የሚችለውን ያህል፡ ያለማመንታትና ያለውልውል ልረዳህ ዝግጁ ነኝ።*

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ቍርባን።

### ራስን ለካህን የማሳየት ትርጓሜ።

---

*"ይኹን እንጂ፡ አንተም፡ እኔም፡ ድክመትንና ሕፀፅን (ጒድለትን) የተመላን፡ ሥጋ ለባሾች ስለኾንን፡ የመለኮት ቅዱስ ሥጋንና ክቡር ደምን የሚያህል ታላቅ ምሥጢርን ለመቀበል የሚያበቃህን፡ የኀጢአትህን ሥርየት፡ በአንተና በእኔ መካከል ብቻ ተካኺዶ በሚፈጸም ንስሓህ አማካይነት፡ "ማግኘት ትችላለህ!" ብዬ፡ አረጋግጬ ልነግርህ ቀርቶ፡ ላስበው እንኳ፡ ለእኔ፡ እጅግ ይከብደኛል፡ አንተም፡ መቼም እንደእኔው ሰው ነህና፡ እኔን የሚሰማኝ፡ አንተንም እንደሚሰማህ አምናለሁ።*

*"ስለዚህ፡ ለቅዱስ ቍርባን የሚያበቃህን፡ የኀጢአትህን ሥርየት፡ በእርግጥ ማግኘት የምትችለው፡ አንተ ብቻ የምታውቀውንና በውስጥህ ያከማቸኸውን፡ በማሰብና በመናገር፡ በማድረግም፡ በምሥጢርና በግልጽ የፈጸምኸውን፡ የኀጢአትና የበደል፡ የጥፋትም ነገር ኹሉ፡ ከአንተ በበለጠ፡ አንድ በአንድ መርምሮ ለሚያውቅብህና ለሚያውቅልህ፡ ለእርሱ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ በፍጹም እውነተኛነትና ግልጽነት፡ በቀጥታ ስትናዘዝለት ብቻ ነው።*

*"የዚህም ምክንያቱ፡ አንተና እኔ፡ በሰውነት የተፈጥሮ ባሕርያችን አንድ ስለኾንን፡ የእኔን ድክመትና ጒድለት፡ በአንተው ድክመትና ጒድለት ስለምታውቀው፡ በዚያ እውቀትህም ስለምትመዝነው፡ በግልና በጋራ ስለሠራሃቸው ኀጢአትህና በደልህ፡ ስለሌላውም ጥፋትህ፡ እውነቱን፡ ፈጽመህ ሳትናዘዝልኝ ልትቀር እንደምትችል፡ አንተም፡ እኔም፡ ኹለታችንም እናውቀዋለን፤ በዚህ ጊዜ፡ ያ ንስሓህ፡ የኀጢአት ሥርየትን፡ ከፈጣሪህ አስገኝቶ፡ ቅዱስ ቍርባንን ለመቀበል፡ የሚያበቃህ አይኾንም ማለት ነው።*

*"ከእርሱ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ግን፡ ማናቸውንም ነገር፡ በምንም መንገድ፡ ልትሸሽግ የማትችል መኾንህን፡ አንተው ራስህ፡ በሚገባ ስለምታውቀው፡ በውስጥህ ያለህን ኹሉ፡ ሳትሠውርና አንዳችም ነገር ሳታስቀር ትነግረዋለህ፡ በዚህ ጊዜ፡ ንስሓህ፡ እውነተኛና የመንፈስ ቅዱስ ኾኖ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነትና በድንግል ማርያም ኪዳንነት፡ ከእግዚአብሔር በተገኘው፡ በእውነተኛው፡ የንስሓ ጸጋ ነጽተህና ታድሰህ፡ የመለኮትን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደሙን ለመቀበል፡ የበቃህ ትኾናለህ።"*

፫ኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁ፡ የቀዳማዊውና የማእከላዊው ብቻ ሳይኾን፡ የመጨረሻው ዘለዓለማዊው **መልከ ጼዴቅ** የኾነው፡ የኢየሱስ ክርስቶስም ልጆች በመኾናችሁ፡ እየራሳችሁ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ቤተ ሕዝብ፡ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና መኾናችሁን አውቃችኋል፡ በዚህም፡ አምናችሁ፡ እነሆ፡ እየኖራችሁበት ነው።

ይህን፡ ከእግዚአብሔር፡ በቃል ኪዳንና በአደራ፡ በጸጋና በክብር የተቀበላችሁትን፡ የቅዱሱ ኪዳን ልጅነታችሁንና ኢትዮጵያዊነታችሁን፡ ኋላ፡ ከፊቱ ቀርባችሁ፡ ለባለቤቱ የምታስረክቡት፡ በነፍስ ወከፍ፡ እየራሳችሁ መኾናችሁንም ተገንዝባችኋል።

ከዚህ የተነሣ: እየራሳችሁን በሚመለከት: "ካህንም፥ ሊቀ ካህናትም!" በኾነው: በኢየሱስ ክርስቶስና በእናንተ መካከል: ሌላ: ማንም ተጠሪና ተጠያቂ ሊኖር እንደማይችል: ይህን እውነታ: በሃይማኖት ማወቅ ብቻ ሳይኾን: በሕይወታችሁ አካኼድ ኹሉ: በምግባርም እየፈጸማችሁ ልታሳዩት የሚገባችሁ መብትና ግዴታችሁ ነው:: "እንዲህ ባይኾንማ ኖሮ: ካህን በማይኖርበት፥ ወይም: እንደዛሬው ዘመን: እውነተኛ ካህን በሚታጣበት ጊዜ: ምን ይበጀኝ ነበር?" ብላችሁ በማሰብ: የዘወትር ተደሳቾችና አመስጋኞች መኾናችሁን እንዳትዘነጉት ያስፈልጋል::

ጥያቄ:- *እዚህ ላይ: ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ካህናት: ሰውን: በኃጢአቱ ምክንያት: "የማሠርና የመፍታት ሥልጣን አላቸው!" ስለሚባለው እምነት: ኢየይዘህ ብትገልጽልን?*

መልስ:- ተገቢ አርእስትን: በተገቢው ጊዜና ቦታ አንሥታችሁ ማስታወሳችሁ አግባብ ስለኾነ: ንቃታችሁን አደንቃለሁ:: ቀደም ብዬ ከሰጠኋችሁ ሓተታ እንደተረዳችሁት: ራሱን: ለቅዱሱ ኪዳን ያበቃ ኢትዮጵያዊ ኹሉ: ጥንት: በብሉዩ ኪዳን የነቦነኔ ዘመን እንኳ: በመልከ ጼዴቅ የቃል ኪዳን ጸጋና በረከት ምክንያት፥ ኋላም: በአዲስ ኪዳኑ የምሕረት ዘመን: በኢየሱስ ክርስቶስ በተገኘው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና በረከት ምክንያት: የእግዚአብሔር ካህን መኾኑን በሚበቃ አውቃችኋል::

ይህን እውነታ መሠረት አድርጌ: የዚህን ጥያቄያችሁን ማብራሪያ ልቀጥልላችሁ! ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ሰዎች: ስለእርሱ ማንነት: ምን እንደሚሉ: ለደቀ መዛሙርቱ: ጥያቄን ካቀረበላቸው በኋላ: *"እናንተስ: እኔን: ማን እንደኾንሁ ትላላችሁ?"* ባላቸው ጊዜ: ቅዱስ ጴጥሮስ: *"አንተ: ክርስቶስ: የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ!"* ብሎ ስለመለሰለት: *"የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ! በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ: ሥጋና ደም: ይህን አልገለጠልህምና: ብፁዕ ነህ:: እኔም እልሃለሁ:- 'አንተ ዓለት ነህ፤ በዚችም ዓለት ላይ: ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም፤ ለአንተም: የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታሥረው ኹሉ: በሰማያት የታሠረ ይኾናል፤ በምድርም የምትፈታው ኹሉ: በሰማያት የተፈታ ይኾናል::"* የሚል ቃልን: ከመለኮት እንዳገኘ ይታመናል::

ይኹን እንጂ: ይህ: ለቅዱስ ጴጥሮስ የተሰጠው ጸጋና በረከት: ለካህናት ብቻ እንደተላለፈ በማስመሰል: ምእመናንን ግን: በዚህ: በመምህረ ንስሓቸው ሥልጣነ ክህነት አማካይነት ብቻ ካልኾነ በቀር: በየራሳቸው ንስሓ በመግባት: ከየኃጢአታቸው ነጽተውና ታድሰው: ለቅዱሱ ቊርባን በመብቃት: ወደእግዚአብሔር መንግሥት የመግባት ዕድል እንደሌላቸው ተደርጎ እንደሚነገር ታውቃላችሁ::

ዳሩ ግን: ይህ: የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል: ለሊቀ ሓዋርያቱ ብቻ ሳይኾን: ለማናቸውም እውነተኛ ምእመን የተነገረ መኾኑን: ያው ወንጌላዊ: በዚያው ከታቡ ውስጥ: ገቅ ብሎ በመዘገበው ጽሑፉ ገልጾታል::

# ምዕራፍ ፫፡ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ቊርባን።

### ራስን ለካህን የማሳየት ትርጓሜ።

ይህም፡

አንደኛ፡ "ደቀ መዛሙርቱ፡ ወደ ኢየሱስ ቀርበው፡ 'በእግዚአብሔር መንግሥት፡ ከኹሉ የሚበልጥ ማን ይኾን?'" ብለው ላቀረቡለት ጥያቄ፡ በመካከላቸው፡ አንድ ሕፃንን በማቆም፡ "እውነት እላችኋለሁ፡ ካልተመለሳችሁ፡ እንደዚህም ሕፃን ካልኾናችሁ፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት አትገቡም፡" ሲል የሰጣቸው መልስ፡

ኹለተኛ፡ "ከእነዚህ ከታናናሾቹ፡ አንዱን እንዳትንቁ፡ ተጠንቀቁ! መላእክቶቻቸው፡ በሰማይት፡ ዘወትር፡ በሰማይት ያለውን የአባቴን ፊት ያዩሉ እላችኋለሁና።" ካለው ጋር አያይዞ፡

ሦስተኛ፡ በመካከላቸው ስለበደል ይቅርታ የሠራላቸውን ሥርዓት አክብሮ የማይፈጽም ቢኖር፡ እርሱን በሚመለከት፡ "እውነት እላችኋለሁ! በምድር የምታሥሩት ኹሉ፡ በሰማይ የታሠረ ይኾናል፡ በምድርም የምትፈቱት ኹሉ፡ በሰማይ የተፈታ ይኾናል።" በማለት የተናገረው ቃል ነው። ከትንሣኤውም በኋላ፡ ለደቀ መዛሙርቱ፡ "ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ኹሉ፡ ይቀርላቸዋል፡ ያላቻችሁባቸውም ተይዘባቸዋል።" ሲል፡ በመንፈስ ቅዱስ ያሳደረባቸው ጸጋና በረከት፡ ይህን ቃሉን አጠናክሮታል።

እንዲህ ከኾነ፡ በዚህ መልክ የሚፈጸመውን ኃጢአት፡ ለማሥርና ለመፍታት፡ ሥልጣኑ የተሰጠው፡ ለካህናት ብቻ ሳይኾን፡ ለእውነተኞቹ ምእመናንም መኾኑን፡ ደግሞም፡ በሃይማኖትና በምግባር ላይ ዓምፀው፡ በአመንዝራነት በክፉ ሰዎች ላይ፡ በምድርም፡ በሰማይም ለሚጸናው መንፈሳዊ እሥራት እና/ወይም መፈታት፡ መነሻ የሚኾነው፡ የ"ኃጢአት"፡ ወይም፡ የ"በደል"፡ ወይም፡ የ"ጥፋት"፡ ምክንያት ኹሉ፡ የተሠወረ ሳይኾን፡ በግልጽ የታወቀ መኾን እንዳለበት፡ እነዚህ፡ አኹን የሰማናቸው ጥቅሶች፡ በሙሉ ያመለክታሉ፡ ከዚህ የተነሣ፡ ይ፡ "ራስህን ለካህን አሳይ!" የሚለው አረታዊ ትእዛዝ፡ "ኃጢአትህን ለካህን ንገር!' ማለት ነው፡" ተብሎ የተሰጠው የተሳሳተ ትርጓሜ፡ እነዚህ ጥቅሶች ከያዙት መልእክት ጋር ምንም ዓይነት አግባብነት እንደሌለው፡ በቀላሉ ልትገነዘቡት ትችላላችሁ።

በሌላው ገጽታው፡ ይህ፡ ለቅዱስ ጴጥሮስ የተሰጠው፡ "የራስ ሰውነት፡ ቤተ ክርስቲያን የመኾን" መንፈሳዊ ጸጋና በረከት፡ "ሳያዩ የሚያምኑብኝ፡ ብፁዓን ናቸው!' ለሚለው፡ ለተጨማሪው የመለኮት ብዕና ለመብቃት፡ ቀዳሚ በኾነው፡ በዚያ፡ "አቤሜሌክ" በተባለው፡ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ሕይወትና የሃይማኖት ምግባር ላይ ተፈጽሞ ታይቷል።

ከዚያ ተመሳሳይ ትንግርት ጀምሮ፡ በመልከ ጼዴቅ ልጅነታቸው ምክንያት፡ በኢትዮጵያ፡ ለቤተ ሕዝቡ፡ ለቤተ ክህነቱና ለቤተ ምልክናው አባልነት ብቁ ለኾኑት፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ኹሉ፡ ይኸው ጸጋና በረከት፡ ጸንቶላቸው የኖረ መኾኑ፡ እስከዛሬ በደረሰው እውነታ፡ እነሆ፡ ተረጋግጦና ገሃድ ኾኖ ይገኛል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ፡ ተወግሮ ለመገደል ያደረሰው፡ *"ነቢዩ:- 'ሰማይ፡ ዙፋኔ ነው፤ ምድርም፡ የእግሬ መረገጫ ናት፤ ለእኔ፡ ምን ዓይነት ቤትን ትሠራላችሁ?' ይላል ጌታ፤"* ያለው ቃሉ፡ እዚህ ላይ ይጠቀሳል:: በመቀጠልም፡ *"'ወይስ፡ የማርፍበት ሥፍራ ምንድር ነው? ይህንስ ኹሉ፡ እጄ የሠራችው አይደለምን?' እንዳለ፡ ልዑል እግዚአብሔር፡ የሰው እጅ በሠራችው አይኖርም::"* ብሎ መስክሮ ባረፈባት ዕለት፡ ያስሰማው ቆራጥ ንግግር፡ ኢትዮጵያዊዉን ሰውነት፡ ለቤተ ክርስቲያንነት ያበቃውን፡ ያን፡ [፲] የኢየሱስ ክርስቶስን ሕያው ቃል፡ የበለጠ ገሃድና እውን አድርጎታል::

ስለዚህ፡ በዚህ የውይይት መድረካችን ላይ፡ በየቦታው ከተጠቀሱት፡ ነክነት ካላቸው፡ ከሌሎቹ ተመሳሳይ ቃላት ጋር፡ እነዚህም፡ ያኹኖቹ ታክለው፡ እያንዳንዱን እውነተኛ ኢትዮጵያዊ፡ እንደቅዱስ ጴጥሮስ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቤተ ክርስቲያኑን የሠራበትን ዓለት ስለሚያደርገው፥ ለዚያ ብፅዕና ያበቃውን ጸጋና በረከት ያስገኝለትም፡ ሃይማኖታዊ ምግባሩ ስለኾነ፡ የንስሓ ሥርዓቱን፡ ቀደም ብዬ በገለጽሁላችሁ መንገድ ፈጽሞ፡ በጣፋጩ ፍሬ ለመጠቀም፡ ምንም ዓይነት ችግር የሌለበት መኾኑን፡ እናንተም ተገንዝባችሁት፡ ተገቢ ድርሻችሁን፡ በእሺታ መንፈስ ትቀበሉና ለሌሎችም ታበረክቱ ዘንድ አሳስባችኋለሁ::

ይህ ኹሉ እውነታ፡ የመለኮት ብቸኛ ሀብቱ ኾኖ የኖረውን፡ ማለትም፡ አንድ ሰብአዊ ፍጡር፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በተገኘው፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ሌላውን ሰብአዊ ፍጡር፡ በኃጢአት የማሠርንና የመፍታትን ክህነታዊ ሥልጣን፡ እግዚአብሔር፡ ለአንድ ተራ ምስኪን ሰው መስጠቱ፡ ፈጣሪ፡ በመልኩ የፈጠረውን ፍጡሩን፡ የቱን ያህል እንደወደደውና እንዳከበረው ያመለክታል፤ ይህም፡ ታላቅ ቸርነት፡ ካህኑ፡ በየጊዜያቱና በየምክንያቱ፥ በየአጋጣሚውም በሚያሰማው፡ የንስሓ ኑዛዜ መጨረሻ ላይ፡ ምእመኑ፡ "ይፍቱኝ!" ሲል፡ "እኔ፡ ፈትቼሃለሁ!" ሳይል፡ "እግዚአብሔር ይፍታሕ!" ማለትም፡ "ንስሓህ እውነተኛ ከኾነ፡ እግዚአብሔር፡ ከኃጢአትህ ኹሉ ፈትቶሃል!" ብሎ በሚያሰማው የምሥራች ቃል፡ ተረጋግጦ ይታወቃል::

### ከንስሓ ስለሚያርቁ ማስፈራሪያ መልእክቶች::

ጥያቄ:- *የኃጢአትን ሥርየት አስገኝቶ፡ ለቅዱሱ ቊርባን ስለሚያበቃው ንስሓ፡ የተነገረና የተጻፈ፡ ይህን የመሰለው የምሥራች ቃል እያለ፡ በብቸኝነት የሚኖሩ፥ በጋብቻ ተወስነው ያሉ፥ ወይም፡ ወደፊት ተጋብተው ለመኖር የሚሹ፡ ለዓቅመ አዳምና ለዓቅመ ሔዋን የደረሱ፡ እኛን የመሰሉ፡ ወንዶችና ሴቶች፡ በንስሓ እየተመለሱ፡ በየግላቸውም ኾነ በአንድነት፡ ሥጋውን ደሙን እየተቀበሉ እንዳይኖሩ የሚያደርጉ፡ ማስፈራሪያ መልእክቶች፡ ከካህናት ሳይቀር፡ ታዲያ ለምን፡ በምእመናን መካከል፡ በሥውር ሲሠራጩና በይፋ ሲነገሩ ይሰማል?*

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::

## ምሥጢረ ቍርባን::

### ከንስሓ ስለሚያርቁ ማስፈራሪያ መልእክቶች::

---

መልስ:- ይህማ: *"ዓለሙን ኹሉ የሚያስተው÷ 'ዲያብሎስና ሰይጣን' የሚባለው ታላቁ ዘንዶ÷ እርሱም የቀደመው እባብ"* በሥውር የሚያሠራጨው: የተለመደው መርዘኛ ወሬው ነው:: ምክንያቱም: ወደር ለማይገኝለት: ለዘለዓለማዊው በረከት የምንበቃበትን: ይህን የመሰለውን: መለኮታዊ ጸጋ ተቀብለን: በዚህ ዓለም እያለን: መልካሚን የገነት ሕይወት እንዳንኖራት ሊያደርግ መኾኑ: በግልጽ ይታወቃል::

ስለዚህ: ይህን የርኵስ መንፈስ መርዘኛ ወሬ ሰምተንና ተታልለን: ከእግዚአብሔር: በቃል ኪዳን ካገኘናቸው: የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን ምግባርና` ሥርዓት እንዳንነዋወጥ÷ በከይሲዉም የጥፋት ወጥመድ እንዳንጠመድ መጠንቀቅ ግዴታችን ነው::

የመጀመሪያዎቹን አዳምና ሔዋን: *"ሌላውን ኹሉ: ብሉ! ነገር ግን: እንዳትሞቱ: በገነት መካከል ከሚገኘው ዛፍ ብቻ አትብሉ!"* ያላቸውን: የአምላካቸውን: የእግዚአብሔርን ቃል በማሳሳት: "የለም! አትሞቱምና: ብሉ!" ብሎ: የፈጣሪያቸውን ፈቃድ: በድፍረት አስፈርሶ: ከገነት ተድላ ደስታ ያስወጣቸውና ለሞት ፍርድ ያበቃቸው: ይህ: የእግዚአብሔር ተቃዋሚ÷ የሰው ልጆች ባላጋራና የክፋት አበጋዝ የኾነው ዲያብሎስ መኾኑን ልንዘነጋው አይገባም:: ዛሬም: ያንኑ የማሳሳት ተግባሩን: በተፃራሪ መልኩ: እንዴት አድርጎ መቀጠሉን መመልከት ነው:: ይኸውም: *"ለዘለዓለም ሕያዋን ኾናችሁ ትኖሩ ዘንድ: የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን: ሥጋዬን ብሉ! ደሜንም ጠጡ!"* ያለውን: የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል÷ በዚህም መለኮታዊ ቃል መሠረት: *"የእግዚአብሔር መንግሥት: እነሆ: በመካከላችሁ ናትና: በቅዱሱ ኪዳን የተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ እንደጸናችሁ: ንስሓ እየገባችሁና ሥጋ ወደሙን እየተቀበላችሁ: ወደእርሷ ግቡ!"* ማለትም: *"ቍረቡ! ወደእግዚአብሔርም ቅረቡ!"* በሚል መልእክት: የምሥራች አዋጅ የሚነግሩትን: የቅዱሱን ኪዳን አገልጋዮች ኢትዮጵያውያን ተልእኮ: እነሆ ሊያፈርስ ሲታገል ይታያል::

ይልቁንም: ሥጋ ወደሙ መቀበል: ለእሥረኛነት: ወይም: ለጭንቀት ኑሮ የሚዳርግ በማስመሰል: "አትቍረቡ!" ማለትም: "ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለመቀበል: አትቅረቡ! ኋላ: ስታረጁ ያደርሳችኋል፤ አሁን: በዚህ ዕድሜያችሁ የቈረባችሁ እንደኾነ: በሥጋችሁ ትቀሠፋላችሁ! በነፍሳችሁም: ገሃነመ እሳት ትወርዳላችሁ!" እያለ: እነሆ: ኢየሱስ ክርስቶስ: በደሙ የዋጃቸውን: የቃል ኪዳን ሕዝቡን: የራሱ ጭፍሮችና የገሃነም ልጆች ለማድረግ: በብርቱ እየጣረ መኾኑን እንመለከታለን::

እንግዴህ: ፈጣሪያችን: ሰው እስከመኾን ተዋርዶና ከማሕፀን ጀምሮ: ከቅድስት እናቱ ጋር: እስከሞቱ ድረስ፡ በማንም ሰው ላይ ያልደረሱ: ታላላቅ ፈተናዎችን: በትዕግሥት ተቀብሎ የተሠዋው: ለማንና ለምን እንደኾነ እናስብ! ይህን ኹሉ ውርደትና ፈተና የተቀበለው÷ መከራውንና ሥቃዩንም የታገሠው÷ በዚህ መሥዋዕትነቱም: ጠላቶቻችንን ኹሉ ድል ያደረገው: ለእኛ ሲል መኾኑን ፈጽመን እንወቅ!

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

እኛም፡ በትንሣኤው፡ ሕያው ያደረገውንና መለኮት የተዋሐደውን ሥጋውን በልተንለትና ደሙን ጠጥተንለት፡ በሥጋችንም ኹነ በነፍሳችን፡ ፍጹም ዕረፍትን እንድናገኝለት መኾኑን አስተውሉት!

ዲያብሎስና አገልጋዮቹ እንደሚያናፍሱት ሳይኾን፡ በቅዱሱ ኪዳን የተዋሕዶ ሃይማኖታችን ተመሥርተንና በምግባር ጸንተን፡ ከየኃጢአታችንም፡ በንስሓ ነጽተንና ታድሰን የምንቀበለው፡ የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለሥጋ አካላችንም ኾነ፡ ለነፍሳችን፡ የኃጢአት ማስተሥረያ፡ መድኃኒትና ሕይወት ይኾነናል።

በዚህ ጊዜ፡ የየግልና የጋራ ኑሮአችን፡ ከሰይጣን ግዛት፤ ከኃጢአት ቀንበርና ከሞት ፍዳ ነጻ ይኾናል፡ ሥጋትና ጭንቀት፡ ፍርሃትና ጥርጣሬ፡ ኀዘንና ትካዜ ተወግደው፡ እውነትና ሰላም፡ ፍቅርና ጤንነት፡ ብልጽግናና ደስታ ይሰፍኑበታል።

ስለዚህ፡ እናንተ፡ ዛሬ የምትኖሩበት ምርጫችሁ፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ጥሪ የተከተለ ሳይኾን፡ ምናልባት፡ ከዚህ የተለየውን፡ የዲያብሎስን ከኾነ፡ ንስሓ ሳትገቡ፡ ሥጋ ወደሙንም ሳትቀበሉ፡ በየኃጢአታችሁ እንዳላችሁ፡ የሞት ጽዋ ተራችሁ እንዳይደርስባችሁ፡ ጊዜ ሳትሰጡ፡ በቶሎ፡ ወደንስሓ እንድትመለሱ አሳስባችኋለሁ። ይህን ማሳሰቢያ የምሰጣችሁ፡ መቼ እንደምትገለጽ የማትታወቀው፡ "የእግዚአብሔር ቀን" እና "ትንሣኤ ዘጉባኤ" የምትባለው፡ የመጨረሻው የሙታን ትንሣኤ የሚፈጸምባት፡ ታላቂቱ የዳግም ምጽዓቱ ዕለት፡ በድንገት እንዳትመጣባችሁ ነው፡ በዚህም የስሕተት ምርጫችሁ ምክንያት፡ ፍጻሜአችሁ፡ እግዚአብሔር፡ እርሱን ለፈለጉት የሰው ልጆች፡ ዓለም ሳይፈጠር ወዳዘጋጃት፡ ወደዘለዓለም የሕይወት መንግሥቱ መግባት ሳይኾን፡ ለሰይጣንና ለሠራዊቱ ወደተዘጋጀው፡ የዘለዓለም ቅጣት መኼድ እንዳይኾንባችሁ ነው፤ እንግዲህ ወዲህ የምንጠብቀው፡ ሌላ ማስጠንቀቂያ አይመጣልንምና፡ በእምቢተኛነታችሁ፡ በኖኅ ዘመን እንደነበረው ትውልድ፡ ጠፍታችሁ እንዳትቀሩ፡ አኹኑኑ፡ እየራሳችሁን፡ በንስሓ እያደሳችሁ፡ "ቁረቡ!" ለሚለው፡ ለቃል ኪዳን አምላካችሁ የመጨረሻ ጥሪ፡ የቢቃችሁ እንድትኾኑ ነው።

## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።

*ጥያቄ፡- የሙታን ትንሣኤ ነገር ከተነሣ ዘንድ፡ ስለዚሁ የረቀቀ ርእስ፡ ሊያስረዳ ስለሚችለው፡ ስለመጨረሻው የ"ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን" ነገር፡ እስኪ፡ ቀጥለህ ንገረን?*

መልስ፡- አዎን፥ እውነታችሁን ነው! ከአምስቱ የአዕማደ ምሥጢረ ሃይማኖት፡ የመጨረሻው የኾነው፡ ይህ አርእስት የሚናገረው፡ ስለዚሁ ጉዳይ ነውና፡ አሁን፡ በ"ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን" ላይ እናተኩራለን።

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::
## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን::

---

በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠሩት አዳምና ሔዋን: የወለዷቸው ወንዶችና ሴቶች ልጆች ተዋልደው ያስገኙት የሰው ዘር: እያንዳንዱ: ከሞተ በኋላ: በመቃብር: ፈርሶ፣ በስብሶ ሳይቀር: በማይጠፋ አዲስ አካል: እንደገና: ሕያው ኾኖ የሚነሣ መኾኑ: በሃይማኖት የታወቀበትና የሚነገርበት ትምህርት: "ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን" ይባላል:: ይህም ትንሣኤ: ከእነዚሁ የሰው ልጆች መካከል: በፈጠራቸው: በሚመግባቸውና በሚጠብቃቸው: በአንዱ እግዚአብሔር አምላካቸው: አምነውና ሥርዓቱን ተከትለው ለኖሩት: የዘለዓለም ሕይወት ይኾንላቸዋል:: የፈጠራቸውን: የሚመግባቸውንና የሚጠብቃቸውን: እግዚአብሔርን ክደውና ዲያብሎስን ተከትለው ለኖሩት ደግሞ: የዘለዓለም ሥቃይ ይኾንባቸዋል::

የሙታን ትንሣኤ የተጀመረውና በግልጽ የታወቀው: አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ: በምሥጢረ ሥጋዌው: ለፍጥረቱ የወጠነውንና እውን ያደረገውን ቸርነቱን: በምሥጢረ ጥምቀትና በምሥጢረ ቍርባን ገሃድ ካደረገ በኋላ: ከዲያብሎስና ከሰዎች: በፈቃዱ በተቀበላቸው ፈተናዎች: መከራዎችና ሥቃዮች: ክፋትን፥ ኃጢአትንና ሞትን: በመቃብር መበስበስንም: በታላቅ ኃይልና ሥልጣን: ድል አድርጎና ደምስሶ፥ ሽሮና አጥፍቶ: ከሙታን ተለይቶ በተነሣ ጊዜ ነው:: በእርሱ አምነውና ተጠምቀው፥ በእውነተኛ ንስሓም: ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበሉ የሚኖሩ ጻድቃን: ያን: እርሱ የተነሣበትን አዲስ አካል ለብሰውና *"እናንተ የአባቴ ቡሩካን!"* ተብለው: ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ: የተዘጋጀላቸውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ፤ እርሱን ክደው: ዲያብሎስን የተከተሉትም ኃጥኣን: የማይጠፋውን አካል ለብሰውና *"እናንተ ርጉማን!"* ተብለው: ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀው ወደዘለዓለም እሳት ሊጣሉ: በፍጥረተ ዓለሙ ፍጻሜ: ሙታን ኹሉ የሚነሡት ትንሣኤ: "ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን" ይባላል::

### የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ::

ጥያቄ:- *የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ እንዴት እንደነበረ ብትነግረን?*

መልስ:- ቀድሞ: *"እግዚአብሔር: ከእንቅልፍ እንደሚነቃና የወይን ስካር እንደተወው ኃያል ተነሣ! ጠላቱንም: አሳድዶ ገደለው!"* ተብሎ በነቢያት ተነግሮ እንደነበረው፥ ኋላም: ራሱ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ: *"እነሆ: ወደኢየሩሳሌም እንወጣለን፤ የሰው ልጅም: ለካህናት አለቆችና ለጻፎች ይሰጣል፤ የሞት ፍርድም ይፈርዱበታል፤ ሊዘባበቱበትና ሊገርፉት፥ ሊሰቅሉትም: ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል፤ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል!"*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

*"ዮናስ፡ በዓሣ አንበሪ ሆድ፡ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደነበረ፡ እንዲሁ፡ የሰው ልጅ፡ በምድር ልብ፡ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል።"፡ "ነፍሴን በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ፡ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ፡ ደግሞም፡ ላነሣት ሥልጣን አለኝ።"* ብሎ፡ ለደቀ መዛሙርቱ፡ አስቀድሞ እንዳስተማራቸው፡ ሕማማተ መስቀሉን ፈጽሞ፡ የሞት ጽዋውን ተቀበለ።

በአንድ በኩል፡ መለኮት በተዋሐዳት ነፍሱ፡ ወደሲዖል ወርዶ፡ የምሥራቹን ቃል፡ ለጻድቃን ነፍሳት ካሰማቸው በኋላ፡ ከዚያ የመርገም እሥራት፡ ነጻ ሲያወጣቸው፡ በሌላ በኩል ደግሞ፡ መለኮት በተዋሐደው ሥጋው፡ ወደመቃብር ወርዶ፡ በዚያ፡ ፫ መዓልትና ፫ ሌሊት በማደር፡ የሥጋ መበስበስን ካጠፋ በኋላ፡ "መግነዝ ፍቱልኝ! መቃብር ክፈቱልኝ!" ሳይል፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ! የተነሣውም፡ *"ሥጋና ደም፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም፡ የሚበሰብሰውም፡ የማይበሰብሰውን አይወርስም!"* በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት፡ በማይሞተውና በማይበሰብሰው፡ በማይለወጠውና በማይጠፋው፡ ሊገለጽና ሊሠወር በሚችለው፡ ለዘለዓለም በሚኖረው፡ በአዲሱ የትንሣኤ መንፈሳዊ አካል ነው።[፺፣]

ይህ ኹሉ የኾነው፡ አያሌ የተለያዩ ታላላቅ ፈተናዎችንና መከራዎችን ተቀብሎ፡ የክፋት መንፈስ የኾነውን፡ ዲያብሎስን፡ ሰውን ከእግዚአብሔር የለየውን፡ ኃጢአትንና የኃጢአት ዋጋ የኾነውን ሞትን ድል ካደረገ በኋላ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ፈተናዎችና መከራዎች መገለጽ የጀመሩት፡ ድንግል ማርያም፡ የእግዚአብሔር ወልድን፡ የትስብእቱን ምሥራች፡ በቤተ ዮሴፍ፡ ከመልአኩ፡ ከቅዱስ ገብርኤል ከመስማቷ አስቀድሞ፡ "ቤተ መቅደሳችንን ታረክስብናለች" ብለው፡ ከፋዎች አይሁድ፡ ለ፲፪ ዓመታት ከኖረችበት ቤተ መቅደስ፡ እርሷን ባስወጡበት ጊዜ ሲኾን፥ ከዚያም፡ ሕፃን ልጇን፡ በበረት እስከወለደችበትና በሄሮድስ የግፍ አዋጅ ምክንያት፡ እርሱን ታቅፋ እስከተሰደደችበት ዘመን ቀጥሏል።

ሕፃኑ ኢየሱስ፡ ካደገ በኋላ፡ በገሊላ ናዝሬት ዋሻዎችና በየአገሩ በመንከራተት፡ ከዲያብሎስ፡ በገዳመ ቆሮንቶስ፥ ከአይሁድ ሊቃነ ካህናትም፡ በኢየሩሳሌም የተዘጋጁለትን ፈተናዎች አስተናግዶ፡ ወደመጨረሻው የመስቀል መከራው ተሻገረ። በዚያም፡ የስድብ ናዳንና የምራቅ ትፋትን መታገሥን፥ የፊጥኝ መታሠርን፥ በጥፊ መመታትን፥ ከልብስ መራቆትን፥ በገመድ መጐተትን፥ በምድር ላይ መውደቅን፥ በእግር መረገጥን፥ ከወዲያ ወዲህ መገፋትን፥ በራቁትነት መገረፍን፥ የራስ መደብደብን፥ የሾህ አክሊል መድፋትን፥ መስቀል መሸከምን፥ የእግርና የእጅ መቸንከርን፥ በእንጨት ላይ መሰቀልን፥ መራራ ሓሞትን መጠጣትን፥ በፍጻሜውም፡ የሞት ጽዋን መቅመስንና ጐንን በጦር ተወግቶ፡ የራሱን ደም ማፍሰስን፡ እኒህን ኹሉ መከራዎች ተቀበለ።

# ምዕራፍ ፫፣ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።

ለሰው ልጆች፡ ከሙታን ተለይቶ የመነሣት ጸጋና ክብር የተገኘው፡ ሰው የኾነው አምላክ፡ እኒህን ፈተናዎችና መከራዎች፡ ስለእናንተና ስለእኔ፡ እኛን ስለመሰሉ የሰው ልጆች ኹሉ ሲል፡ እስከመጨረሻ በጸና ትእግሥት በመቀበሉ መኾኑን፡ ዘወትር ማስታወስ ይገባናል።

*"አሁን ግን፡ ክርስቶስ፡ ላንቀላፉት፡ በኵር ኾኖ፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቷል! ሞት፡ በሰው በኩል ስለመጣ፡ ትንሣኤ ሙታንም፡ በሰው በኩል ኾኗልና። ኹሉ፡ በአዳም እንደሚሞቱ፡ እንዲሁ፡ ኹሉ፡ በክርስቶስ ደግሞ፡ ሕያዋን ይኾናሉና። የሰው ኹሉ ትንሣኤ፡ በየሥርዓቱ ይኾናል፡ ከሙታን ተለይቶ የተነሣው ክርስቶስ፡ ቀዳሚ ነው፡ ከዚህ በኋላ፡ የክርስቶስ የኾኑት ናቸው፡ ያም፡ በምጽአቱ ጊዜ ይኾናል።"*

እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ፡ ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡ በዳግም ምጽአቱ፡ ለሰው ልጆች ኹሉ ለሚኾነው፡ ለመጨረሻው ትንሣኤ፡ የመጀመሪያው ኾነ! ከእርሱ ቀጥሎ፡ የዚህ ትንሣኤ፡ ተከታይዋና ኹለተኛዋ ባለዕድል ኾና፡ ይኸው ትንሣኤ የተፈጸመላት፡[፶፯] በዜና ፍልሰታዋ እንደሚነገረው፡ እናቱ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ናት።

አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከሙታን ተለይቶ ስለመነሣቱ፡ ገና በሕይወቱ ሥጋ ሣለ፡ ለደቀ መዛሙርቱ በነገራቸው መሠረት፡ እኛን፡ እያንዳንዳችንንና ፍጥረተ ዓለሙን ለማዳን ሲል፡ በተፈጥሮው፡ መስቀልኛ የኾነው ዕርቃን ሥጋውን፡ በእንጨት ላይ አመሳቅሎ፡ በሾህ አክሊሉ ደም የተሸፈነ ራሱንና ፊቱን፡ ወደላይ አቅንቶ፡ በመስቀሉ ግማዶች ላይ፡ ወዲያና ወዲህ የተወጠሩትን፡ የቀኝና የግራ እጆቹን መዳፎች፡ ወደታች የተሳቡ እግሮቹንም፡ ከእንጨቱ ጋር በብረት ችንካር አስጠርቆ፡ በጀርባው ከተዘረጋና የሞት ጽዋውን ከተጐነጨ በኋላ፡ እንዴት፡ ከመስቀል ወርዶ እንደተገነዘ፡ እንደተቀበረና በመጨረሻ እንደተነሣ፡ እንዲህ የሚለው፡ የወንጌላውያኑ ቃል፡ በሚገባ ያስረዳል፡-

*"ስድስት ሰዓትም ያህል ነበረ፤ ጨለማም፡ እስከዘጠኝ ሰዓት በምድር ኹሉ ላይ ኾነ! ፀሓይም ጨለመ! የቤተ መቅደስ መጋረጃም፡ ከመካከሉ ተቀደደ። ጌታችን ኢየሱስም፡ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፡ 'አባት ሆይ! ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ!' አለ፤ ይህንም ብሎ፡ ነፍሱን ሰጠ።*

*"...እነሆም፡ በጎና ጻድቅ፡ የሸንጎም አማካሪ የኾነ፡ 'ዮሴፍ' የሚባል ሰው ነበረ፤ እርሱም፡* [በአይሁድ] *በምክራቸውና በሥራቸው አልተባበረም ነበር፤ 'አርማትያስ' ከምትባልም፡ ከአይሁድ ከተማ ኾኖ፡ እርሱ ደግሞ፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ይጠባበቅ ነበር። ወደጲላጦስም ቀርቦ፡ የጌታችን ኢየሱስን ሥጋ ለመነው፤* [ስለፈቀደለት፡ ከመስቀል] *አውርዶ፡ በተልባ እግር* [ከተልባ ልጥ ክር የተሠራ ጠንካራ ጨርቅ] *ልብስ ከፈነው፤ ማንም፡ ገና ባልተቀበረበት፡ ከዓለትም በተወቀረ መቃብር አኖረው።*

*"...ከገሊላም፡ ከእርሱ* [ከኢየሱስ] *ጋር የመጡት ሴቶች፡ ተከትለው፡ መቃብሩን፡ ሥጋውንም፡ እንዴት እንዳኖሩት አዩ። ተመልሰውም፡ ሽቱና ቅባት አዘጋጁ። በሰንበትም፡* [ቅዳሜን] *እንደትእዛዙ ዐረፉ።*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

*"ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው፡ ከእነርሱም ጋር አንዳንዶቹ፡ ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን፡ [እሑድ]፡ እጅግ ማልደው፡ ወደመቃብሩ በመጡ ጊዜ ግን፡ ድንጋዩን፡ ከመቃብሩ ተንከባሎ አገኙት:: ገብተውም፡ የጌታችን የኢየሱስን ሥጋ አላገኙም:: እነርሱም፡ በዚህ ሲያመነቱ፡ እነሆ፡ ኹለት ሰዎች፡ የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሰው፡ ወደእነርሱ ቀረቡ፡ ፈርተውም፡ ፊታቸውን ወደምድር አቀርቅረው ሳሉ፡ እንዲህ አሏቸው:- "ሕያውን፡ ከሙታን መካከል፡ ስለምን ትፈልጋላችሁ? ተነሥቷል እንጂ፡ በዚህ የለም! 'የሰው ልጅ፡ በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ሊሰጥና ሊሰቀል፡ በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ ግድ ነው!' እያለ፡ ገና በገሊላ ሳለ፡ ለእናንተ እንደተናገረ አስቡ!" እነርሱም ቃሎቹን አሰቡ:: ከመቃብሩም ተመልሰው፡ ይህን ኹሉ፡ ለአሥራ አንዱና ለሌሎች ኹሉ ነገሩአቸው::"*

*"ስለዚህ፡ ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር [ዮሐንስ]፡ ወጥተው፡ ወደመቃብሩ ኼዱ፡ ኹለቱም፡ አብረው ሮጡ፡ ሌላው ደቀ መዝሙርም፡ ከጴጥሮስ ይልቅ፡ ፈጥኖ፡ ወደፊት ሮጠና፡ አስቀድሞ፡ ከመቃብሩ ደረሰ፡ ዝቅም ብሎ ቢመለከት፡ የተልባ እግሩን ልብስ [የተገነዘበትን ጨርቅ] ተቀምጦ አየ፡ ነገር ግን፡ አልገባም::*

*"ስምዖን ጴጥሮስም፡ ተከትሎት መጣ፡ ወደመቃብሩም ገባ፡ የተልባ እግሩም ልብስ ተቀምጦ አየ፡ ደግሞም፡ በራሱ የነበረውን ጨርቅ፡ ለብቻው፡ በአንድ ሥፍራ ተጠምጥሞ እንደነበረ እንጂ፡ ከተልባ እግሩ ልብስ ጋር ተቀምጦ እንዳልነበረ፡ አየ:: በዚያን ጊዜ፡ አስቀድሞ፡ ወደመቃብር የመጣውም፡ ሌላው ደቀ መዝሙር ገባ፡ አየም፡ አመነም፡ 'ከሙታን ተለይቶ ይነሣ ዘንድ እንዲገባው፡' የሚለውን፡ የመጽሐፉን ቃል፡ ገና አላወቁም ነበርና:: ደቀ መዛሙርቱም፡ ወደቤታቸው ተመለሱ::*

*"[መግደላዊት] ማርያም ግን፡ እያለቀሰች፡ ከመቃብሩ በስተውጭ ቆማ ነበር:: ስታለቅስም፡ ወደመቃብር ዝቅ ብላ ተመለከተች፡ ኹለት መላእክትም፡ ነጭ ልብስ ለብሰው፡ የጌታችን ኢየሱስ ሥጋ ተኝቶበት በነበረው፤ አንዱ በራስጌ፡ ሌላውም በግርጌ ተቀምጠው አየች:: እነርሱም፡ "አንቺ ሴት! ስለምን ታለቅሻለሽ?" አሏት:: እርሷም፡ "ጌታዬን ወስደውታል፡ ወዴትም እንዳኖሩት አላውቅም::" አለቻቸው:: ይህንም ብላ ወደኋላ ዘወር ስትል፡ ጌታችን ኢየሱስን ቆሞ አየችው፡ ጌታችን ኢየሱስም እንደኾነ አላወቀችም:: ጌታችን ኢየሱስም፡ "አንቺ ሴት! ስለምን ታለቅሻለሽ? ማንንስ ትፈልጊያለሽ?" አላት:: እርሷም፡ የአትክልት ጠባቂ መስሏት፡ "ጌታ ሆይ! አንተ ወስደኸው እንደኾንህ፡ ወዴት እንዳኖርኸው ንገረኝ፡ እኔም ወስጄ፡ ሽቱ እንድቀባው!" አለችው:: ጌታችን ኢየሱስም፡ "ማርያም!" አላት:: እርሷም፡ ዘወር ብላ፡ በዕብራይስጥ፡ "ረቡኒ!" አለችው፡ ትርጓሜውም፡ 'መምህር ሆይ!' ማለት ነው:: ጌታችን ኢየሱስም፡ "ገና፡ ወደአባቴ አላረግሁምና፡ አትንኪኝ! ነገር ግን፡ ወደወንድሞቼ ኺደሽ፡ 'እኔ፡ ወደአባቴና ወደአባታችሁ፡ ወደአምላኬና ወደአምላካችሁ ዐርጋለሁ!' ብለሽ ንገሪያቸው!" አላት:: መግደላዊት ማርያም መጥታ፡ ጌታን እንዳየች፡ ይህንም እንዳላት፡ ለደቀ መዛሙርቱ ነገረች::*

## ምዕራፍ ፫፡ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
### ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።

"እነሆም፡ ከእነርሱ ኹለቱ፡ በዚያ ቀን፡ ከኢየሩሳሌም፡ ስድሳ ምዕራፍ ያህል ወደሚርቅ፡ "ኤማሁስ" ወደሚባል መንደር ይኼዱ ነበር፡ ስለዚህም፡ ስለኾነው ነገር ኹሉ፡ እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር። ሲነጋገሩና ሲመራመሩም፡ ጌታችን ኢየሱስ ራሱ ቀርቦ፡ ከእነርሱ ጋር ይኼድ ነበር፡ ነገር ግን፡ እንዳያውቁት፡ ዓይናቸው ተይዞ ነበር። እርሱም፡ "እየጠወለጋችሁ ስትኼዱ፡ እርስ በርሳችሁ የምትነጋገሩዋቸው፡ እነዚህ ነገሮች፡ ምንድር ናቸው?" አላቸው።

"ቀለዮጳ የሚባለውም አንዱ፡ መልሶ፡ "አንተ፡ በኢየሩሳሌም፡ እንግዳ ኾነህ፡ ለብቻህ ትኖራለህን? በእነዚህ ቀኖች፡ በዚያ፡ የኾነውን ነገር አታውቅምን?" አለው። እርሱም፡ "ይህ ምንድር ነው?" አላቸው። እነርሱም፡ እንዲህ አሉት፡ "በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ኹሉ ፊት፡ በሥራና በቃል፡ ብርቱ ነቢይ ስለነበረው፡ ስለናዝሬቱ ኢየሱስ፡ እርሱንም፡ የካህናት አለቆችና መኳንንቶቻችን፡ ለሞት ፍርድ፡ እንዴት አሳልፈው እንደሰጡትና እንደሰቀሉት ነው። እኛ ግን፡ እስራኤልን እንዲቤዥ ያለው፡ እርሱ እንደ ኾነ፡ ተስፋ አድርገን ነበር። ደግሞም፡ ከእርሱ ኹሉ ጋር፡ ይህ ከኾነ፡ ዛሬ፡ ሦስተኛው ቀን ነው።

"ደግሞም፡ ከእኛ ውስጥ ማልደው፡ ከመቃብሩ ዘንድ የነበሩት አንዳንድ ሴቶች አስገረሙን፡ ሥጋውንም ባጡ ጊዜ፡ 'ሕያው ነው! የሚሉ፡ የመላእክትን ራእይ ደግሞ አየን!' ሲሉ መጥተው ነበር። ከእኛም ጋር ከነበሩት፡ ወደመቃብር ኼደው፡ ሴቶቹ እንደተናገሩት ኾኖ አገኙት፡ እርሱን ግን፡ አላገኙትም።

"እርሱም፡ "እናንተ የማታስተውሉ! ነቢያትም የተናገሩትን ኹሉ፡ ልባችሁ ከማመን የዘገየ! ክርስቶስ፡ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደክብሩ ይገባ ዘንድ፡ ይገባው የለምን?" አላቸው። ከሙሴና ከነቢያት ኹሉ ጀምሮ፡ ስለእርሱ፡ በመጻሕፍት ኹሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው።

"ወደሚኼዱበትም መንደር ቀረቡ፡ እርሱም፡ ሩቅ የሚኼድ መሰላቸው። እነርሱም፡ "ከእኛ ጋር እደር! ማታ ቀርቧልና፡ ቀኑም ሊመሽ ጀምሯል፡" ብለው ግድ አሉት። ከእነርሱም ጋር ሊያድር ገባ። ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ፡ እንጀራውን አንሥቶ ባረከው፡ ቈርሶም ሰጣቸው፡ ዓይናቸውም ተከፈተ፡ አወቁትም፡ እርሱም፡ ከእነርሱ ተሠወረ።

"እርስ በርሳቸውም፡ "በመንገድ ሲናገረን፡ መጻሕፍትንም ሲከፍትልን፡ ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን?" ተባባሉ። በዚያችም ሰዓት ተነሥተው፡ ወደኢየሩሳሌም ተመለሱ፡ አሥራ አንዱና ከእነርሱ ጋር የነበሩትም፡ "ጌታ፡ በእውነት ተነሥቷል! ለስምዖንም ታይቷል!" እያሉ፡ በአንድነት ተሰብስበው አገኟቸው። እነርሱም፡ በመንገድ የኾነውን፡ እንጀራውንም በቈረሰ ጊዜ፡ እንዴት እንደታወቀላቸው፡ ተረኩላቸው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

"ይህንም ሲነጋገሩ፡ ጌታችን ኢየሱስ ራሱ፡ በመካከላቸው ቆሞ፡ "ሰላም ለእናንተ ይኹን!" አላቸው፡፡ ነገር ግን፡ እነርሱ፡ ደነገጡ፤ ፈሩም፤ መንፈስም ያዩ መሰላቸው፡፡ እርሱም፡ "ስለምን ትደነግጣላችሁ? ስለምንስ አሳብ በልባችሁ ይነሣል? እኔ ራሴ እንደኾንኹ፡ እጆቼንና እግሮቼን እዩ! በእኔ እንደምታዩት፡ መንፈስ፡ ሥጋና አጥንት የለውምና፡ እኔን፡ ዳስሳችሁ እዩ!" አላቸው፡፡ ይህንም ብሎ፡ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው፡፡ እነርሱም፡ ከደስታ የተነሣ፡ ገና ስላላመኑ፡ ሲደነቁ ሣሉ፡ "በዚህ፡ አንዳች የሚበላ አላችሁን?" አላቸው፡፡ እነርሱም፡ ከተጠበሰ ዓሣ፡ አንድ ቁራጭ፤ ከማር ወለላም ሰጡት፤ ተቀብሎም በፊታቸው በላ፡፡

"ነገር ግን፡ ከአሥራ ኹለቱ አንዱ፡ 'ዲዲሞስ' የሚሉት ቶማስ፡ ጌታችን ኢየሱስ በመጣ ጊዜ፡ ከእነርሱ ጋር አልነበረም፡፡ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት፡ "ጌታን አይተነዋል!" አሉት፡፡ እርሱ ግን፡ የችንካሩን ምልክት፡ በእጆቹ ካላየሁ፡ ጣቴንም፡ በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ፥ እጄንም፡ በጎኑ ካላገባሁ፡ አላምንም!" አላቸው፡፡

"ከስምንት ቀን በኋላም፡ ደቀ መዛሙርቱ ደግመው፡ በውስጥ ነበሩ፤ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ፡፡ ደጆች ተዘግተው ሣሉ፡ ጌታችን ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ፡ "ሰላም ለእናንተ ይኹን!" አላቸው፡፡ ከዚያ በኋላም፡ ቶማስን፡ "ጣትህን ወደዚህ አምጣና፡ እጆቼን እይ! እጅህንም አምጣና፡ በጎኔ አግባው! የመንህ እንጂ፡ የላመንህ አትኹን!" አለው፡፡ ቶማስም፡ "ጌታዬ! አምላኬም!" ብሎ መለሰለት፡፡

"ጌታችን ኢየሱስም፡ "ስላየኸኝ፡ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ፡ ብፁዓን ናቸው!" አለው፡፡"

"ጌታችን ኢየሱስም፡ 'ከእናንተ ጋር ሣለሁ፡ "በሙሴ ሕግና በነቢያት፥ በመዝሙራትም፡ ስለእኔ የተጻፈው ኹሉ፡ ይፈጸም ዘንድ ይገባል!" ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው፤' አላቸው፡፡ በዚያን ጊዜ፡ መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ፡ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤ እንዲህም አላቸው፡- 'ክርስቶስ መከራ ይቀበላል! በሦስተኛውም ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ይነሣል! በስሙም፡ ንስሓና የኃጢአት ሥርየት፡ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ኹሉ ይሰበካል!' ተብሎ፡ እንዲሁ ተጽፎአል፡፡ እናንተም፡ ለዚህ፡ ምስክሮች ናችሁ! እነሆም፡ አባቴ፡ የሰጠውን ተስፋ፡ እኔ እልክላችኋለሁ! እናንተ ግን፡ ከላይ፡ ኃይልን እስክትለብሱ ድረስ፡ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ!"

"እስከቢታንያም አወጣቸው፡፡ እጆቹንም አንሥቶ ባረካቸው፡፡ ሲባርካቸውም፡ ከእነርሱ ተለየ፤ ወደሰማይም ዐረገ፡፡ እነርሱም፡ ሰገዱለትና በብዙ ደስታ፡ ወደኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ ዘወትርም፡ እያመሰገኑና እየባረኩ፡ በመቅደስ ኖሩ፡፡"

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ፡ አማናዊው የትንሣኤው ምሥራችና ዜናው፥ ደግሞም፡ በእርሱ የሚያምኑ፡ እውነተኞች ወገኖቹ፡ እንዲቀዳጁት ያስገኘላቸው፡ ዘለዓለማዊው የትንሣኤ ሕይወት፡ እንግዲህ፡ ይህ ነው፡፡[፺፯]

## ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።

### የሦስት መዓልትና የሦስት ሌሊት ስሌት።

ጥያቄ:- *አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ: በሰውነቱ ሞቶና ተቀብሮ: በዚያ መቃብሩ ውስጥ: "፫ መዓልትና ፫ ሌሊት ካደረ በኋላ: ከሙታን ተለይቶ ተነሣ!" የሚለው የቀኑና የሌሊቱ ስሌት: ከዓርብ ምሽት ጀምሮ እስከእሑድ ጠዋት ድረስ ያለው ጊዜ: በተለመደው መሥፈርት ሲታሰብ: እንዴት ትክክል ሊመጣ ቻለ? ይህን ጥያቄ: እባክህ: እዚህ ላይ አየይዘህ ብታብራራልን?*

መልስ:- *"ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት"* የሚለው የጊዜ ስሌት: በኹለት መንገዶች ሊታሰብ ይቻላል:

፩ኛው መንገድ: አንድ ዕለት: "፩ መዓልት" እና "፩ ሌሊት" ተብለው: እኩል የተከፈሉ: የብርሃንና የጨለማ ጊዜያትን የያዘ የ፳፬ ሰዓቶች የጊዜ መጠን ስለኾነ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: በከርሠ መቃብር ውሎ ካደረበት: ከሙሉው የቅዳሜ አንድ ቀን ጋር: ተሰቅሎና ሙቶ የተቀበረበትን: ዓርብንና በሌሊት አጥቢያዋ: ከሙታን ተለይቶ የተነሣባትን እሑድን: እያንዳንዳቸውን: እንደአንዳንድ ሙሉ ቀን: ማለትም: ኹለቱን ዕለታት: እንደኹለት ሙሉ ቀኖች በመቁጠር: ጌታችን: በመቃብር ውስጥ: "፫ መዓልትና ፫ ሌሊት ካደረ በኋላ: ከሙታን ተለይቶ ተነሣ!" የሚለው አስተሳሰብ: የሚያስኬድ ይኾናል።

፪ኛው መንገድ: አንድ መዓልት: ማለትም: የብርሃኑ ጊዜ: ሰዓቱ: ፲፪ ሲኾን፥ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ስቅለቱ፥ ሞቱና ቀብሩ የተፈጸመባት: የዓርብ ዕለት: መዓልቷ: ከ፫ ተከፍሏል። ከነግሁ (ከጧቱ) ፩ ሰዓት አንሥቶ: እስከቀትር ፮ ሰዓት ድረስ: ሰዓቱ: ፮ ነው፤ በመስቀል ላይ የተሰቀለውን የፈጣሪያቸውን ዕርቃን ለመሸፈን: ፀሓይና ጨረቃ: ከቀትር አንሥቶ: እስከ፱ ሰዓት ድረስ: ብርሃናቸውን ባለመስጠታቸው: ዓለሙ ኹሉ ጨልሞ ስለነበረ: ከነግህ እስከቀትር ያለውና ብርሃን ኾኖ የቆየው ጊዜ: ፩ መዓልት ተብሎ ተቆጥሩዋል። በዚህ መሠረት: ከቀትር እስከ፱ ሰዓት ያለው: የጨለመው ጊዜ ደግሞ: ፩ ሌሊት ተብሎ ተቆጥሩዋል። ከ፱ ሰዓት አንሥቶ እስከሠርክ ፲፪ ሰዓት ድረስ: ሰዓቱ: ፫ ነው፤ ያም ጊዜ: እንደገና: በፀሓይ ብርሃንነት ስለቀጠለ: ፩ መዓልት ተብሎ ተቆጥሩዋል፤ እስከዚህ ባለው ስሌት: የዓርብ ዕለት: መዓልቱ: ፪፥ ሌሊቱ: ፩ ይኾናል። ከዓርብ ሠርክ አንሥቶ እስከቅዳሜ አጥቢያ ያለው የጨለማ ጊዜ: ፲፪ ሰዓት ኾኖ: ፩ ሙሉ ሌሊት በመኾኑ: የዕለተ ዓርቡን ሌሊት ቁጥር: ወደ፪ ከፍ ስላደረገው: ሌሊቱ: ፪ ይኾናል። ከነግህ እስከሠርክ ያለው የዕለተ ቅዳሜው መዓልት: ማለትም: የብርሃኑ ጊዜ: በሙሉ ለ፲፪ ሰዓት የቀጠለ በመኾኑ: ፩ መዓልት ተብሎ: ከዓርቡ የ፪ መዓልት ቁጥር ጋር ሲደመር: ፫ መዓልት ይኾናል። በመጨረሻ: ከቅዳሜ ሠርክ እስከእሑድ አጥቢያ ያለው የጨለማው ጊዜ: ፩ ሙሉ ሌሊት ስለኾነ: እስከቅዳሜ አጥቢያ: ፪ የነበረው የሌሊት ቁጥር: ወደ፫ ከፍ ብሎ: ሌሊቱን ፫ ያደርገዋል።

እንግዴህ፡ በኹለቱም መንገድ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከሙታን ተለይቶ ከመነሣቱ በፊት፡ በመቃብር፡ ፫ መዓልትና ፫ ሌሊት አደረ!" ያሰኘው፡ የጊዜ አቈጣጠር፡ ይህ ነው።

## የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡ ለመዋቲው ሰው፡ ያቀዳጀው የድል አክሊል።

*ጥያቄ፡- የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡ ከአልዓዛር ትንሣኤ የሚለይበትንና የሚበልጥበትን ባሕርይ ገልጸህ ብታስረዳን?*

መልስ፡- አዎን! የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡ ከአልዓዛር ትንሣኤ ይልቅ፡ እጅግ ከፍ ያለ ብልጫና ልዩነት አለው፤ ይኸውም፡ የአልዓዛር ትንሣኤ፡ ጊዜያዊ፥ ሥጋዊና ምድራዊ ስለነበረ ነው፤ ማለትም፡ አልዓዛር፡ ሙቶና ተገንዞ፡ ከተቀበረ በኋላ፡ ራሱ፡ *"ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ!"* ብሉ፡ ላስነሣው ፈጣሪ፡ ምስክርና ማስረጃ ይኾን ዘንድ፡ እንደገና፡ በምድር ላይ፡ ለተወሰነ ዕድሜ፡ በሥጋው ኖሮ፡ እንደገና ለመሞት፡ የተነሣው፡ ለጊዜያዊ ትንሣኤ ስለነበረ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ግን፡ ዘለዓለማዊ፥ መንፈሳዊና ሰማያዊ ነው።

ያ፡ ጊዜያዊ የትንሣኤ ተአምር፡ በአልዓዛር ላይ እንዲፈጸም አስፈላጊ የኾነው፡ በመለኮታዊው የተስፋ ቃልና በነቢያት ትንቢት መሠረት፡ አምላክ፡ ሰው ኾኖ በምድር ላይ መገለጹን፥ እርሱም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑን፥ ደግሞም፡ የጊዜያዊው ኾነ የዘለዓለማዊው፥ የሥጋዊው ኾነ የነፍሳዊው ትንሣኤና ሕይወት፡ ባለቤቱ፥ ሠሪውና ሰጪው፡ ራሱ መኾኑን፡ በዘመኑ ለነበረው የሰዎች ትውልድ አረጋግጦ ለማሳየት ነበር።

ይህም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ማርያም" እና "ማርታ" የተባሉት የአልዓዛር እኅቶች፡ ወንድማቸው፡ በጠና ታምሞ፡ ሊሞት በተቃረበ ጊዜ፡ ስለላኩበት፡ ወደእነርሱ መጥቶ ሣለ፡ አልዓዛር፡ ሙቶና ተቀብሮ፡ አራት ቀን ኾኖት ነበረና፡ ኹለቱም እኅቶቹ፡ ለየብቻ ሲያገኙት፡ *"ጌታ ሆይ! አንተ፡ በዚህ ኖረህ ብትኾን፡ ወንድማችን ባልሞተም ነበር!"* ካሉት በኋላ፡ በተለይ፡ ከማርታ ጋር በተለዋወጣቸው፡ እንዲህ በሚሉት ቃላት ታውቋል፡- *"'አሁንም፡ ከእግዚአብሔር የምትለምነውን ኹሉ፡ እግዚአብሔር እንዲሰጥህ አውቃለሁ!' አለችው። ኢየሱስም፡ 'ወንድምሽ ይነሣል!' አላት፤ ማርታም፡ 'በመጨረሻው ቀን፡ በትንሣኤ እንዲነሣ አውቃለሁ!' አለችው። ኢየሱስም፡ 'ትንሣኤና ሕይወት፡ እኔ ነኝ! የሚያምንብኝ፡ ቢሞት እንኳ፡ ሕያው ይኾናል፤ ሕያው የኾነም፡ የሚያምንብኝም ኹሉ፡ ለዘለዓለም አይሞትም፤ ይህን ታምኚለሽን?' አላት። እርሷም፡ 'አዎን! ጌታ ሆይ! አንተ፡ ወደዓለም የሚመጣው፡ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደኾንህ፡ እኔ አምናለሁ!' አለች።"* [፲፰]

## ምዕራፍ ፫፣ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

### ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።

### የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ: ለመዋቲው ሰው: ያቀዳጀው የድል አክሊል።

---

**ጥያቄ:-** *"የሚያምንብኝ: ቢሞት እንኳ: ሕያው ይኾናል፤ ሕያው የኾነም: የሚያምንብኝም ኹሉ: ለዘለዓለም አይሞትም፤" የሚለው የጌታ ቃል ስለረቀቀብን: በቀላል ሊገባን አልቻለምና: ብታብራራልን?*

**መልስ:-** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ከተከተሉት ደቀ መዛሙርት መካከል: አንዱ: *"አስቀድሜ ልኼድና: አባቴን እቀብር ዘንድ ፍቀድልኝ!"* ባለው ጊዜ: *"ሙታናቸውን እንዲቀብሩ: ሙታንን ተዋቸው! አንተስ: ተከተለኝ! ኼደህም: የእግዚአብሔርን መንግሥት ስበክ!"* ባለው መሠረት: ከእግዚአብሔር እምነትና ምግባር ውጭ ኾኖ: በምድር ላይ: በሕይወተ ሥጋ የሚንቀሳቀስ ሰው ኹሉ: በእግዚአብሔር ዘንድ: ሞቶ እንደተቀበረ: እንደሬሳ የሚቆጠር ነው።[፶፱]

ሰዎች: በየግል ፍላጎታቸው መርጠው: ዕድል ፈንታቸው ያደረጉትን: እንዲህ ያለውን: የምውትነት ኹኔታ: ወደሕያውነት ሊመልሱ የሚችሉበት ኃይል ተሰጥቷቸዋል፤ ይህም ኃይል: ይህንኑ ምውትነት: በቤዛነቱ: ፈጽሞ አድሶ በለወጠው: በኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒትነትና በቅድስት ድንግል ማርያም እናትነት ማመን ነው፤ አዎን! ሰዎች: ይህን ሃይማኖት ተቀብለው፥ ምግባሩንም አጽንተው በሚኖሩበት ጊዜ: ይህ ምውትነታቸው ተወግዶ: ሕያዋን ይኾናሉ። አለዚያ: በኢየሱስ ክርስቶስ በተገኘው ሃይማኖትና ምግባር ጸንተው ለመኖር ካለመፍቀዳቸው የተነሣ: በተያዙበት ኃጢአታቸው ምክንያት: የሚጠብቃቸው: የሥጋውም፥ የነፍሱም ሞት ስለኾነ: በምውትነታቸው ይቀጥላሉ።

በዚህ አንጻር: በኢየሱስ ክርስቶስ በተገኘው ሃይማኖትና ምግባር ጸንታ በመኖርዋ: ሕያው የኾነችው: የሰዎች ነፍስ: ከሥጋዋ ብትለይና የኖረችበት ሥጋ: ወደመቃብር ቢወርድም: እርሷ: በለበሰችው: የክርስቶስ መንፈሳዊ አካል ምክንያት: ሕያው ኾና: ዛሬ: ወደገነት ገብታ: በዚያ ትቆያለች፤ ኋላ ደግሞ: በዚህ ሕያውነቷ: በገነት የቆየችበትን ሕይወቷን: በመጨረሻው ትንሣኤ: አዲሱን የትንሣኤ አካል ለብሳ በገባችበት: በእግዚአብሔር መንግሥት ትቀጥላለች፤ የእግዚአብሔር ሕይወት ባለቤት ኾና: ለዘለዓለም ትኖራለች ማለት ነው።

### ስለትንሣኤ ዘጉባዔ።

**ጥያቄ:-** *ጠቅላላው: የሰው ዘር የኾነው ፍጡር: ከሞተና ከተቀበረ፥ ከበሰበሰም በኋላ: የሚነሣበትና ከመቃብር የሚወጣበት: "ትንሣኤ ዘጉባዔ" የሚባለው: የሙታን ትንሣኤ ምሥጢርስ እንደምንድር ነው?*

**መልስ:-** **የጌታችን የኢየሱስ** ክርስቶስ ትንሣኤ: ለሰዎች ኹሉ ትንሣኤ በኵር: ማለትም: **በር ከፋች፥ መጀመሪያ** ነው።